አድርጋ ለሞኑን ቀረበችኝ:: ሜሪም ከበፊቱ ባነሰ ሁኔታ ብዙም ሳትወደኝ እንደሁኔታው ሀይ ትለኛለች እኔም በአዕምሮዬ አዋራሁሽ:: ማለቴ «በአቅሌ»



# ምዕራፍ አምስት

መጀመሪያ ስገባ ከዋናው በር ግራና ቀኝ የቆሙ ባለስድስት እጆች አስፈሪ ሰው መሳይ ፍጡሮች በጠቆረ ድንጋይ ተቀርፀው ወደ መቃብር ስፍራ እንኳን ደህና መጡ ይግቡ የሚሉ ይመስል ስድስቱን እጆቻቸውን በየአቅጣጫው ቀስረው ያስበረግጋሉ::

ፀጥ እረጭ ጨለም ያለው ቤት ውስጥ ገብቼ ቆሜ ሳለሁ ድምፅዋ ከአካሏ የበረታ ሰውነቷ ከድምፅዋ እጅግ ድክምክም ያለች ሴት መብራት አብርታ ያለምንም ፈገግታ ለደቂቃዎች አስተዋለችኝ . . . ከላይ እስከታች:: ለእርሷ ምን እንደገረማት ባላውቅም እኔ ግን እንደዚህ የድምፅና የአካል ልዩነት አይቼ ስለማላውቅ ይኸው ጉዳይ አስደመመኝ::

«ምን ሂና /በዚህ በኩል/» የሚል ትዕዛዝ ሰጥታኝ ረጅሙን ኮሪደር ተከተልኳት::

ሥራውን ያገኘችልኝ ሴት ባሏ ስለሴትየዋ የነገራትን ሁኔታ አስቀድማ ብትነግረኝም የሴትየዋ አስፈሪነትን በተረት ላይ ከሚነገሩት አስማተኛ ሴቶች በላይ ሆኖ አገኘሁት:: ቤቱም እንደመቃብር የከበደ ቀፋፊ ስሜትን የሚፈጥር ነበር::

እቤቷ የደረስኩት ገና በቀኑ ቢሆንም የሠራተኛ ክፍል እንደደረሰችኝ ሌሎች እንደሚያደርጉት ስለሥራዬ ሁኔታ ምንም ሳታብራራ «ነቢ /ተኚ/» ብላኝ ሄደች። እኔ አረብኛ አልገባኝም ወይስ ይህች ሴት ልታስተኛኝ ነው የቀጠረችኝ?! እኔ እንጃ።

ፀጥ ባለው ቤት የነገሰው የብዙ ሰዓቶች ድምፅ ቲክ ታክ እያለ ሙሉ አዕምሮን ሰብስቦ የመግዛት ኃይል አለው። ይህ ድምፅ ሙሉ ሀሳቤን እየወሰደ ከዚህ በፊት በማላውቀው አይነት ምስጥ እንድል አድርጉኝ በፍራቻ ስለዘፈቀኝ ድምፁን ጠላሁት። በድምፁ ልክም ድው ድው የሚለው የልቤ ምት ድምፁን ጨምሮ በፍራቻ አሰቃየኝ። በር ላይ ካየኋቸው የሀውልት እጆች ተንጋግተው መጥተው አንቅ የሚያደርጉኝ እየመሰለኝ በሩ ላይ አፍጥጬ እንዴት ልከላከላቸው እንደምችል አውጠነጥን ጀመር። ተረጋጋሁና . . . ቢመጡ እሰብራቸዋለሁ። ሽክላ ቢበዛ ደግሞ ለስላሳ ድንጋዮች ናቸው። ምን ነካኝ . . ምን ነካኝ። ፈራሁ።

በሚቀጥለው ሌሊት እመቤቱ በዚያ ጠንካራ ወንዳማ ድምፅዋ ስለሥራ ሁኔታ አስረዳችኝ።

«የምንተኛው ቀን ነው። የምንነሳው ደግሞ ሌሊት ነው ገባሽ? ያ ማለት የሥራ ሰዓትሽ ሌሊት ነው። ቀን ምንም ከሽታ መስማት አልፈልግም።»

«የመጀመሪያ ሥራሽ በቤቱ ውስጥ ያሉትን ሀውልቶች ባጠቃላይ ማፅዳት ነው። አንድ ሀውልት ላይ



ብናኝ አቧራ ማየት አልፈልግም። ለመሬቱ ለዕቃዎቹ ለወንበሩ ለመስታወቱ ለመስኮቱ ለወጥ ቤቱ ለባኞው ፅዳት ግድ የለኝም። ደስ ሲልሽ አፅጂአቸው ደስ ካላለሽ «ፊ ሲቲን ዳህያ» /ጀሀነብ/ ግድ የለኝም። ሀውልቶቹ ግን በህይወቴ አስፈላጊ ነገሮች ስለሆኑ ተጠንቀቂላቸው። ለእነሱ ብዬ የገዛሁት ሻንፑ አለ ካፀዳሻቸው በኋላ የራሳቸውን ክሬም ትቀቢአቸዋለሽ።

በማግሥቱ ጠየቀችኝ «ሀውልቶቹን አፀዳሽ?» ሀውልት ሀውልት እያለች የምትደጋግመውን ቃል ጋብ ብታደርግና በምትኩ ለቅርፆቹ ትክክለኛ ስማቸውን ሰጥታ ቅርፃ ቅርፆቹን ብትል እኔም ስለሞት ማሰቤን ላቆምና ፍራቻዬም እንዲያበቃ በማሰብ ላርማት

«ቅርፃ ቅርፆቹንም ቤቱንም በደንብ አፅድቼአለሁ እመቤቴ!» ከወገቤ ሰበር አልኩ።

አስበረገገችኝ ድምፅዋን አስጩሀ «ሀውልቶቹን ቅርፃቅርፅ ብለሽ እንድትጠሪያቸው አልፈቅድልሽም። ስማቸው ሀውልት ነው ገባሽ ሀ-ው-ል-ት!»

እራሴን በእሺታ ነቀነቅኩ።

ሁሌ ማታ ማታ አንድ ሰዓት ላይ ሽርጥ ያሸረጡ የሆቴል ሰዎች መጥተው ላንድ ትንሽ ድግስ የሚበቃ ጣፋጭ ምግቦችን ትተው ይሄዳሉ። ሲነጋ ሲል እንደገና መጥተው ያልታጠቡ እቃዎችን ሰብስበው ይመለሳሉ።

በሳምንት አንዴ የላውንደሪ ቤት ሰዎች መጥተው የቆሸሸውን የቤቱን ልብስ ሰብስበው አጥበው ተኩሰው ይመልሳሉ::

እንዲህ አይነት ቤት አጋጥሞኝ አያውቅም:: ሴትዮዋ በጣም ሀብታም ሆና ግን ድሀ ለመሆን እየጣረች ያለች ትመስላለች:: የምግቦቹ የሆቴሉ ወጪ ቀላል አይመስለኝም:: ለምን እንደሌሎቹ የወጥ ቤት ሠራተኛ ቀጥራ እቤቷ የጣፈጠ ምግብ በቀላል አስቤዛ የማድረግ ሀሳብ እንደሌላት አላውቅም:: ገንዘቧን ለማውጣት መንገድ የምትፈልግ ዓይነት ናት::

እርሷ እንዳለችው ሀውልት የማፅዳት ሥራዬን በሚገባ አከናውናለሁ:: ሀውልቶቹ ከሥራቸው የወከሉት ሬሳ ባይኖርም በየቦታው በሰው ቁመት ልክ ተገትረዋል:: ምናልባት በሀውልቶቹ ብዛት ያህል በየቦታው ተሰቅለው የሚታዩት የቀን መቁጠሪያዎች ቤቱን የተለየ አድርገውታል:: ምን ዓይነት ቤት ነው:: ሰዓት . . . ቁጥር . . . ቀን . . . ቁጥር ሀውልት ሰዓት የቀን መቁጠሪያ . . . ማለት የፈለጉት ሞትን ይሆን? ሞት . . . እኔንጃ ብቻ ስነቃም ስተኛ የሰዓቶቹ የቀን መቁጠሪያዎቹ . . . የሀውልቱ . . . በብዛት መገኘት ሞትን በጥሞና እንዳስብ አድርጉኛል::

በዚህ ቤት ትልቅ ሚስጥር እንዳለ ስለገመትኩ ብቻ ፍራቻዬን ዋጥ አድርጌ ሥራዬን ለመቀጠል ባስብም ስለሞት ማሰቤን ማቆም ያለመቻሌ እንዳያሳብደኝ ፈራሁ::



ከህብረተሰቡ ተገልሎ ብቻውን የቆመው ይህ ቤት ስልክ የለውም . . . ቴሌቪዥን የለውም . . . ሙዚቃ የለም . . . ጋዜጣ የለም . . . የሚመጣ የለም:: ሀውልት ብቻ . . .

የሴትዮዋ ሁኔታ . . . ልብሷን አዙሮ መልበስ . . . ጫማ አጣሞ መልበስ . . . እብድ ናት? እኔንጃ:: ንግግሯ ውስን ነው ስለጤንነቴ ጠይቃኝ አታውቅም:: ሰላምታ የለም::

«ሀውልቶቹን አፀዳሽ?»

«የትኛውን ሀውልት ትወጃለሽ?»

«መሞት ወደድሽ ዛሬ? ስትወድጂ ሀውልት እንድቀርፅልሽ ንገሪኝ እ! ዘር ማንዘሮችሽ ሊረሱት የማይችሉት አይነት ሀውልት ልቀርፅልሽ ቃል እገባልሻለሁ»

«በስመአብ ምን ገፊዋ ናት» አልኩኝ በሆዴ:: እኔ ገና ህያዎቹን ዓመታቴን በደንብ ሳላጣጥም ለወደፊቴ በማሰብ ደፋ ቀና ስል ባጭር ልትቀጨኝ ሀውልት ልቅረፅልሽ የሚለው ጥያቄዋ ያስገርመኛል::

የተለያየ ቤት የተለያየ የሕይወት ልምድ አለው:: እኔም ለሥራ የምቀያይራቸው ቤቶች በገንዘብ ብቻ ሳይሆን የህይወትን ድሎትን ሀዘንን ችግርን ተስፋን በመጠኑም በሌሎች እያየሁ ብቻ ለራሴ ኖራዋለሁ:: ለምን እንደሆነ እኔንጃ ይህ የቤት ሠራተኝነት ሥራዬ ወደፊት ለሚኖረኝ ህይወቴ የማይበገር ጥንካሬን የካበልኝ

ይመስለኛል። የብዙ ህይወቶች ቅንብርም ጥሩ ትምህርት ሰጥቶኛል። ልጅ ሳልወልድ የሕፃን አያያዝን የምታውቅ እናት ሚስት ሳልሆን የባል አያያዝን አውቄአለሁ። ለሴት ትልቁ ልምዷን ማለት ነው።

የሰው ሚስጥር የማወቅ ጉብዝናዬን ተጠቅሜ ከዚህ ድብርታም ቤት ለመውጣት ብጥርም ማወቅ አልቻልኩም። ብቻ ብዙ ሚስጥሮች እንዳሉ ይሰሙኛል።

አንደኛ የባልና ሚስቶቹ የእድሜ መራራቅ ሁለተኛ የሀውልቶቹ ሦስተኛ የእመቤቴን የመኝታ ክፍል እንዳይም ሆነ እንዳፀዳ ያለመፈቀዱ ሁኔታ አራተኛ የእመቤቴ ፀባይ እንዲህ እንዲሆን ያደረገውና የገፋፋው ምክንያት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ጓደኞቼ እነ ቅድስት የሰው ሚስጥር ላይ የማድፈጤን ጉዳይ ከአወራሬ ስለሚያውቁ አጉል ፀባይሽን ትተሽ የራስሽ ህይወት ላይ ብታደፍጪ ይሻልሻል ብለው ይገስፁኛል። እግዜር ለዚህ ግርድና ባይዳርግሽ ኖሮ ጥሩ የወንጀል መርማሪ ወይ ሚስጥር ፈልፋይ ሰላይ ይወጣሻል።« አዕምሮሽ ነገር ለመገጣጠም እግሮችሽም ኮቴ የማያሰሙ ጆሮዎችሽም ሳተላይቶች ናቸው» ብለው ይተርቡኛል። እኔም የሚያስደስተኝ ልማድ ስለሆነ ሳላፍር በተለያየ መልኩ ልጠቀምበት ወደኋላ አልልም።

የሥራዬ መጨረሻ አመድ አመድ ቀለም ቀለም ብረት ብረት ወደሚሸተው ቀፋፊ ክፍል ገብቶ ጅምር ሀውልቶችን ማለቅ አለማለቃቸውን ማየት ነበር። ካለቁ



የሚሰጣቸውን ቦታ እመቤቴን ጠይቆ እንደሌሎቹ ሀውልቶች የፅዳት አገልግሎት እንዲሰጣቸው የማድረጉ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶኛል። ግራ የሚያጋባው ነገር የሀውልቶቹን ማለቅ አለማለቅ እራሴው አውቄ ሥራ መጀመሩ ነው። ሴትየዋ በዚህ ጉዳይ ገና ስገባ አስጠንቅቃኝ እኔም ተስማምቼአለሁ። ይህን ካላደረግሁ ግን በደሞዝ እንደምትቀጣኝ ተነግሮኛል።

እራሷን የምትመስል ሴት ምስል እየሰራች ባለችበት ሰሞን ከመቅረጪያ ክፍሏ ስትወጣ እንባዋን ስትጠርግ አንድ ሦስቴ አጋጥማኛለች። ሰው ለራሱ ሀውልት ማዘን ቢችል በርግጥ ከእርሷ የበለጠ ለማዘኑ ጥርጥር የለውም። ደግነቱ ሰው ለራሱ ሀውልት እንዲያዝን ዕድል አልተሰጠውም። እና ለምን ይህች ሴት እድሉን ያገኘት ይመስል ስለራሷ ምስል ሀውልት ቀርፃ ታነባለች? የዕንባዋ ምክንያት ባይገባኝም ከፍቷት ሳይሆኑ ይንበጫበጫል።

ጨረስኩት ብላ የደመደመችው ሀውልት ያላለቀ መስሎኝ እስኪያልቅ ስጠብቅ ጉድ ሰራኝ። ይኸው የራሷን መልክ የያዘው ሀውልት አንድ ጡት ብቻ አለው። እኔ ሁለተኛውን ጡት እንዲሠራለት ስጠብቅ ባንድ ጡት ብቻ ፀናና ደሞዜን አስቆረጠብኝ። መቼም ስምምነት ነውና አልተቃወምኩም። ግን ለመጀመሪያ ጊዜ እመቤቴ ፊት ቆሜ ባለአንድ ጡት ሴት ተፈጥራ እንደማታውቅ ተከራከርኩ። ለነገሩ እዚህ ቤት ገና ስገባ ያፈጠጡብኝ እነዚያ ባለስድስት እጆች ጥቁቁር ሀውልቶችን የመሰለ

ፍጡር የለም፡፡ ብቻ በዚህ አንድ ጡት ጥያቄ መረታት የለብኝም፡፡

በቀስታ እንድቀርባት ጠየቀችኝ፡፡ ቀረብኳት፡፡ በእጇ ሁለት ሶስቴ ጉንጬን እንደሚስም ሰው አመቻችታ ባለ በሌለ ሀይሏ በጥፊ አጮለችኝ፡፡ ጆሮዬ ጭውውው ሲል ተሰማኝ፡፡ ግን ጥፊው ለርሷው ዞሮ ያሳመማት ይመስል ከኔ ቀድሞ የሷ ፊት ቲማቲም መሰለ፡፡ ይህ ጥያቄ ከኔ ጥፊ ይልቅ ሳያማት የቀረ አይመስለኝም፡፡

«ይህን አምስት ሰዓት ተደበቂ አለበለዚያ ከዚያ በፊት ካየሁሽ የማደርግሽን እኔ እራሴ አላውቅም፡፡» አለችኝና እራሷ ከራሷ የፈራችልኝ ሁለት ሰው መሰለች፡፡

ያለችኝን አምስት ሰዓት ክፍሌ ተደብቄ ስወጣ ፊቷ ላይ ምንም እንዳልተፈጠረ ሆኖ እርጋታን አነበብኩ፡፡ ከአናደዳት የአንድ ጡት ነገር በፊት የነበራት ፊት ተመልሶ ቀዝቃዛ አስተያየቷን አስፍናለች፡፡ ይህች ሴት ካየኋቸው ሴቶች ሁላ ደስ የሚል ፀባይ አላት፡፡ ቅድም ተጣላን አሁን ሰላም ነን፡፡ ጥላችን ቂም ሳያስይዛት እንድትረሳው አምስት ሰዓታት ብቻ የሚፈጅባት ከሆነ ባሏና ዘመድ ጓደኞቿ በዚህ ፀባይዋ እድለኞች ናቸው ማለት ነው፡፡ ግን ዘመዶች ጓደኞች እናት አባት ቢኖራት ነበራ!! ስራዬን ወደድኩት!!

እንደበፊቱ ሳይሆን የዚህ ቤት ጥበብ እየታየኝ መጥቷል፡፡ የእመቤቴ ችሎታ እጅግ የሚደነቅ መሆኑን አመንኩ፡፡ ያስፈራሩኝ ቅርፃቅርፆች ለኤግዚቢት ከሚቀርቡ



ጥበቦች አይተናነሱም፡፡ ቅርፃ ቅርፆቹ ውስጣቸው ያፈኑትን ሀዘን ቀስ በቀስ በውበታቸው ያነቡታል . . . ደጋግመው ሲታዩ፡፡

እራሷን ጥበብ ውስጥ የደበቀች ሚስኪኗ ሴትም በደንብ ስትታይ ከላይ የሸፈናትን የቁጡነት መንፈስ ተገርስሶ በምትኩ ደግነትን ከልክ በላይ የተጐዳ ስብር ልቧን ሀዘኗን ቀስ እያለ እንደ ቅርፃቅርፆቿ ይገለጣል፡፡

ቆይቶ የገባኝን የቅርፃቅርፅ ውበት ለማድነቅ ማንም ሳያየኝ አዳዲሶች ገና ያላለቁ ቅርፃቅርፆች ወደሚገኙበት ክፍል ከመግባቴ በፊት ሰዎቹ ፎቅ እንዳሉ በትክክል አረጋገጥኩ፡፡ መብራት አበራሁና ማየት ስጀምር ኮቴ ሰማሁ፡፡ ያለሥራ ሰዓቴ ስለሆነ ለመግባቴ ምክንያት ማቅረብ የምችል ስላልመሰለኝ ገብተው እስኪወጡ ቁምሳጥን ስር ገባሁ፡፡

እመቤቴ ከተደበቅሁበት ፊት ለፊት ተሰቅሎ ያለ ስዕል አወረደችና ግድግዳው ላይ ያለ ማብሪያና ማጥፊያ በጣቷ ተጫነች ከጐን ያለ ግድግዳ ብርግድ ብሎ የተከፈተ ሞሰለኝ፡፡ ደነገጥኩ፡፡ግድግዳ መሳዩ ገፅታ የሚከፈት የሚዘጋ ሚጥራዊ መደርደሪያ ሆነ፡፡ ቀጠለችና በመስታወትማ ፕላስቲክ የተቀመጠ ዱቄት አወጣች፡፡ ከዱቄቱ በትንሽ ወረቀት ቆንጥራ ጠቀለለችና በጥንቃቄ መልሳ እንደገና ያን ማብሪያ ማጥፊያውን ተጭና ግድግዳውን እንደነበረ መለሰችው፡፡ ስዕሉን ሰቅላ ሁሉም

ነገር እንደበፊቱ መሆኑን ለማረጋገጥ ገልመጥ ብላ ዘግታ ወጣች::

በሚቀጥለው ቀን ምሽቱን የሚያሳልፉበትን ሳሎን ሳፀዳ ጠረጴዛ ላይ ያን ዱቄት ስትቆነጥር ያየሁበትን ትንሹን የወረቀት ኪስ አገኘሁ:: ውስጡም የቀረ ዱቄት አለ:: እጄ ላይ በትንሽ ፊሰስ አድርጌ በጣቶቼ ነካሁትና እየፈራሁ ምላሴ ላይ አደረግኩ . . . ስኳር ስኳር ይላል:: መርዝ እንዳይሆን ስለፈራሁ የነበረበት ትቼው ሥራዬን ቀጠልኩ::

የመደርደሪያው ነገር እንቅልፍ ነሳኝ:: ሰዎቹ ሲገኙ በእርጋታ ሚስጥረኛውን ግድግዳ ጠቅ ጠቅ አድርጌ መደርደሪያ እከፍትና በውስጡ ያገኘሁትን የፎቶ አልበም ክፍሌ ቁጭ ብዬ አገላብጣለሁ:: ያን ዱቄት የያዘው ይህ መደርደሪያ የቀን መቁጠሪያዎች ደብተሮችና የፎቶ አልበሞች ብቻ ሲኖሩበት ገንዘብና ጌጥ መሳይ የካዝና ንብረቶች የሉበትም::

በዕድሜ በጣም የሚያንሳት ወጣቱ ባሏ አልበሞቹ ውስጥ አንድ ቦታ እንኳን የለበትም:: በምትኩ በልጅነቷ ባል ክንድ ውስጥ እንዳለች በቬሎ ደምቃ ትታያለች:: አፍንጫዋ ስር ያለው የተፈጥሮ ምልክትን እዚህ ፎቶ ላይ ባላየው ያሁኗ ሴት ናት ለማለት ያስቸግረኝ ነበር:: በጣም ቆንጆ ነበረች:: አልበሟ ላይ ያለ ፈገግታዋንም ከገባሁ ጀምሮ አይቼም አላውቅም:: የልጅነት ባሏ ይፍታት



ይሙት እርግጠኛ ባልሆንም የህውልቶቹ እና የሀዘኗ መንስኤ የባሏ ሞት ይሆናል ብዬ ገመትኩ::

ደብተሮቹ ሁሉ የተፃፉት በአረብኛ ነው:: ድንገት ከስር ውትፍ ያለች ጉስቋላ ቀይ ደብተር ብጤ ላይ አይኔ አረፈ:: አንስቼ ሳገላብጣት በተለያየ ዓይነት ብዕር የተሞነጫጨረ ፅሁፍ አለው:: የብዕሩ መለያየት በተለያየ ቀናት መፃፉን ያመለክታል:: ይህ ደብተር ስለሴትዮዋ ብዙ ወሬ ስለሴትዮዋ ያወራልኛል ብዬ ያለምንም ፍራቻ ደብተሯን ለቀም ሳደርግ ያችን ግብፃዊት አረብኛ ቃላቶቹን እንደምትተረጉምልኝ በማመን ነበር::

በዕረፍት ቀኔ ደብተሯን ይዤ ግብፅዋ ሴት ቤት ስሄድ በፍላጐት የበራ ፊቴን አይታ «ዋህሽቱኪ» /ናፍቀሽኝ ነው?/ ብላ ቀለደች::

«ነአም» /አዎን/ አልኳትና ቀድታ ያመጣችልኝን ከባድ የቱርክ ቡና እንቢ አልኳት::

«የቱርክ ቡና የምትወጂ መስሎኝ ነበር::»

«ወድጄው አላውቅም:: አገራችን የቡና እናት መሆኗን ታውቂያለሽ! እንዴት ታዲያ የሌሎች ቡና ይጥመኛል?!»

«እ! ለሱ ነዋ! እሺ ቁምነገር ለምን መጣሽ? ከሥራ አባረሩሽ?»

«አይ! አንድ የማስተዋሻ ደብተር አገኘሁ የተፃፈበትን ነገር ለማወቅ ጓጓሁ:: ደብተሩን ያገኘሁት

በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ስለሆነ ይህን ያህል አስፈላጊ ነገር ያለው አይመስለኝም:: ሞኝ ሀሳብ ስላለኝ ነው:: ትርጉሙን በእንግሊዘኛ ቃል በቃል እንድትተረጉሚልኝ ነው ያመጣሁት:: ለዛ ዋጋ በልብስ አጠባ እስማማለሁ:: በሚቀጥለው ዕረፍቴ ማስታወሻው ያለውን ፅሁፍ ለማወቅ በመቋመጥ በርሬ ስለምመጣ አደራሽን! እ!»

ሳምንቱን ባገኘሁት አጋጣሚ እዛ መቅረጨ.ያ ክፍል እየገባሁ መደርደሪያው መከፈት አለመከፈቱን እንዲያስታውቀኝ ማብሪያ ማጥፊያውን የሸፈነው ስዕል ላይ ሳያስታውቅ ለምልክት ያስቀመጥኩትን የወረቀት ቁራጭ እያየሁ የማስታሻዋን መሰረቅ እንዳታውቅብኝ ተሳቀቅኩ:: የዕረፍቴ ሰዓት ደረሰ:: ወደ ግብፅዋ ቤት ከነፍኩ::

«ውሸታም ነሽ» አለችኝ ገና ስገባ «ይህን የመሰለ ጽሁፍ ያቀፈ የግል ማስታወሻ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ወይ ሳይቀደድ ወይ ሳይቃጠል አይጣልም:: ከየት አመጣሽው? እመቤትሽ ታሪኳን የሚተርከውን ማስታወሻዋን አንቺ እንድታነቢው አስተካክላ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ከመጣል ይልቅ ጋዜጦች ታሪኳን በመጀመሪያ ገፃቸው እንዲያትሙት መላክ ይቀላት ነበር::»

ሚስጥሩን ለማወቅ አይኔን በልጥጬ ያመጣሁበትን መንገድ ባጭሩ አስረዳኋት «በእውነቱ ቃል በቃል ተርጉሜልሻለሁ:: ማንበብ ስጀምር በፊልም



የሚከሰት ታሪክ እንጂ እውነተኛ አልመሰለ ብሎ ስበኛል ብላ አጋነነችልኝ::

«በተጨማሪም የዚችን ሴት የተለየ ስለመሆን ባሌ ሁሌ ተገርሞ ሲያወራልኝ ሳላውቀው በደንብ ሳውቃት በውስጤ ሳልጓጓ አልቀረሁም:: ከዚህ የሚቀጥል ሌላ ደብተር አለ ፈልገሽ አምጪና እናንበበው:: ሰው የራሱን ህይወት በየጊዜው አጋጣሚውን ደስታውን ፍቅሩን ስሜቱን ሀዘኑን ቢፅፍ ሁሉም ሰው በራሱ ታሪክ ጀግና ደራሲ ይሆን ነበር:: ታውቂያለሽ! የዚች ሴት ታሪክ ያሳዝናል:: እኔም በየቀኑ የሆንኩትን ብፅፍ የህይወቴን ልዩነት ለማወቁ ይረዳኛል:: ግን የኔ ህይወት በጣም ቀላል ናት» አዘን አለች:: ገረመችኝ:: ነገረ ሥራዋ ያሳዝናል ባለችው የእመቤቴ ታሪክ ቀንቼአለሁ የሚል አይነት ሆነብኝ::

«የእኔ ህይወት አሰልቺና ተደጋጋሚ ነው:: አዲስ ነገር ተፈጥሮብኝ ወይም እራሴው ልፈጥር ሞክሬ አላውቅም:: ጠዋት እነሳለሁ ልጄን አጥባለሁ አበላለሁ ለባሌ ምሳ እሠራለሁ:: ከምሳ በኋላ ልጄን አስተኛለሁ:: ለባሌ ቡና አፈላለሁ:: ማታ ባሌ ከመምጣቱ በፊት ልጄ ያተራመሰውን ቤት በትክክል አስተካክላለሁ:: ባሌ ደክሞት ይመጣል:: ትንሽ ቁጭ ብለን ቴሌቪዥን እናያለን:: አንዳንዴ እንደባልና ሚስት አንዳንዴ እንደ እህትና ወንድም እንተኛለን:: በጣም አንጣላም በጣም አንፋቀርም:: አንዳንዴ ልጃችንን ልናጫውት የመጫወቻ ስፍራ አንዳንዴ ሱቅ እንሄዳለን:: ታዲያ እኔ እንደዚህች ሴት ስለህይወቴ

መፃፍ ቢኖርብኝ በየወሩ መጀመሪያ ላይ የአንድ አንቀፅ ውሉዬን እፅፍና ከዛ በየቀኑ እንደትናንትና! እንደትናንትና! እንደትናንትና! እያልኩ የተቀሩትን ሀያ ዘጠኝ ቀናት እንደትናትና ብዬ ልደመድም ነው ማለት ነው:: ታዲያ ይህን ህይወት ትይዋለሽ?! ውስጤ ሁሌ የሚያልመው ነገር ክንፍ ላውጣና ልብረር ይለኛል:: ይህ ጉዳይ ደስተኛ አያደርገኝም::»

«ኡም ሰዒድ /የሰኢድ እናት/» እንደኔ ናት ማለት ነው:: እኔም መግለፅ አልቻልኩበትም እንጂ የተመሳሰለ ህይወት ይሰለቸኛል እንዳለችው ብበር ደስ ይለኛል::

ያለችው አኗኗሯን በጥቂቱ አይቼው ነበር:: ይህን ሥራ ከመጀመሬ በፊት እዚህች ግብፅ ቤት ለአስራ አምስት ቀናት ሰርቼ ነበር:: እዚህ አገር ከገባሁ በልጇ ስም እንድጠራት እመቤቴ ሳልላት የሰዒድ እናት ብዬ እንዳቀርባት የፈቀደችልኝ ብቸኛዋ አረብ ሴት ነች:: ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ ግን የወር ደሞዝ መክፈል እንደሚከብዳት ነግራኝ በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ለተወሰኑ ሰዓታት ብቅ እያልኩ ልብስ አጥቤ እንድተኩስላት ብቻ በርካሽ ዋጋ ቀጠረችኝ:: የሆቴል ሰራተኛው ባሏ ሥራው ከብዙ ሰዎች ጋር ስለሚያገናኘው ሥራ በቀላሉ እንደሚያገኝልኝ በማመን በርካሽ እርሷ ጋር መሥራቱን ተቀበልኩ::



እንዳሰብኩት ሥራ አግኝቶልኝ ሀውልቶቹ ቤት አስቀጠረኝ:: ከዛ በኋላ ግን ባሏ ሥራ ስላስቀጠረኝ ውለታዋን እንድከፍል በነፃ እየሄድኩ እረዳታለሁ::

«እህና አፍሪቃ አኽዋት /እኛ አፍሪካዎች ወንድማማች ነን/» እያለች ወደ ስጋዋ አቅርባ ከገንዘቧ አራቀችኝ:: አዲሱ ሥራዬ ላይ ለመስከኔ እርግጠኛ እስክሆን ኡም ሰኢድ ጋር በየሳምንቱ መጨረሻ እየሄድኩ ከባዱን የቱርክ ቡናና አጠባ ሳልወድ ተጋትሬ ወደ ቤቴ እመለስ ነበር::

«እንዴ! ያች ትንሽ ማስታዋሻ ይህ ሁላ ሉክ ወጣት?»

«በቋንቋው የተነሳ ነዋ:: አረብኛ ለእያንዳንዱ ድርጊት የራሱ የሆነ አጭር ቃል አለው:: ታዲያ ወደ እንግሊዘኛው ልተርጉመው ስትይ በአረብኛ የፃፍሽትን አንድ ቃል ለመተርጐም ሦስት አራት ቃላት ተጋግዘው ያችን አንድ ቃል መተካት አለባቸው:: አረብኛ ሰፊ ነው:: ለዚህ ነው በእንግሊዘኛ ሲጻፍ የበዛብሽ:: አንቺ ደግሞ በቋንቋሽ ልፃፍ ብትይ ቋንቋሽ ከእንግሊዘኛው ስለሚያንስ፤ በቃላት ብዛት ማለቴ ነው፤ ተመጣጣኝ ትርጉም ለማግኘት ቃላት ማጋጨት ስለሚኖርብሽ ይበልጥ ይበዛል::»

«በጣም አመሰግንሻለሁ::»

ከመውጣውቴ በፊት «ዛሬ አጠባ የለኝም የሚቀጥለው ሳምንት መጥተሽ ማጠብ አለብሽ:: ቃልሽን ጠብቂ!»

የምኖርበት ቤት ከግብያቹ ቤት በጣም ቅርብ ስለሆነ ራመድ ራመድ አልኩ ቸኩዬ ለማንበብ:: እቤት ስገባ እነቅድስት የሉም:: ተመስገን ንባቡን አያቋርጡኝም:: ወረቀቱን ገልጬ ለማንበቡ ተደላደልኩ::

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

«ምነው በጣም የደከመሽ ትመስያለሽ? የስፖርት ቤቱ የገጠመውን አዲሱን የስፖርት መሣሪያ ሰውነትሽ አልወደደው ይሆናል ለስ ያለ ውሀ የገላ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ሙይና አብረን እንነከር ቀለል ይልሻል» አለኝ ሰሚር ገና ከሥራ ሲገባ የዛን እለት::

ክንዴን ሲነካኝ ክንዴ ውስጡ በጣም የመለብለብ ህመም ተሰማኝ:: «ውይ ክንዴ ለበለበኝ» አልኩ::

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተለይ የግራ ክንዴን የመለብለቡ ህመም የዘወትር ስቃዬ እየሆነ መጣ:: ይህም ሕመም እያለኝ ሆስፒታል አልሄድኩም:: ባሌንም ስለህመሜ ነግሬ ላስጨንቀው አልፈለግኩም:: እናቴን የገደላትን የጡት ነቀርሳ አስቤውም አላውቅ:: በህይወቴ



ለደቂቃ እንኳን ቢሆን የዚህ በሽታ ባለቤት እሆናለሁ የሚል ፍራቻ አልነበረኝም::

ለዕረፍት ከባሌ ጋር ውጭ አገር ለሽርሽር ሄደን በነበርንበት ጊዜ ከባህር ዳርቻ ጉዞ በኋላ ባለንበት ሆቴል በባኞ ቤት መስታወት ሁለቱን ጡቶቼን ሳይ ከቆየሁ በኋላ ባሌን ጠራሁና «ጡቶቼን ተመልከታቸው ዛሬ በጣም የሚያስቅ ቅርፅ አላቸው» አልኩት::

ሰሚር ነገሩን በቀልድ አላለፈውም:: ፊቱም እንደመሸበር ብሎ «ጡቶችሽ እንደበፊቱ አይደሉም:: ይህን ከዚህ በፊት አይቻለሁ:: ያሁኑ ግን አሳሳቢ ለውጥ ነው ሆስፒታል መታየት አለብሽ::» አለና በሚያጠና አይነት አነካክ የጡቶቼን ዙሪያ ነካ:: የግራ ጡቴ ላይ የሚጠጥር ነገር እንዳለ ነገረኝ::

ወደ ሆስፒታል እየሄድን እያለ የእናቴን ስቃይና ነቀርሳ በጣም አስታወስኩ:: ከልቤም

«አምላኬ እባክህ የእናቴን እድል አትስጠኝ!» እያልኩ በፀሎት አነበነብኩ:: የሚሾፍረው ባሌም ውስጡ የሚተራመሰውን የጡቶቼን ጥርጣሬ እንዳይወጣበት ለማፈን ድምፁን ዋጥ አድርጐአል::

የመጀመሪያው የምርመራ ውጤቱ ለሁለተኛው ተላለፈ:: ሀኪሞቹ ያዩትን ለማረጋገጥ ብዙ ዓይነት ምርመራ ተጠቀመዋል:: ከዶክተሮቹ ፊት ላይ ምን እንደሆንኩ ማንበብ ባያቅተኝም እነሱ ግን በግልፅ ስለህመሜ አላስረዱኝም:: የሚሉኝ ነገር ቢኖር ተስፋ

መቁረጥ እንደሌለብኝ ነው:: ዶክተሬ ለሆነ ጉዳይ ካለበት ሲንቀሳቀስ የምርመራ ውጤቴን የያዘውን ፖስታ ሰርቄው ወደ ሌላ ዶክተር ሄድኩ::

ለዶክተሩ የእህቴ የምርመራ ውጤት እንደሆነ ዋሽቼው ስለእህቴ መጨነቄን ነገርኩት:: ዶክተሮቹም የሆነችውን በትክክል ሳይነግሩን እንደገና ለሦስተኛ እና ለመጨረሻ ምርመራ ቀጠሮ መያዟን ዋሽቼ አስረዳሁት:: ዶክተሩ ትንሽ አመነታና በጣም ስለለመንኩት በውጤቱ ስላለው ዝርዝር ነገረኝ:: የሰው ልጅ ሊሸከመው የማይችለውን ጭንቀት አሸክሞ ላከኝ::

የመጀመሪያው ዶክተሬ ባሌን አፈላልጐ የሕክምና መዝገቤን ሰርቄ መውጣቴን ነግሮት «በሽተኛዋ እራሷ ላይ የምትፈጥረው ሽብር የህክምና ክትትሏ ላይ ችግር ስለሚፈጥር ነው እኔ ያልነገርኳት» አለው::

ቅዱሱ ባሌ እንደለመደው ክጉኔ ቆሞ ሁኔታዬን በቁጥጥሩ ስር አዋለው::

«ሰሀር ለኔ ስትይ ሁሉን ነገር እንደምታደርጊ ቃል ገብተሻል ትዝ ይልሻል?»

«አዎን»

«በሽታሽን በትክክል ትጋፈጪለሽ:: እኔም ይኸው ከጐንሽ አለሁ:: ለችግራችን መፍትሄ አብረን እንፈልጋለን:: ኑሮአችንን ካሁኗ ደቂቃ ጀምረን ደስተኛ ለማድረግ እንጥራለን እሺ! እባክሽ አግዢኝ::»



ለሰሚር ስል ተመልሼ ለመጨረሻው ወሳኝ ምርመራ እራሴን አዘጋጀሁ:: ስካነር የተባለው የምርመራ መሳሪያ የመጨረሻ ተስፋዬ ነበር:: ረጅሙ ደረቅ አልጋ ላይ አስተኝተውኝ መሳሪያው ወደሚገኝበት ብርሃናማ ክፍል ለብቻዬ አንሸራተው ሲያስገቡኝ ከዚህ በፊት ከቶ ባልተማፀንኩት አይነት በፀሎቴ ተማፀንኩ::

«አቤት ይህ ሁሉ ስህተት ነው:: ጤነኛ ነሽ:: ስላስፈራራንሽ ይቅርታ አድርጊልን» ቢሉኝ ብዬም ተመኘሁ:: የሆነ ተአምር መቶ እንደነበርኩ ጤነኛ እንዲያደርገኝ ለመንኩ::

ስካነሩ ግን በጡቶቼ አንሰራርቶ የሚገኘውን ነቀርሳ በግልፅ አሳየ:: ስለነቀርሳዬ እርግጠኛ ሲሆን ዶክተሩ በቶሎ ለቀዶ ጥገና እንድዘጋጅና ስለበሽታዬ ከባሌ ጋር እያለሁ በግልፅ አስረዳኝ:: መላ አካላቴ ተንቀጠቀጠ:: አይኖቼ እናንስው ሊጠፉ እስኪደርሱ አነባሁ:: ባሌ አብሮኝ እንዲሆን ባለመፈለጌ ለብቻዬ የሆነ መኝታ አዘጋጀሁ:: ባሌም ሳይረብሸኝ ሁኔታው እስኪበርድልኝ እና የነቀርሳዬን እውነታማነት አዕምሮዬ እስኪቀበለው ጊዜ ሰጠኝ:: ለማልቀሱ ለማዘኑ እምላክን ለማማረሩ ድክም ብዬ እስክዝል ድረስ ደህና ጊዜ አገኘሁ:: ጮህኩ! ፈረጥኩ! አጨስኩ! የተቀየረ ነገር የለም:: ብቻዬን ሆኜ ረጅም መንገድ ተጓዝኩ:: ረጅሙ መንገድ አዲስ ሀሳብ አስተማረኝ::

በደረቴ የያዝኩትን በሽታ እንደያዝኩት ቁጭ ማለት ያለመፈለግ አዲስ ሀሳብ ውስጤ ሲያድግ ተሰማኝ።

ሚስኪኑ ሰሚርን ለምን አሰቃየዋለሁ ብዬ ባሌን የማኮራ ጠንካራ ሴት መሆን አለብኝ አልኩ።

እቤት ስገባ ጥሩ እራት አዘጋጅቼ ለስ ባለ ውሃ ተነከርኩና ተቆነጃጅቼ ሰሚርን ጠበቅኩት። ምንም አዲስ ነገር እንዳልተፈጠረ ሁሉ ተሳስቀን ጥሩ ለሊት አሳለፍን። ጠዋት ላይ ስለበሽታዬና ቀዶ-ጥገናዬ በርጋታ አወራን።

በሚቀጥለው ቀን ሆስፒታል አብረን ሄድን። የመረመረኝ ዶክተርም ለቀዶ-ጥገናው ብቸኛ ወሳኝ እኔው መሆኔን ነገረኝ። በነገሩ ለማሰብ ብዙ ጊዜ ባልወስድም እንደሚያዋጣኝ መከረኝ።

እኔ ግን ተስፋ በመቁረጥ «መሞቴ ላይቀር ለምን ጡቴን እቆረጣለሁ። ሳልቆረጥ ከነሙሉ አካሌ ብሞት እመርጣለሁ» አልኩ።

ሀኪሙ ለበሽታዬ የጥርስ ህመምን ምሳሌ ሰጠኝ። በጣም የሚጠዘጥዝሽን ጥርስ ብትነቅይው እፎይታን ታገኛለሽ። ይኸም እንደዛ ነው አለኝ። ከዚህ በፊት ታምሚው በማላውቀው መልኩ የሚያሳብድ ስቃይ በጡቴ ላይ ይሰፍራል። ያኔ አሁን በቀን አራት ጊዜ የምትወስጂው የስቃይ ማስታገሻ ክኒኖች ስቃይሽን መቆጣጠር ያቅታቸዋል። ያኔ ለእርዳታ ወደ ህክምና ስፍራ መሄድሽ አይቀርም። የዛን ጊዜ ለሀኪሙም ላንቺም አስቸጋሪ የሆነ ቀዶ-ጥገና ይጠብቃችኋል። ለበሽታው



በጣም እንዲያንሰራራ ዕድል ስለሰጠሽው የሚኖሩሽን ኣመታት በስቃይ እራስሽን በመርገም ታሳልፊያለሽ። ነለዚህ እንድንረዳሽ ብቸኛው አማራጭ የግራ ጡትሽን ኣርጦ ማውጣት ነው። ብሎ ተነተነልኝ።

ሰሚር በዶክተሩ ፊት እንባውን አፈሰሰ። ዶክተሩ ነእይኑ ሲገስፀውም አይቻለሁ።

«የኔ ማር! መፍትሄ ነው ያሉት የጡትሽን መቆረጥ ከሆነ እኔን የጡትሽ መቆረጥ አይቀይረኝም። ምንም ነገር ቢሆን በጣም እንደምወድሽ እወቂልኝ። እወድሻለሁ በጣም።» ብሎ ባሌ ጥብቅ አድርጐ አቀፈኝ።

አይኔን ጨፍኜ ለጡቴ መቆረጥ ፈጥኜ ተስማማሁ። ቀዶ-ጥገናውን በማላውቀው አገር ማድረጉን ባለመውደዴ በዚያው ሳምንት ሽርሽራችንን አቋርጠን ወደ ቤታችን መጣን።

የምርመራ ወረቀቱን የተቀበለኝ ሀኪም እላዩ ላይ ተቀባ ልዩ ነገር አለው። ልብ ያስከናል። በቀላሉ እንዳምነው አደረገኝ። ለቀዶ ጥገናው ስኬታማነት መጀመሪያ በሽተኛው ዶክተሩን መውደድ አለበት። ካልወደደው ወደ ሌላ ዶክተር ይሄድ ዘንድ ይመከራል። እኔ ግን የመጀመሪያውን ዶክተሬን ወድጀው አምኜዋለሁ። እድለኛ ነኝ።

እንደሚሉት ከሆነ ጡቶቼን በየቀኑ መቆጣጠር ይገባኝ ነበር። ይኸን ባለማድረጌ ነቀርሳው ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ጡቶቼን ጉድቶአቸዋል።

እየሾለ ለመጣው ጡቴ ደስተኛ ነበርኩ:: ስፖርት ቤት እየሄድኩ ስፖርት እሠራ ስለነበር እስፖርቱ የሰጠኝ ውበት እንደሆነ ነበር የገባኝ:: በክንዴ ላይ ለሚወጥረኝ ህመም ቁብ መስጠት አልፈለግሁም:: ወጣትነቴን እስከመጨረሻው ብቻዬን እየቦረቅሁ አፍላ ጉልበቴን በስፖርት መገምገም በጣም ያስደስተኝ ነበር:: ልጅ ውለጅልኝ እያለ የሚለምነኝንም ባሌን ቀጠሮ እሰጠዋለሁ:: ሰላሳ ሁለት ወይ ሦስት ሲሞላኝ እወልድልሀለሁ እያልኩ እስከዛ ግን ልጁ አንተ ነህ ብዬ ጥያቄውን እንዲረሳ እየሳምኩ አባብለው ነበር::

የሚገርመው ነገር ስለዚህ በሽታ የተፃፈውን የዶክተሮች አባባል ሳነብ ከሰላሳ ዓመቷ በፊት ልጅ ወልዳ ያጠባች ሴት ለዚህ በሽታ የመጋለጧ ዕድል የቀነሰ መሆኑ ነው:: ቆጨኝ:: ጥሩ ዕድል አመለጠኝ:: ቢያንስ ባሁኑ ወቅት ፀጉሩን እያሻሽሁ የማስተኛው ህፃን ይኖረኝ ነበር:: ካሁን በኋላ ልጅ የመውለዱ ነገር የማይታሰብ ነው:: ፈፅሞ::

ዶክተሬን ስለበሽታው መንስኤ ጠየቅሁት:: ለበሽታው መንስኤ ከግምት በቀር ትክክለኛ መልስ አልተገኘለትም:: ብቻ ግምቶቹ ወደእውነተኛው መንስኤ የቀረቡ ዓይነት ናቸው:: ጭንቀት የሚፈጥረው የሰውነት መኮማተርም ይህን በሽታ ያመጣ ይሆናል ተብሎ ተገምቶአል:: አንቺ በምን መጣብኝ ብለሽ እራስሽን አታስጨንቂ ይኼ መሺአትላህ /የአምላክ ትዕዛዝ/ ነው



ብሎ ነገረኝ:: እኔ ግን የእናቴ ነቀርሳ ተከትሎኛል ባይ ነኝ::

ሐኪሜ አማራጭ የቀዶ-ጥገና ዘዴዎችን አንድ በአንድ ዘረዘረልኝ:: እኔም ጡንቻዎችን በመጠቀም የሚካሄደውን ዘዴ መረጥኩ:: ምክንያቱም ይህ ዘዴ የሆድ ስብን ከመጠቀሙ ዘዴ ያጠረ ቀዶ-ጥገና ስለሆነ ነው::

ስለቀዶ-ጥገናው የማስታውሰው ክንውን ወይም ህመም የለም:: ከዛ በኋላ ግን ከታሸገው ግራ ጡቴ ይልቅ ግራ ክንዴን ቀፍድዶ ያያዘ ሀይለኛ ህመም ተሰማኝ:: ሀኪሜም ሙሉ ጡቴንና ባካባቢው ያሉትን ስቦች ሙሉ ለሙሉ ማስወገዱን ነገረኝ:: ፋሻው ሲፈታ ስለሚኖረው ጎድጓዳ ቦታ እንደውም በቀዳዳው ሳንባዬን ወይም ልቤን ስመለከት ብዙ ጊዜ አለምኩ:: በሕልሜ ያየሁትን በውኔ ላለመድገም ያ ፋሻ ለዘለዓለም እላዬ ላይ ተጠምጥሞ እንዲቀር ተመኘሁ:: እንደኔ ላለች ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ስለሰውነቷ ቅርፅ ለምትጨነቅ ሴት የጡት መቆረጥ ምን ዓይነት የቀን አስፈሪ ቅዠት እንደሆነ መገመት አያዳግትም:: እጄን ወይም አንድ እግሬን ባጣ ከሚሰማኝ ስሜት የበለጠ ውስጤ ሲቆስል ተሰማኝ:: ባዶ የሆንኩ መሰለኝ:: ሴትነቴም ትርጉም እንዳጣ ይገባኛል::

የቀዶ-ጥገናውን ጨርሼ በቀላሉ አልተገላገልኩም:: ራዲዮቴራፒ በየቀኑ ለተወሰነ ጊዜ ማድረግ ነበረብኝ:: ይህ የህክምና ክትትል ውስጤን እየረበሸው በማስመለስ ብዙ

ተቸግሬ ነበር። ከቤቴ እስከሆስፒታሉ ያለውን መንገድ ለማየት በጣም አስጠልቶኝ የግዴን ደጋገምኩት።

ነገሮች ሁሉ እንደበፊቱ አልነበሩም። እቤቴ ስገባ ሰሚር በጣም የሚጠላውን የቻይናዎችን ቅመማ ቅመም ለነቀርሳ የሚሰጠውን መድኃኒት/ሳይድኢፌክት/ የሚጉዳ መልኩን ይቀንሳል የሚለውን የሀኪሞቹን ምክር ተቀብሎ ኩሽናዬን በቻይናዎቹ ቅመም ሞልቶልኝ ወጥ ቤቱ በቅመማ ቅመሞች አስቀያሚ ሽታ ታምቆአል። እንኳን ምግቤ ውስጥ ገብቶ ይቅርና ሽታው አንገሸገሸኝ። ሰሚር ግን የበሽታሽን ውጊያ የምንጀምረው ከዚሁ ነው ብሎ በቻይና ቅመም የተንተከተከ ሾርባ አስዋጠኝ። ሰሚር እቤት እስክመጣ በካሮት ጭማቂ አጨማመቅ ጀምሮ ሁሉን ነገር ተምሮ ቆየኝ።

ጠዋት ላይ በካሮች ጭማቂ ብቅ ይላል። እራሱ ጨምቆ እራሱ ቁርስ አዘገጅቶልኝ ሠራተኞችንን እንኳን ሳያስቸግር . . . መልአክ ነው።

«አልበዛም?! በጣም አቀበጥከኝ። ስለታመምኩ ነው? እንክብካቤህ . . .»

«እንደምንከባከብሽ ዛሬ ገና ማወቅሽ ያሳዝናል። እኔ ካየሁሽ ጀምሮ ነው እንክብካቤ የጀመርኩት። አንቺ ግን ያየሽው ዛሬ ነው። በፊት በብዙ ነገር በጣም ስለምትጠመጂ የኔን ድርጊት አታጠኚም።»

«ይቅርታ አድርግልኝ ሰሚር የማላይ እውር ነበርኩ።»



እውነቱን ለመናገር እንዴት ይንከባከበኝ እንደነበር በደንብ አውቅ ነበር። ብቻ ባሌ እንደዛ የሚሆንልኝ ለሚያምረው ቅርጼ መልኬ ቁመናዬ ይመስለኝ ስለነበር ባጭሩ ኮራ ብዬ «ይገባኛል!» ብዬ ወስጄው ነው።

ከምወደው እስፖርት በስጋ ከሚሰራው ምግቤ ተለይቼ በምትኩ ነጭ ሽንኩርት። የምጠላውን ነጭ በቁሙ እውጣለሁ። ጠረኔ፣ ትንፋሼ ወይ የቻይናዎቹን ቅመም ወይ ነጭ ሽንኩርት ወይ መድኃኒቶቼን ብሎ ምንም ሳሙናና ውሃ ሳይቀይረው የራሴው ሆኖአል።

የሴለሪይ ጭማቂ እና የሲትረስ ፍራፍሬዎችም የግዴታ መጠጦቼ ናቸው። የካሮቱን ጭማቂ ጨምሮ። የሰሚር ቤተሰቦች ሊጠይቁኝ መጡ። አይናቸው ላይ «ኡፍ ልንገላገልሽ ነው። ቶሎ በሞትሽ የልጃችንን ሕይወት ገሀነብ አደረግሽው ለሞትሽ እንፀልያለን።» እንደሚሉኝ አነበብኩ። እኔም ተመልሰው እንዳይመጡብኝ በአስተያየቴ ቀጣኋቸው . . . ሰሚር ሳያይ። በርግጥ ደረቴ ላይ የተፈጠረውን ጉደሎ በጭንቀት ለሚቃኙት አንዳንድ አዛኝ ጓደኞቼ አስቀይሜ መለየት ባይኖርብኝም

«ስታሳዝን መሞቷ ነው ቻው አፈሩ ይቅለልልሽ» የሚለውን አስተያየታቸውን ልሸከመው አልቻልኩም። «አይናችሁን ማየት አልፈልግም አትምጡብኝ» ብዬ ከቤቴ ባስወጣቸውም እንደማይጠሉኝ እርግጠኛ ነበርኩ።

አንዷ ጓደኛዬ አስቀያሚ ፊት ያለው ትልቅ የድብ አሻንጉሊት አመጣችልኝና ተሰናብታኝ ከመሄዷ በፊት

«እንደኔ ከሆንሽ በጣም ስትበሳጪ ይህን ድብ እየሰደብሽ ደብድቢው። እመኚኝ ከዛ በኋላ ውስጥሽ እፎይ ይላል። ይህን የሚመስል ድብ እቤቴ አለኝ የንዴቴ ማብረጃ ነው። ሞክሪው!» አለችኝ።

በእውነቱ ትልቅ እርዳታ ነው።

ፋሻዬ የተፈታልኝ ዕለት ከትልቁ መስታወት ፊት ቆሜ ለማየው ነገር ለመዘጋጀት ከአስር ደቂቃ በላይ ፈጀብኝ። ትንፋሼን ሰብስቤ የቀሚሴን አዝራር መፍታት ጀመርኩ። ፈታሁ። አይኔን ጨፈንኩ። እንደምንም ስገልጠው ያየሁት የራሴን ገላ መሆኑን ተጠራጠርኩ። ጡቶቼን አቀለጥኩ። እራሴን መቆጣጠር ተሰኖኝ መስታወት ላይ የማየውን ምስሌን ለማጥፋት ያገኘሁትን ነገር ሁሉ መስታወቱ ላይ ወረወርኩ። ቀረብ ብዬ የተሰነጣጠቀውን መስታወት በቡጢ ሳጉነው እንክሽክሹ ወጣ።

ሰሚር ድምፁን ሰምቶ ደረሰልኝ። የሚንዘፈዘፈውን ሰውነቴን እቅፍ አድርጐ በጆሮዬ፦

«አይዞሽ ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል» አለኝ። የመስታወቱ ስባሪ የቆረጠውን እጄን አከመልኝ።

በነጋታው ተመሳሳይ ትልቅ መስታወት አስመጥቶ ነይ ብሎ ከመስታወቱ ፊት አቆመኝ። ያደረግሁትን የመኝታ ቀሚስ እያወለቀ አንገቴን እየሳመኝ



«ተቀበይ! ይህ አዲሱ ሰውነትሽ ነው ተቀበይው!» ብሎ አንሾካሾከልኝ።

እረጋ ብዬ የተጐዳ ደረቴን አየሁ። ሰሚር እንባዬን ጠረገ። እጄን ይዞ ደረቴን አብረን ዳበስን። መጥፎ ስሜቴ ሲቀንስ ገላዬን ባለበት ሁኔታ ስቀበለው ተሰማኝ። ሰሚር ተአምረኛ ባል ሆኗል።

ክንዴን ለማንቀሳቀሱ ጊዜ ፈጅቶብኝ ሰሚር እንደሕፃን ልጅ እያቀማጠለ ፀጉሬን ያበጥርልኝ ነበር። ወደመዳኑ ስደርስ አንድ ቀን ሰሚር እንደለመደው እያሳሳቀ ሲያበጥር ድንገት ተንተባተበና ማበጠሪያውን ወደኋላው ሲደብቅ አየሁ። ምክንያቱ በትክክል ባይገባኝም ልጫነው አልፈለግኩም። የችኩል ፈገግታ ፈገግ ብሎልኝ ወደመታጠቢያ ቤት ሲሄድ ቀስ ብዬ በጣቶቼ እየተራመድኩ ተደብቄ አየሁት። የሽንት ቤቱን ውሃ ለቆ ተመልሶ መጣ።

«ሁሌ እኔው እንዳበጥርልሽ ትፈቅጂልኛለሽ?»

«ተገኝተህ ነው»

«አንቺን አላምንሽም የኔ የሆነውን ፀጉርሽን እኔ ሳልኖር ታበጥሪብኛለሽ ስለዚህ ማበጠሪያሽን ሁሉ መደበቅ አለብኝ» ብሎ አሳቀኝ።

እኔን ሊያስደስተኝ የማይፈጥረው ሰበብ የለም አልኩ። ሸሚዙን ወደቆሻሻ ልብስ ማጠራቀሚያ ስወስድ ማበጠሪያዬን አገኘሁ። ቀልዱን አስቤ እየሳቅኩ ባኞ ቤት

ገብቼ ከቀዶ-ጥገናው ቀኔ ጀምሮ አበጥሬው የማላውቀውን ፀጉሬን ማበጠር ጀመርኩ:: ፀጉሬን በማበጠሩ ይህን ያህል ደስታ ተሰምቶኝ አያውቅም:: እያንዳንዱ የአካሌ ክፍል ውድ መሆኑን በበሽታዬ አውቄዋለሁ:: በመቀጨሪያዬ ጊዜ ይህንን ማወቄ ያሳዝናል:: ረጅሙ ፀጉሬን በአንገቴ ወደኋላ መታ አድርጌ ከፊት ያለውን ፀጉሬን ላስተካክል ቀና ስል እጅግ ብዙ ፀጉሬ ማበጠሪያውን ሞልቶ አየሁት:: ሰሚር ያስደነገጠው እና ማበጠሪያዬን ያስደበቀውን ምክንያት የፀጉሬ ከልክ በላይ መነቀል መሆኑ ገባኝ:: እኔንም ክው አድርጐ አደረቀኝ:: የራሰ ቅሌ ብቻውን የቀረ መሰለኝ:: «ለምን ይህ ሁላ ይደርስብኛል ምን ክፉ ሰርቼ ነው» ብዬ ወደሰማይ ሳንጋጥጥ ደካማ አይኖቼ እንባ አፈሰሱ:: በየቀኑ ሰውነቴ ላይ አዲስ ለውጥ እያለሁ:: ነቀርሳዬ ወጣትነቴን ያለጊዜው እንደሚወስድ ሊያስታውቀኝ አይኖቼ ስር፣ ጉንና ጉን በኔ እድሜ ከቶ የማይከሰተውን መስመር አጋደመልኝ:: የራሱ እንደሚያደርገኝ እያወቅኩ ዕድሜዬን እንደሚቆርጠው እያወቅኩ ፊቴ ላይ የተመሰመሩትን ሽብሽብ መስመሮች እጅግ ከብደው ታዩኝ::

አይኔ ስር ያለውን አዲስ ሽብሽብ ቆዳዬን ልለጥጥ በጣቶቼ ስታገል ሰሚር እጄን ከፊቴ አነሳና በፈገግታ እያየኝ «ጥሩ ክሬም መጠቀም ትችያለሽ ለምኑ ነው ሀዘኑ!» ባሌ ጣፋጭ ነገር ነው:: ተሰብሮ ብትንትን ያለውን ልቤን መጠገኛ ቃላት አያጣም::



«እኔ ጥሩ ክሬም አልፈልግም እኔ የምፈልገው. . .» ተናነቀኝ:: «ይገባኛል ሳሀር ይገባኛል ብቻ አንቺ በአሳሁ ተመኪ ነገ የሚከሰተውን ማን ያውቃል?!»

«መድኃኒት ይገኛል ብለህ ታስባለህ?»

«ይሆናል::» ፊቱ ላይ ግን «አይገኝም» የሚል መልስ ይነበባል::

ከእርሱ ጥንካሬን አገኝ ዘንድ አጥብቆ እንዲያቅፈኝ መጠየቅ መፍትሔ ሆኖኛል::

ሰሚርም የቤተሰቦቹን 'ሌላ አግባ' ጉትጉታን የኔን ስቃይ ባንድ ላይ አጣምሮ በውስጡ ይዞታል:: ፊቱ ግን ምንም ችግር እንዳልተጋፈጠ ሁሉ እኔ ፊት የፈካ ነው::

ቤተሰቦቹ የመጀመሪያ መነሻዬ ክርስቲያን ስለሆንና የሌላ አገር ሰው ስለሆንኩ አልወደዱኝም:: የእኔ ወደ እስልምና መቀየር ብቻ በቂ አልመሰላቸውም:: ቢችሉ እንዳለ ወደ ሊባኖስ ሄደው ዘርማንዘሬን ቢያሰልሙ ደስታቸውን አይችሉትም:: የኔና የሰሚር ፍቅር ግን ሊበገር ያልቻለ በጣም ጠንካራ ነበር:: ሰሚር ከልቡ ወደደኝ እኔም ከስሜ ጀምሮ ሀይማኖቴን ሁሉን ነገሬን እንዲቀይር ፈቀድኩለት:: አዲስ ስም አወጣልኝ:: እኔም ያወጣልኝን ስም አመለኩ:: ደጋግሜ ሰሀር እያልኩ ስሜን ተለማመድኩ:: ሊባኖስ መጥቶ እያለ ነበር የተዋወቅነው:: በፍቅሩ በጣም ሰምጬ ገባሁ:: የሚለው ነገር ሁላ ትክክል መሆኑን ልቤ አመነ:: ሀይማኖቴን ከመለወጤ በፊት ጥሩ ጥሩ አሳማኝ የቁርአን ታሪኮችን ያለመታከት ይነግረኝ

ነበር። ከሁሉም ከሁሉም የመካን ዘምዘም /ጠበል/ ታሪክ ጭንቅላቴን ቀይሶበታል። ወስዶም አሳየኝ።

በዚያ ድብን ባለ ደረቅ ስሀራ ቦታ ላይ የመነጨው ጠበላዊ ምንጭ በእስላሞች የተለየ ታሪክ አለው። አጀማመሩ እንደ ክርስቲያኑ አብርሃምና ሳራን ታሪክ ያወሳል።

ሳራ ኢብራሂምን ከገረዱ እንዲወልድ ከፈቀደችለት በኋላ ገረዷን ከሕፃኑ እስማኤል ጋር ስታያት ትቀናና አርቀህ ውሰዳቸው ትለዋለች. . . ኢብራሂምን። አላህ ለኢብራሂም ልጁን ከነእናቱ ከሳራ ቦታ አርቆ ስሀራማው ቦታ ትቶት እንዲሄድ ይነግረዋል። ኢብራም ሁሉን ነገር በአላህ ትቶ ጭው ባለ በረሀ ሕፃን ልጁን ከነእናቱ ይተወዋል። ቦታው ውሃ የለበት የሚቀመስ የለበት። እናትየው ለልጇ ውሃ ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ስትል ሕፃኑ እስማኤል በእግሮቹ ጫር ጫር ሲያደርግ የጠራ ውሃ ከእግሮቹ ስር ፍልቅ ፍልቅ ይላል። ይህ ቦታ ነው እንግዲህ ዘምዘም /ጠበል ውሃ/ በመካ እስካሁን የሚፈሰው። እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ አብሮኝ የኖረውን ክርስቲያንነቴን ባይ ባይ ብዬ ሰሚርን ተከትዬ ወደአገሩ ስመጣ ያኔ ከዘርማንዘሮቼ ጋር ተቆራረጥኩ። በድሮ ስሜም ሆነ በሰሀር ሊጠሩኝ ሊያስቡኝ ሊያዩኝ አይፈልጉም። ረስተውኛል። አባቴም ልጄ አይደለችም ብሎ ቆርጦ ፊቱን አዙሮብኛል። ያን ሁሉ ኪሳራዬን አብቃቅቶ የሚተርፈኝ ልዩ ዓለም ውስጥ ከሰሚር ጋር ገብቼ እኔም በበኩሌ ረስቼአቸዋለሁ። የሰሚር ቤተሰቦችም



ሰሚርን ከኔ ጋር ትተው ቢረሱት ደስታውን አልችልም። በተለይ ከታመምኩ በኋላ። የሚደወለውን ስልካቸውን እንኳን ለመመለስ ተሳቆ ሞቷል።

አንዴ እህቱ ስትደውል በሌላኛው ስልክ ሳዳምጥ «እኔ የምትወዳትን ሚስትህን ተዋት አልልህም። የምትወልድልህን ሌላ ሴት እንድታገባ ሕጉ ይፈቅድልሀል እባክህ አግባ። ስለ እናትና አባቴ አስብ። ስለአንተ መጉዳት በጣም ይሰማናል። ከበሽተኛ ሴት ጋር እራስህን አፍነህ. . .» ስትለው ሰማሁ። እውነቷን ነው አልኩ የሰሚር ጉዳት ተሰማኝ። እኔስ አንዴ ፈርዶብኛል የሉን ሕይወት መበከሌ ግን ራስወዳድነት ነው ብዬ ሳናግረው አሰብኩ። እርሱ ግን ሕይወቱን ከሕይወቴ ጋር ጠፍሮ አስሮአል።

ማንኛውንም ዓይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒን የግድ ማቋረጥ ስላለብኝ ዶክተሩ ያቀረበለትን ምርጫ ያለምንም ማወላወል ተቀብሎታል። በሁለታችን ያለው ግንኙነት እንዲቀጥል ለወንዶች የሚሰጠውን የወሊድ መቆጣጠሪያ ለመውሰድ ተስማምቶ ወስዶአል። ይኸን የገዛ ዶክተሬ በአድንቆት ነው የነገረኝ።

«እሱን የመሰለ ወንድ በአለም ላይ አጋጥሞኝ አያውቅም» ብሎ።

የእህቱን ስልክ እንደዘጋ የእህቱን ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ መስማማቴን ስነግረው «አንቺ ሕይወቴ ነሽ ሙቼ ነው ያ የሚገባሽ?!» ብሎ በጣም ሳመኝ።

የዛኑ እለት የስልክ ክሩን አስቆረጠ::

የመጀመሪያውን ቀዶ-ጥገናዬን ባደረግኩ በአሥራ ስምንተኛው ወር በተደረገልኝ ምርመራ በቀኙ ጡቴ ላይ ተመሳሳይ የነቀርሳ ሙሽራ መብቀሉን አረዱኝ:: እርሱ ብቻ ሳይበቃ በቀኝ ክንዴ ስርም ይኸው ሙሽራ ቁጭ ብሎአል:: በጉላ ድምፅ «አምላኬ ሆይ ሳታሰቃይ ውሰደኝ አካሌ ተቆራርጦ ማለቁ ነው» ብዬ ጮኽኩ::

ሰሚር ይህን ዜና እንደበፊቱ እረጋ ብዬ እንድቀበለው አልገፋፋኝም:: በፊት ለፊቴ ጭንቅላቱን ይዞ በድምፅ አለቀሰ:: ከዛ በኋላ በጣም ተሰወጠ:: እንኳን እኔን ሊያፅናና ለራሱም አፅናኝ ፈለገ:: «ነገሩ እኮ በበፊቱ ስቃይ ብቻ ያለፈልሽ መስሎኝ ነበር:: ስቃይሽ እያሰቃየኝ ታግሼ ስቃዬን በውስጤ ይዤ ፈገግ እል ነበር:: አሁን ግን ያን ማድረግ የምችል አይመስለኝም:: ስሀር ይህ ሁላ ይህ ልስልስ ገላሽ ላይ?!» ብሎ ከሚገባው በላይ አዘነልኝ::

የመጨረሻ ያየሁት ቀንም ሀዘንተኛ ፊቱን አልደበቀኝም:: ትክዝ እንዳለ ነበር የወጣው:: የመኪና አደጋው የእኔን ሕይወት ቢወስድ ምን ነበረበት. . . የሞቱ ብቸኛ ተጠያቂ እኔ ነኝ:: ይህ ካንሰሬ ያመጣው ጣጣ የወደፊት ሕይወቴን ብቻ ሳይሆን በህይወት እያለሁም ህይወቴን ሙልጭ አድርጐ ወሰደ:: ምንም ጠንክሬ ብገኝም ሞቱ ሀይለኛ ሆኖ ጣለኝ:: የባሌንም ጭምር ዕድሜ ቀጨ::



የሰሚር እናት ለገላጋይ አስቸግራ ለሀዘን በተሰበሰቡት ሴቶች መሀል «ገፊ ነሽ ገፊ! ልጀን ገፋሼ ብላ በሰሚር ሞት ተጠያቂ አደረገችኝ:: አንገቴን ሰብሬ

«እውነትሽን ነው እኔ ነኝ የገደልኩት ይኸው ከፊትሽ አለሁ ቅጪኝ?! መቼም አምላክ ሰሚርን ወስዶ ከቀጣኝ የባሰ ቅጣት በዚህ ምድር የለም:: ሰሚር ላንቺ ልጅሽ ነው:: ለኔ ግን ምን ልበል . . . ሁሉም ነገር ነበር::» ብዬ መለስኩላት::

ሰሚር እንዲያቅፈኝ እንዲደብቀኝ ተመኘሁ በዚያች ደቂቃ:: ዞር ብል ዞር ብል ሰሚር የለም:: ጉሮሮዬን እየመረረኝ እየከረከረኝ ተንሰቀሰቅኩ:: በዚያችው ሳምንት እንባዬን አደረቅኩ::

ለሁለተኛው ቀዶ-ጥገናዬ አጠንክሮ ያዘጋጀኝ አንድ ጉዳይ ነበር:: «የልጃችን ሚስት ሞቷን የምትጠባበቅ በሽተኛ መድኃኒት በሌለው የጡት ነቀርሳ የምትሰቃይ ሴት ስለሆነች የሰሚር ንብረት ለእኛ ይገባናል:: ለሚስቱ የሚደረገውን ማንኛውም የህክምና ወጪ በቅርብ ሆነን እንከታተልላታለን::» የሚለውን የንብረት ይገባኛል ጥያቄያቸው ነበር ለሁለተኛ ጊዜ ያዘጋጀኝ:: ምክንያታቸው ዳኛውን አናደታል:: ንብረቱ የሚስቱ ነው እርሷ የፈለገችውን የማድረግ ሙሉ መብት አላት ብሎ ምንም እድል ሳይሰጣቸው የሰሚር ብቸኛ ወራሽ አደረገኝ:: በርግጥ እኔ ይህን ሁላ ንብረት ባለው አጭር ጊዜዬ ምንም ልጠቀምበት አልችልም:: ለራሴ አብዛኛውን

ጊዜዬን የማሳልፈው በሆስፒታል ሆኗል። ግን የሰሚር ቤተሰቦች ያደረጉት ነገር በጣም ስላናደደኝ ከሰሚር ንብረት አንዲት ሚስማር እንኳን ለእነሱ ትቼላቸው አልሞትም ብዬ ቀዶ-ጥገናዬን አፋጠንኩ። በሰሚር መሞት ቅስሜ ተሰብሮ ፈጥኜ እንድከተለው የሁለተኛ ቀዶ-ጥገና ችላ የማለት ሀሳብ ነበረኝ። ስቃዩንም የምወደው መስሎኝ ነበር። አሁን ግን እነዚህን ጨካኝ ሰዎች መቅጣት አለብኝ ብዬ የንብረቱን ጉዳይ ለማስተካከል ስል ብቻ መኖር ፈለግኩ።

ከባሌ ሞት በኋላ በሽታዬን አስታኮ ሊጐዳኝ ወይ ሊጠቀምብኝ የመጣን ሰው በበቂ ሁኔታ የመበቀል አዲስ ፍላጐት አደረብኝ።»

የሁለተኛው ጡቴ ሲቆረጥ ከበፊቱ የባሰ ስቃይ ነበረው። ሦስተኛው ሙሽራም በቀኝ ክንዴ አውጡኝ እያለ አሞጥሙጧል።

ለሶስት ወራት ያህል በየቀኑ ለሀያ ደቂቃ ያህል በራዲዮቴራፒ ስር ደረቴን ሰጥቼ እተኛለሁ። ልብስ ማውለቅ ልብስ መልበስ እራሱ ለጉዳተኛ ክንዶቼ አሰልቺ ነበር። ያን ሁላ ጥርሴን ነክሼ ቻል አደረግኩ።

በፊት የቀረፅኳቸውን የደስታ ቅርፃ ቅርፆቼን ሰባብሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የነቀርሳን ምስል ያዘሉ ሁለቱን ሀውልቶች ቀርጬ ከበሬ በራፍ ግራና ቀኙን አቆምኩ። አንዱ የባሌ ህይወት ላይ የሆነ የውስጤ በሽታ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ እኔው ውስጥ አልወጣም ብሎ ለብዙ



መድኃኒቶችና ቢላዎች አልበገር ብሎ እንድልሻለሁ የሚለኝን ጭራቅ መሳይ ነቀርሳን ይወክላሉ። ባለ ብዙ እጆቹ ይህ ሀውልት ባሌን አዘናግቶ የመኪና አደጋ ላይ የዳረገውን ስራስራሙን ሙሽራ በትክክል ይመስላል።

ይህን በሽታ ከያዝኩበት ጊዜ አንስቶ በየአራት ሰዓቱ የምወስደው የስቃይ ማስታገሻ ቀለቤ ሆኖአል።

ሁለተኛውን ባሌን ረገብን እዚያው ሆስፒታል ነው ያወቅኩት። የሰሚርን ቤተሰቦች የማደማበት ብትር እየፈለግኩ ነበር። ወጣቱን ጥሩ ማድሚያ ባል ወዲያውኑ አግብቼ እቤቴ ይዤው ገባሁ። ጋብቻችንን የፈፀምነው እዚያው ሆስፒታል ነበር። የሰርጉ እለት ዶክተሬ ነርሴ እና የማላውቃቸው ምስክሮች «መአዙን /በእስላም ሕግ የሚያስተሳስር የመስጊድ ተወካይ/ እና ሙሽራው እኔ ብቻ ሆነን በብርቱካን ጭማቂ ደገስን።

ለነርሴ ሁሉን ነገር እነግራት ነበር። የዚህን ጋብቻ ዋና ምክንያት የምታውቀው እሷ ብቻ ነበረች። የሰሚርን ንብረት ለዚህ ወጣት ትቼለት ብሞት ዕድቅም ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር።

ምን ያረጋል! ረገብ አዲሱ ባሌ ሊያታልለኝ፣ ታሪኬን ከነርሷ ሚስቱ ሰምቶ በኔ ላይ ሻጥር ተማክረው፣ ኮንትራት ጋብቻ ከኔ ጋር ለመፈፀም ሚስትየው የገዛ ነርሴ ስቃዬን ሕመሜን ያየችው ሴት ፈቅዳለት መሆኑን ደረስኩበት። ሁለቱንም ልቀጣ አሰብኩ። እርሷን ባሏን በማታስበው መንገድ ነጥቄ የራሴ ብቻ ላደርገው። እርሱን

ደግሞ ገንዘቤን በማይወደው መንገድ ልግተው. . . ይህንንም እንዳይ አምላኬን እድሜ ጠየቅኩ:: ለነርሴም ሆነ ለረገብ ባልና ሚስት መሆናቸውን ማወቄን አላስታወቅኳቸውም:: ሲመስሉ እየሳቅሁ ፊልማቸውን አደነቅሁ:: የፊልሙ መጨረሻ የኔ ተራ እንደሚሆን ሳስብ ፈነደቅሁ:: ሀውልቶቼን ከመቅረፅ በኋላ የሚተርፈኝን ሰዓታት ረገብን በመበቀል አሳልፋለሁ ብዬ ወሰንኩ::

በጫጉላ ጊዜአችን ቡና እያፈላሁለት በውድ ዋጋ የገዛሁለትን ስጦታ አደንዛዡን ዕፅ ከስኳር ጋር አማስዬ አጠጣዋለሁ:: እርሱም ቡናዬን እጅግ እየወደደው መጣ:: ሱስ እንደሆነበት ሳውቅ ከለከልኩት:: ለመነኝ:: ሚስቱን በፊት ለፊቴ እንዲፈታ አዘዝኩት:: ትዕዛዜን ያለማወላወል ፈፀመ:: ነርሴ የምትወደው የአምስት ዓመት ባሏን አጣች:: ብልጣ ብልጥ ባሏም ከቀን ወደ ቀን እየተጃጃለ ሰውነቱ እያለቀ እግሬ ስር እንደውሻ ረገጥኩት:: የማሽትተው ሀሺሽ የትም እንዳይንቀሳቀስ አደረገው:: በቀሌን ጨረስኩ ብሞት ግድ የለኝም::

⁂ ⁂ ⁂ ⁂ ⁂ ⁂

የሚስጥሩ ማስታወሻ ደብተር ጉዳይ ከግብፃዊቷ እሙ-ሰዒድ ጋር አቃቃረን:: ከዚያች ሴት ጋር ልቃቃር ወይስ ልፋቀር የቱን መምረጥ እንዳለብኝ አላውቅም:: የሆቴል ሠራተኛው ባሏ ሥራ እንዲያፈላልግልኝ ስል



ልጣላት አልፈልግም:: ግን ደግሞ በነፃ እያሳሳቀች በምታሰራኝ ሰበብ እቤቴ ስገባ እራሴን መስታወቱ ላይ ሳይ ሞኛ ሞኝ ምስል ስለማይ እበሳጫለሁ::

እራሴን መስታወት ላይ ሳየው የተለየየ ይሆንብኛል:: ይህ ሁኔታ ሌሎች ላይ ደርሶ ነግረውኝ ስለማያውቁ ነው መሰለኝ እኔ ላይ ብቻ ያለ ልዩ ልማድ አድርጌ እቆጥረዋለሁ:: እሙ-ሰዒድ አጃጅላኝ ልብሷን ሙልጭ አድርጌ አጥቤላት እቤቴ ገብቼ ፊቴን በመስታወት ላይ ለህጪ የተዝረከረከ ጅላጅሏ እኔነቴን አያለሁ:: አብዛኛው ጊዜ ግን ጥንካሬዬንና በራስ መተማመኔን ማየቴ ለስደቱ ምስቅልቅል ህይወቴ ኃይልን ይሰጠኛል::

ታዲያ እሙ-ሰዒድ የደብተሩን ዝርዝር ትርጉም ሰለሰጠችኝ ብዙ አስባበት ለእመቤቱ እንደምትናገርብኝ አስፈራርታ የወር ድፍን ደሞዜን ደፍራ ጠየቀችኝ:: ይመስለኛል ተመሳሰለብኝ ብላ የምታማርረውን ህይወቷን በኔ ደሞዝ ለመቀየር የወሰነች ትመስላለች::

ሞቷን እየተጠባበቀች ያለችው እመቤቴ የጠቀሰችው አረፍተ ነገር ትዝ አለኝ:: «ከባሌ ሞት በኋላ በሽታዬን አስታኮ ሊጉዳኝ ወይ ሊጠቀምብኝ የመጣን ሰው በበቂ ሁኔታ የመበቀል ልዩ ፍላጐት አደረብኝ» የሚለው ታዲያ ሚስጥሯን ያለፍቃዷ ሰርስሬ አውቄ ሌሎቹንም አሳውቄ . . . እሙ-ሰዒድ ከነገረቻች ምኔ ሊተርፍ ነው በሰው አገር ብዬ ፈራሁ::

የግብፃዊቷን ፋክራ ለማክሸፍ ተነክልኩ:: ለእረፍቴ ስወጣ ተዘጋጅቼ ግብፃዊቷ ቤት ሄድኩና

«አንቺ ስለተረጉምሽልኝ ደብተር ለሴትየዋ ልትነግሪ ክወሰንሽ እኔም ለእመቤቴ የምለው አለኝ::»

የቀልድ ሳቅ ሳቀችና በርከክ ብለሽ «ሰም ሂኒ . . . ሰም ሂኒ» /ይቅር በይኝ/ ብለሽ ልታለቅሺ . . . ያ አይሆንም . . . የምትምርሽ ይመስልሻል? ከማረችሽ እንኳን ያለ ደሞዝ ከሥራ ታባርርሻለች ገባሽ?» አለችኝ::

መቼም ልነግራት ያሰብኩትን የተነከልኩላትን ብትሰማ ከሳቋ ጋብ ብቻ ሳይሆን . . . ባሏን ምን ያህል እንደምትፈራው አውቃለሁ:: ፍርሀቷ የመነጨው እርሱ እየሠራ ስለሚያበላት ስለሚያለብሳት የሚፈጠረባት ተፅእኖ እንደሆነ እገምታለሁ::

«ትዝ ይልሻል እህና አፍሪካ አኽዋት /እኛ አፍሪካ ወንድማማቾች ነን ስትይኝ/?»

«ማ እሌሽ /ግድ የለም/ ይቅርታ አድርጊልኝ» ለስለስ አለችና እንደገና የወር ደሞዝ ጥያቄ ላይ ከረረች::

«እንግዲያውስ!» አልኳት «ያን ደብተር እንዳመጣ የላከኝ የሆቴል ሠራተኛ ባልሽ እንደሆነ ዋሽቼ ብነግራትስ? እ! ምን . . . ትል . . . ይ-መ-ስልሻል?!»

ክው አለች ከቤቷ እንድወጣ በትህትና ነገረችኝ:: ነገሩን እንርሳው ብላ እራሷው ጠየቀችኝ:: ፊቷ ያስቃል:: እቤቴ እንደገባሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዚያች ግብፅ ቤት



ስመጣ መስታወቴ ላይ የማየው ፊቴ ተቀይሮ ቆየኝ:: ፍርስ እስክል በተንከሌ ሳቅኩኝ:: ደግ አደረግኳት ኡሁሁ ሁ . . . .::

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

አገር ሰላም ብዬ ስራዬን ጨርሼ ክፍሌ ነበርኩ:: ቀበጥ ሲያደርገኝ የጨኸቱን መነሻ ለማወቅ ተስፈንጥሬ ወጣሁ:: ኮሽታ እንዳላሰማ በጣም ተጠንቅቄ የባልና ሚስት ንትርክ ለማዳመጥ ጆሮዬን በቀጥታ ያሉበት ክፍል በር ላይ አስደገፍኩ::

«ባህቢክ /እወድሻለሁ/::»

«ካም መራ /ምን ያህል/?»

«እልፍ መራ /ሺ ጊዜ/::»

«ውሸታም አንተ መጀመሪያ ወደህ የመጣኸው ገንዘቤን ነበር አሁን ደግሞ የምቀልብህን ዱቄት ነው የምትወደው:: ለነገሩ እንዳንተ ያለ ልፍስፍስ እንዲወደኝ አልፈልግም:: ወንድ እንዴት ለሴት ይንበረከካል? ይታይህል ተንበርክከህል እኮ ኡሁሁ. . .» የፌዝ ሳቅ የእመቤቴ ድምፅ ነው::

«ይህን ሁልጊዜ ትነግሪኛለሽ:: ታስታውሻለሽ ለመጀመሪያ የወንድ ወንድ ነበርኩ:: ደግሞ ሁሌ ወንድ

አይደለህም ትይና ወንድ ሁን ብለሽ ናልኝ ትይኛለሽ። ህይወቴን እንዴ ወስደሻታል። እጠላሻለሁ። ያላንቺ መኖር እንዳልችል አደረግሽ። ሰውነቱ ሁላ ሲሰባበር እየተሰማኝ ነው። ዱቄቴን ካልሰጠሽኝ እንደምሞት አውቀዋለሁ ከመሞቴ በፊት ግን እገድልሻለሁ! አንቅሻለሁ! ገባሽ ድምፁ ወደ ህፃን ተቀየረና አለቀሰ «ዱቄቱን የት አደረግሽው?»

«ዛሬስ እንደፈለግክ ብትሆን አልሰጥህም ብዙ ብሬን እንደማፈስበት እወቅ አሁን ሀሳቤን ቀየርኩ ገንዘቤን ባንተ ዱቄት አልጨርስም ሌላ ነገር አስቤበታለሁ»

ምን እንደደበቀችበት ገብቶኛል። የሚያፈካውን ሲያስቅ ሲያስፈነድቅ ሲያዘፍነው የሚያድረውን ነገር ነው። ያ ሁሌ አፍንጫው ውስጥ እንዲገባ በቀሰም መሳይ ካርቶን የሚስበውን ከዛም እሰይ የሚያሰኘውን እፅ።

ይህን ሁኔታ በግልፅ ማየት ከጀመርኩ ሳምንታት ቢያልፉኝም ምንም ሚስጥር ሳይቀር አውቄም እያለ አፍዞ እዚህ ያስቀመጠኝ ምን እንደሆነ እኔንጃ። በርግጥ ሴትዮዋ የካንሰር በሽተኛ መሆኗን ካወቅኩ በኋላ ልተዋት አልፈለግኩም። እንደውም ቀስ በቀስ ልቀርባትና የቀራትን አጭር ዓመታት የእስላም ንሰሐ እንድትገባ ልመክራትም እቅድ ነበረኝ። በሌላ በኩል ይህ ሞት የሚያስፈርደው የጌታዬን ያን መጥፎ ዱቄት መጠቀም የፖሊስ ሁኔታ እያሰላሰልኩ ባካባቢዬ ያጠረኝን አደጋ ለመጋፈጥ አለመንቀሳቀሴ የሚገርም ነው። በዚያ ላይ የመኖሪያ



ፍቃድ የለኝም። እንዴ ሳሚ ባለበት ስለሀሺሽ ሲወራ ሳሚ የነገረንን ታሪክ አልረሳውም።

አንድ ፓክስቲያናዊት ናት አሉ . . . ሴት ሕፃን ልጅ ይዛለች። ለካ የያዘቻት ሕፃን ትኩስ ሬሳ ናት እና የሆድ ዕቃዋን አውጥተውት ሆዷን በጥበብ ሀሺሽ ሞልተውታል። . . . አቤት ስንት አይነት ቀውጢ ሕዝብ አለ . . . ከዛ ረጅም ሰዓት የሕፃኗን መተኛትና የሴትዮዋን መረበሽ ያስተዋለች አስተናጋጅ ትጠራጠርና ትጠይቃታለች በዚህ ሁኔታ ተያዘች። ሴትዮዋ መፍዘዟ ሞቷን ፈርታ ነው። አውሮፕላን ውስጥ ወደሰዑዲያ ሲገባ የሚሰጠው ፎርም ላይ በቀይ ፅሁፈት ሞት ለሀሺሽ አጓጓዦች ይላል። እርሱ ይሆናል የሀሺሿን ፓክስቲያን ያርበተበታት።

ጆሮዬን እንዳስደገፍኩ በሀሳቤ ይህ ዱቄት የሚያመጣው ሰበብ ውስጥ በማላውቀው ሁኔታ ብገባና . . . ወዲያውኑ ልብስሽን ጠቅልለሽ ውጪ ውጪ አለኝ። ጌታዬ ማልቀሱን መጮሁን መለመኑን አላቋረጠም። ቆየና «ትሰጪኛለሽ . . . አትሰጪኝም» ብሎ አስፈራራ

«ስበረው ሌላ እቀርፃለሁ» አለችው ረጋ ብላ፣ ወዲያው ቧ ብሎ የተፈረካከሰ ነገር ሰማሁ። ድንገት በሩን ሲከፍት ተንደረደርኩና ክንዱ ላይ ወደቅኩ።

«ኦ! ነገር ስትጠቢ ነበር» አለኝ በንዴት። የእመቤቴ ፊትም በንዴት ቀልቷል። እኔም ድርጊቴ አሳፈረኝ።

«ጥሩ ጊዜ ነው የደረስሽው» ብሎ ሻሼን ጨምድዶ እንደያዘ ቀለደ «እቃ ሲከሰከስ ዷ ይላል እንደሀውልትሽ፤ ሰው ከፎቅ ሲከሰከስ ምን ድምፅ ይፈጥር ይሆን?» ብሎ ጐተተኝ:: ሰውዬው ሙሉ ለሙሉ አዕምሮውን ስቶ የሚያደርገውን አያውቅም::

መጀመሪያ የተቀጠርኩ ሰሞን እያስበረገገ ያስነሳኝ የነበረው ክፉ ቅዠት እውን ሆኖ ከፊቴ ሲራመድ አየሁት:: ፀጉሬን ጨምድዶ እየዛተ ወደ ፎቁ መጨረሻ ሲጐትተኝ ለይቅር በለኝ ነፍሴን በሰላም ተቀበላት ፀሎትን ለመድገሙ እንኳን አዕምሮዬ በፍርሀት አልሰከን አለ:: በሽንቴ የራሱ እግሮቼም እየተንቀጠቀጡ አልታዘዝ አሉኝ::

«ፀጉሬ ወደመነቀሉ ደርሶአል:: ጭንቅላቴ ላይ ያለው ህመም ሲበረታ እግሮቼን ወደሚጐትተኝ ሀይል አቀረብኩ . . . ተራመድኩ . . . ወደፎቁ ጫፍ ላይ እንደደረስን::

«አቲኒ ሽም ዋላ? /የሚሸተተውን ስጪኝ ወይደሞ!/ ብሎ ታች ላለችው እመቤቴ በማስፈራራት ጮኸ:: እኔ ውሳኔዋን አውቄአለሁ:: ለእኔ ስትል ያን ውድ ዱቄት አትሰጠውም:: ሀውልቷን የምትወደውን ህይወቴ ነው እያለች የምትደጋግመውን . . . ሀውልቷን ሲሰብር ያልሰጠችው እኔማ ምንድነኝና . . .:: ወይኔ መከስከሴ ነው:: የዱቄቱን ቦታ አውቀዋለሁ ብዬ እንኳን ለመናገር አማርኛ ብቻ እየቀናኝ ሰውየው አልገባውም አረብኛም



እንግሊዘኛም ጨርሰው ጠፉብኝ በዚያች ቀውጢ ደቂቃ:: ተከስክሼ ብሞት እንኳን ጥሩ . . . ያሳሰበኝ የመዳን ጉዳይ ነው:: ብድንስ? ፎቁ በጣም ቢረዝም እንኳን እንደሚገድለኝ እርግጠኛ እሆን ነበር:: ይህ አጠር ያለ ነው:: እግሬን . . . ወይ እጄን . . . ወይ ጀርባዬን . . . ወይ ደግሞ አእምሮዬን ከጥቅም ውጭ አድርጐልኝ. . . ወይ አልሞት . . . ወይ አልድን ::

ጭው ያለ ሌሊት ስለሆነ ሊረዳኝ የሚሞክር የለም:: ራሱን ሊቆጣጠር ያልቻለው ጌታዬ አይኖቹ ደፍርሰው የሞት መላክ ሆኖ ታየኝ::

ዝልፍልፍ ብዬ ልወድቅ ስል ክንዴን ጨምድዶ ብድግ እያደረገ «ለመሞት አትቸኩይ! ደግሞ ማን እንቺን ሊሸከም እና ሊወረውር ነው?! እራስሽው ነሽ የምትዘይው!»

እመቤቴ ለነገሩ በጣም የተዝናናች ትመስላለች

«ካላስ /በቃ/ ተዋት ሀውልት እንደምቀርፅላት ቃል ገብቼላታለሁ:: መጀመሪያ ከመሞቷ በፊት ሀውልቷ ማለቅ አለበት:: ከዚያ ሀውልቷን በገዛ እጇ ታፀዳለች:: ከዛም ለሀውልቷ ታነባለች:: ከዚያ እንደፈለግክ ትከሰክሳታለህ!» አለችና ቀለደች:: ዱቄቱን ልትሰጠው ተስማማች:: ሽንት ሽንት የሚለውን እግሬን እንኳን ለመታጠብ ጊዜ ሳልወስድ በጠዋቱ ወደ ቤቴ ተመለስኩ::

ወዲያውኑ ቦታዬን መቀየር ነበረብኝ። አብረውኝ የተከራዩትን ቅድስትና ሰባህን ማሳመኑ አስቸጋሪ ነበር። አዲስ ሥራ ለመፈለጉም ሆነ አዲስ ቤት ለመከራየቱ ማሰቡ እራሱ ከባድ እራስ ምታት ነው። ለአንድ ወር እንኳን ሥራ መፍታቱ ሊያስከትለው የሚችለው ችግር አመቱን ሙሉ ይጉትታል። ደግነቱ አብረውኝ የተከራዩት እነሰባህ ፖሊስ በጣም ይፈራሉ ሁላችንም የመኖሪያ ፍቃድ የለንም። የምታሰራኝ ሴት በፖሊስ ታስፈልገኛለች ብቻ ማለቱ አስፈንጥሮ ሻንጣቸውን እንዲያዘጋጁ ያደርጋቸዋል።

በዚህ ሁኔታ ከከባዱ ፍርሀቴ እፎይ ብዬ ተገላገልኩ።



# ምዕራፍ ስድስት

በዚያን ወር በጣም ብዙ የሳዑዲ ሴቶች የአበሻ ሠራተኛ ይፈልጉ ነበር። ለኔም ይሄ ጥሩ አጋጣሚ ሆነልኝ። ምክንያታቸው የፊሊፒን ሠራተኞችን ከቤታቸው ማስወጣታቸው ነው። እኚህ የሳዑዲ ሴቶች የአንድ አገር ሰው አንድ ይመስላቸዋል።

ነገሩ እንዲህ ነው ወሬው የተናፈሰው ከሌላዋ አረብ አገር ከኩዌት ነው። የኩዌት ሴቶች የቤት ሠራተኞቻቸውን በጣም እንደሚያሰቃዩ ይታማሉ።

እናም አንዲት ፊሊፒናዊት እመቤቷ እንደጋርዮሽ ዘመን እየጠፈጠፈች ታሠራታለች። ፊሊፒኗ በጣም ትማረርና ቂም ትይዛለች። ከዛ የሁለት ወር ዕድሜ ብቻ ያለውን የአሠሪዎቿን ሕፃን የማቀዝቀዣ /የበረዶ መሥሪያ/ ውስጥ ከትታ መሞቱን ስታረጋግጥ ከአልጋው መልሳ ታስተኛውና ዝም ትላለች። ሕፃኑ ሆስፒታል ሲመረመር በሀይለኛ ብርድ መሞቱ ይታወቃል። የሕፃኑ ወላጆች በሕፃኑ ክፍል የተደረገለትን የአየር ማቀዝቀዣ መቋቋም አቅቶት መሞቱን ተረድተው ሠራተኛዋ ሳትጠረጠር የሥራ ጊዜዋን እየተጠፈጠፈች ትጨርስና ወደ አገሯ ትገባለች። አገሯ ሆና ላሰቃየቻት እመቤት የቂም በቀል ደብዳቤዋን ትልካለች። ደብዳቤው የሕፃኑን አገዳደል በቅደም ተከተል ይገልፃል።

ይህ ወሬ ጅዳ እንደደረሰ ወዲያውኑ የፊሊፒን የቤት ሠራተኞች ተፈላጊነታቸው ቀነሰ። እኛ ሀበሾቹ ቦታቸውን ልንተካ መልካም አጋጣሚ ሆነልን።

እመቤቴ አጠር ያለች ሆና ከአንገቧ ስር የተንጠለጠለው ስጋ ጉትቷት ይበልጥ ያጠረች ትመስላለች። ያለምንም ስጋ እንቢ ብሎ ለብቻው የተገተረ ዘለግ ያለ አፍንጫዋ ከወደላይ እንደቁራ ምንቃር ሰበር ያለ ነው። ስትናገር የሚያነፋንፋትም ስብራቱ ሳይሆን አይቀርም። ሰውነቷ እጅግ በጣም ወፍራም እያለ ፍጥነቷ የማይታመን ነው። ከቂጧ ጋር ብቻውን የሚንቀሳቀስ አካሏ ሌላ ስም ያሻዋል። እንደው አንድ አሽሟጣጭ አዝማሪ ሽንጧ ሲውረገረግ አቤት ወገቧ እያለ የሚያዜምላት አይነት ነች። ስታወራ ከመጠን ያለፈ እጆቿን ስለምታወናጭፍ የምትለው ከእጆቿ መወራጨት ጋር ዝብርቅርቅ ይልብኛል። ትናገር ትናገርና ብረታማ ጥርሶቿን ፍልቅቅ ታደርጋለች። አንዳንዴ የራሷ ያልሆኑት ብረታማ ጥርሶቿ እየተንገጫገጩ የራሷኑ ጆሮ ሳይዘገንኑ አይቀሩም። ሴትዮዋ የሴት ወዘና የለባትም።

ልጆች እንደሌላት ገና ስገባ ነው የነገረችኝ። ለማየት የጓጓሁት ባሏ ያልጠበቅሁትን ውበት ይዞ ክው አደረገኝ። የገረመኝ ደግሞ በመሀላቸው ትልቅ የውበት ልዩነት እያለ በባሏ ሳትቀና እንደሌሎቹ እመቤቶች የተለመደ ማስጠንቀቂያ ፈፅሞ አላሰማችኝም . . . «ባሌን ቀና ብለሽ ብታይ?! . . .» የሚለውን። እኔም «ፐ ደግሞ ቀሚስ ለብሶ ለሚንጀላጀል ወንዳቸውን ወንድ ብለው . .»



በሚለው ማሽሟጠጤ ፋንታ «ወንዱ እብድ ነውን? ይህን ሁሉ ውበት ለዚች አስቀያሚ እንዴት ይሰጣል። እርሷስ ይህ ሁላ ውበት ያለው ወንድ እንደማይገባት እያወቀች እንዴት ይህን ከባድ የተፈጥሮ ወንጀል ትፈፅማለች!» በሚለው ተካሁ።

የአረብ ወንዶችን በቀሚሳቸው መናቄ ከልብ አልነበረም። ነገሩ ሌላ ነው። የአረቡ ወንዶች በጣም በጣም የሚያጓጉ ናቸው በጣም . . .

«ጀዲድ ሽቃላ /አዲስ ገረድ/?» ጠየቀ

«አይዋ /አዎን/» አለችው

ከአይኑ ስር ሊሸሸገው ያልቻለ ፈገግታ አየሁበት። በጣም እረጅምና ደልዳላ አካል አለው። ልቤ ወዲያውኑ መጨፈር ጀመረ። ግን ቁመቱን ችላ እንዳለ ሰው አይኔን ወደመሬቱ አደረግኩ። ተስማምቼ ሥራ ጀመርኩ።

ልጆች ስለሌሉ ብዙ የሚያደክም ሥራ አልገጠመኝም። ብቻ ወጣትነቴን የሚፈታተን ውበትን ፈርቻለሁ። ቀስ በቀስ ከሰውዬው ጋር ሳላስበው የአይን ንግግር ጀመርኩ። የዓይን ጨዋታ . . . ባይኑ ብቻ።

ከወደመሀል ጥቁር ሰማያዊ የሆነውን የዓይኑን ብሌን ወደ አመዳማ ግራጫ የሚያደላ ወፍራም ክብ ሰርቶ አድምቆታል። የተቀረው የዓይኑ ክፍል ነጭ ነው . . . የንጣት መጨረሻ ነጭ። እንቅልፉ እንኳን ቢመጣ ይቀንሳሉ እንጂ አይደፈርሱም ሁሌ የነፁ ናቸው። በእግር

ጣቶቹንና እጆቹን የወረሰው ፀጉሩ አካላቱ በሙሉ ፀጉር ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። ፀጉር የሞላው ወንድ ውድድ የማደርግ ይመስለኛል። ልክ ሕፃናት እያለን አባ ጨጓሬ እያልን የምንጠራው ተክልን ቆርጠን እጆቻችን ላይ ስናነካካው የሚፈጥረውን ልስላሴ ዓይነት ልስላሴ መላ አካሌን . . . ገላዬን በመላ በፀጉሩ የሚያጫውተው ይመስለኛል።

ሁሌ ማታ ማታ ሥራ ጨርሼአለሁ ብዬ ለመኝታ ስሰናበት እመቤቴ አይናን ከቴሌቪዥን ላይ ሳትነቅል

«ነሚ /ተኚ/» ስትለኝ ባሏ ግን ስርቅ አድርጎ የሚያጠግብ ፈገግታ በዓይኑ ይሰጠኛል። ባይኑ ፈገግ የሚል ሲያሰኘው የሚፈነድቅ ቆንጆ ነው ብዬ ተመኘሁት። በማያገባኝ በሚስቱ ስቀና ተሰማኝ።

«ለምን አትወፍር ይህን የመሰለ ገላ እያቀፈች» አንዳንዴ በህልሜ በዚያ ወንዳወንድ ቁመናው በጣም ሲጫነኝ ደክሞኝ አድራለሁ። የእውነት አብሮ ያደረ ያክል ሰውነቴ በምኞት ድቅቅ ሲል ይውላል።

ምኞቱ ምኞት ሆኖ አልቀረም አንድ ቀን አይኔን ስከፍት የእውነት ከፊት ለፊቴ ቆሞ አየሁት። ያን የመሰለ ወንድ የክፍሌን በር ከፍቶ ካልጋዬ አጠገብ . . . የምሆነው ጠፋኝ። ረጋ ብሎ አልጋዬ ጫፍ ተቀመጠ።

«ባህቢክ /እወድሻለሁ/» አለኝ እኔ ዝም



«ምን አወል ነዝራ /በመጀመሪያ እይታ/» አለኝ። እኔ ዝም

«ኢንቲ ጀሚላ ወቡኒ /ቆንጆና ቡናማ ነሽ/» አለኝ። እኔ ግን ዝም።

ብድግ ብዬ አልፌው ልወጣ ስል ወገቤን ያዘኝ . . ጠንከር አድርጐ መተንፈስ አቃተኝ። ወደ ላይ ብድግ አደረገኝና እንደሕፃን አየኝ። ደግሞ አወረደኝ። መፍዘዜን እርግጠኛ ሲሆን ቀስ አድርጐ አስተኛኝ። ረጅም የመኝታ ቀሚሴን ከእግሩ ጀምሮ እስከ አንገቱ ቀደደው . . . በመንገብገብ ዓይነት። ቢጃማዬ ሲቀደድ ያሰማው ድምፅ ሚስቱን ከእንቅልፏ የሚቀሰቅስ የመድፍ ድምፅ ሆኖ ጐልቶ በጆሮዬ አንጣረረ። በጣም ስለሰጋሁ ከእጁ ተስፈንጥሬ ተነሳሁ።

«እንዴታ ዳዋ አሻን ትነም /እንድትተኛ መድኃኒት ሰጥቼአታለሁ/» አለኝ። ፍራቻዬን አቃለለልኝ። ግን ደግሞ በውበቱ የሚያታልለኝ ሰይጣን መስሎ ተሰማኝ። ለወትሮ ያስቀናችኝ ወፍራሚ ሚስቱ አሳዘነችኝ ሲጠጋኝ ገፋሁት። እርሱ ግን ሀይል አልተጠቀመም። ዓይኖቹ ብቻ የተለየ ሀይል አላቸው። ልከላከለው የማልችል የውበት ጌታ ነው። እንዴት ላመልጠው እችላለሁ?

የለሰለሱ አረብኛ ቃላት እያለልኝ በትላልቅ እጆቹ እሽት አደረገኝ። ሀሳቤን አንስቼ ለልቤ ፈቀድኩለት። መላ ሰውነቴን የመንክስ ያህል ሳመኝ። እንደዛ ተስሚ አላውቀም። ቀስ እያለ እውስጤ ሲገባ ሀይለኛ ህመም

ተሰማኝ:: ሰውነቴን ማንቀሳቀስ አቃተኝ:: አቅፎ አነሳኝና ባኞ ቤት ከተተኝ . . . አጠበኝ እያባበለ:: አንሶላዎቹን ማጠቢያ ማሽን ከትቶ እስኪጨርሱ በተፈጠረው ነገር እንዳልሰጋ ሌላ ቤት ተከራይቶ እንደእመቤት እንደሚያስቀምጠኝ ቃል ገባልኝ::

ማሽኑ አንሶላዬን አድርቆ ሰጠው:: አልጋዬን በትክክል አንጥፎ ሁሉም ነገር እንደነበረ ሆነ ከእኔና ከመኝታ ቀሚሴ በስተቀር:: ጠዋት እየታመምኩ ተንቀሳቀስኩ::

በሦስት አራት ቀን ዩሰሪ እንዴት ነሽ ይለኛል:: ለሊቱን ከኔ ጋር ያሳልፋል . . . ሚስቱን በመኝታ ድባብ ቀልፎባት:: እየበዛ ሲመጣ እኔው መቅናት አመጣሁ . . . በወፍራሚ ሴት :: ቅናት ቅጥል ሲያደርገኝ አትንካኝ ስለው እርሱ በእልህ ጭምቅ ሲያደርገኝ ሲያሳምመኝ ብዙ ቆየን::

አነስ ያለች ቆንጆ ቤት ተከራይቶልኝ ሥራዬን ለቀቅኩ:: ሴትዮዋ ምንም ሳትጠረጥር ባሏን ይዤ ወጣሁ:: ማንም ሳያውቅ ጉጆ . . . ትዳር ግን ላጭር ግዜ:: ምግብ ውሃ ሁሉንም ነገር ያመጣልኝና የቶሎ ቶሎ ሳም ሳም አድርጐኝ ውልቅ ይላል::

ለሽርሽር ከከተማ ወጣ ብሎ ከባህር ዳር የተሠሩ ትናንሽ ቪላ ቤቶች ካሉበት ወሰደኝ:: «ይኼ ትንሽ ነፃነት አለው ግን የሚፈቀደው ለተጋቡ ሰዎች ብቻ ነው» አለኝ:: እኔ ታዲያ «መች ተጋባን እኛ» አልኩት:: የደረት ኪሱን እየዳበሰ «አትጨነቂ» አለኝ የሆነ ወረቀት እንዳለ ገባኝ:: ወረቀቱን ለማየት አልጓጓሁም:: እንዳልተጋባን አውቃለሁ::

እስካሁን ባአገራቸው ያላየሁትን ውበት አሳየኝ:: እኔ ደግሞ ውበት ሳይ ከምግብ ጀምሮ የሁሉ ነገር ፍላጐቴ ይቀሰቀሳል . . . ኡፍ ውበት ይገዛኛል:: ቦታው ውብ ነው::

የሰማዩና የባህሩ ከለር ተመሳስሏል:: ባህሩ ፀጥ ያለ ነው. . . በዚያ ላይ ጥርት ብሎአል:: ከላዩ ላይ የሚነፍሰው ሽውታ ህይወት ነው:: በበረሃ ላይ ይህን የመሰለ ውበት . . .:: እየሩም በተናጥል ለዚህ ስፍራ ብቻ የተሠራ ይመስላል . . . ቀዝቀዝ ያለ ነው::

ባህር ዳር ተቀመጥን:: ሁለታችንም ለለበስነው ልብስ መበስበስ አልተጨነቅንም:: ተቀራርበን ተቀምጠናል:: እግሩን በውሃ ውስጥ ከእግሬ ጋር ቆለፍ ፈታ እያደረገ እሩቅ እሩቅ ያያል:: እኔ ቀስ እልና አየት ሳደርገው ዩስሪ የማላውቀው ቆንጆ ነገር ይሆንብኛል:: የተቀመጥንበት ቦታ ጨምሮለት ነው መሰለኝ ይበልጥ አምሮአል:: እሱም እኔን የመሰጠኝ ቦታ እጅግ መስጦታል:: በሀሳቤ አረብ ባይሆን ኖሮ ሰዓሊ ይወጣው ነበር አልኩ. . . እነሱ ከልጅነታቸው ጀምረው የሚጫናቸው ከባድ ድሎት አሟሙቆ ስለሚያስተኛቸው ደስታ ፍለጋ አይደክሙም ለስዕል . . . ለፅሁፍ::

አኳኋኑን ሳይለውጥ የአገጩን ጺም ሳብ ሳብ እያደረገ በአንደኛው እግሩ ከጣቴ ጀምሮ ወደ ጭኔ . . . ቀስ እያለ ወደላይ ወጣ። እኔም የባህሩ ውሃ ሞቅ እያለ የመጣ መሰለኝ። ሙቀቱ ደስ ይላል። ለስለስ ያለ ነው። የዩስሪ እግርም።

እኔ ስቁነጠነጥ እሱ ግን ርቆ ሄዶ ወደ ሄደበት ሊስበኝ ይሞክራል። ተጠጋሁት አሁንም አያየኝም ብቻ እግሬን እንደቅድሙ ደጋግሞ ያደርጋል። መላ ሰውነቴ ጋለ። ወደ ባህሩ ሳይ ባህሩ ለእኔ ብቻ የተንጣለለ የራሴ መሰለኝ። እጄን በውሃ ውስጥ ከተትኩና ስነካው እርሱም ከእኔ የበለጠ እንደፈለገኝ ተረዳሁ። ዞሮ አላወራልኝም። እንደሚፈልገኝ አልነገረኝም። ከቤት ውጪ የፍቅር ተግባራት ነውር ነው። እራሴን ወደባህሩ ገፋሁና ውሃው እስከአንገቴ አለበሰኝ። የድንብሩን አካባቢውን አየና «ኤብ /ነውር/» አለኝ። የክፍላችንን ቁልፍ ሰጠኝና «ሂጂ እከተልሻለሁ» አቃሰተ።

እክፍል ውስጥ ብቻችንን ስንሆን ዩስሪ የተለየ ነው እብድ ይሠራኛል። በሴትነቴ እስካመልክ ድረስ እየካበ በአይኖቹ ፍቅር መበተን ይችልበታል። አይኖቹን ፍዝዝ ካደረገ ቁንጅናው ይበልጥ ይገንና ውበት ወዳጁ ልቤን ቅልጥ ያደርግብኛል። አንዳንዴ እራሴን በእንባ ስታጠብ አገኘዋለሁ።

ከሽርሽሩ መልስ አዲሷ ቤታችንን ቁልፎብኝ ሲሄድ ግን እስኪመጣ ብዙም አልናፍቀውም። ፍቅር ናፍቆትን



ያስከትል የለ? እኔ ግን በግማሽ ፍቅር ተጠምጄ ወይ ጉድ ማለት ጀምሬአለሁ። እኔ የማፈቅረው ሲዋብ አይኖቹ ሲፈዙ ብቻ የመሆኑ ጉዳይ ገርሞኛል።

ነገሮቹ ሁላ በፍጥነት አድገው በፍጥነት ሊጠፉ ነው። ብዬ ብዬ ስለሚስቱ እንዲነግረኝ ጠየቅኩት። ለምን እንደሆነ እራሴም አላውቅም። ከሁለት ላንዱ ሁኔታዬ እንደሚሆን ግን እርግጠኛ ነኝ። ስለሚስቱ ሲያወራልኝ በቅናት ነድጄ እየከሰመ ሊሄድ የተቃረበውን ፍቅር እፍ ብዬ ለማንደድ ወይ ደግሞ ስለ ሚስቱ ሲያወራልኝ ምንም ሳልቀና እየጠፋ የሄደው ፍቅር እፍ ብሎ ጨርሶ ለማጥፋት . . . እራሴን አዘጋጀሁ።

«ስለሚስትህ ንገረኝ»

«ሚስቴ እንዳየሻት አስቀያሚና ወፍራም ሴት ነች»

«ታዲያ ምኗ ነው . . .»

«ታውቂያለሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሚስቴ ለሌላ ሴት ፍላጐት ሲኖረኝ! ምናልባት በህይወትሽ የመጀመሪያው ወንድ ስለሆንኩ ይሆን እንዲህ ስለሁሉ ነገር የማወራልሽ? ብቻ ምን ያህል ጥሩ ልጅ እንደሆንሽ ታውቂያለሽ?» ሳመኝ።

የፍቅር ጨዋታ ውስጥ እንዲገባና ውይይታችንን እንዲያበቃ አልፈለግኩም። ለወሬው ብቻ ሳይሆን ፍላጐቱ ቅዝቅዝ ብሏል . . . ዩስሪ አጠገቤ ሆኖም። ያ ሁሉ የጋለ ስሜት የት ገባ? ስለፍቅር ብዙ ሲባል ሰምቼአለሁ።

ላጭር ጊዜ አፍቅረው ቶሎ የሚረሱ ዓይነት ሰዎች እንዳሉም አውቃለሁ:: እኔ ከእንደነሱ አይነት ሰዎች አንዷ እንድሆን ፈፅሞ አልመኝም:: ይሉኝታም በጣም እየተሰማኝ መጥቶአል:: በዚች ሦስት ወራት ዩስሪን በቃኸኝ ማለቱ የእብደት ያህል ተሰማኝ:: በየሦስት ወራቱ የሚያከትም ፍቅር የሚይዘኝ ፍጡር ከሆንኩ በህይወት ዘመኔ የስንት ፍቅር ባለቤት ልሆን ነው?! ወይስ የያዘኝ ፍቅር አልነበረም?! ያ ሁሉ ቃጠሎስ ሌላ ስም ይኖረው ይሆን?!

ዩስሪ የሚስቱን ገለፃ ቀጠለልኝ::

«ሚስቴ እስከሁን ካየኋቸው ሴቶች ሁሉ የተለየች ናት ማለቴ ከእናቴ እህቶቼ ከዚህ በፊት ካየኋቸው ፍቅረኞቼ . . . ከሁሉም::»

አቋረጥኩትና «ዩስሪ ሚስቴ አትበል በኔ ፊት በስሟ ጥራት»

«ለምን? ትቀኛለሽ?» የደስታ ፊቱ ቦግ አለ:

«አይ ሳይሆን . . .»

«እሺ ልቀጥልልሽ ሚስቴ . . . ይቅርታ . . . ናዲያ ሁለት ወንድማማቾች የወለዱን የአጐት ልጃማቾች ነን:: በልጅነታችን ጊዜ ብቻዋን የመሆን ልማድ ስለነበራት ምንም የልጅነት ትዝታ ከእርሷ ጋር የለኝም:: ስንጋባ የመረጥኳት እኔው ነበርኩ:: እናቴ በተለይ አስቀያሚነቷን እንደ ትልቅ ነውር ቆጥራ ስርጉ



እንዲሰናከል ብዙ ጥረት አድርጋ ነበር:: እኔ እንግዲህ እንዲህ ነኝ ሚስት ስመርጥ:: ሚስቴ ለእኔ ብቻ መሆን አለባት ባይ ነኝ:: ቆንጆ ከሆነች ብዙ ነገሮች ይጋሩኛል:: ወንድ ማለቴ አይደለም:: የሳውዲ ሴቶች የሚያደርጉት ግብዣ ብዙ ነው:: እንደውም ብዙዎቹ ግብዣ ህይወታቸው ነው:: ይጋበዛሉ ይጋበዛሉ ይለብሳሉ ይፈነድቃሉ:: ይህ ሁላ ባላቸው ትከሻ ላይ ነው:: እንደምታውቂው ሚስቱን የሚያሠራ ወንድ ወንድ አይደለም የሚል ባህላዊ ተፅእኖ አለ:: ወንድ ይሠራል ሚስት የሠራውን ሁላ በግብዣ ምሽት ውድ ቀሚሶች አፍሳ ትጨርሳለች:: በተለይ በተለይ ለእራሳቸውና ለልጆቻቸው በቂ ነው ብለው የገመቱትን ሀብት ከያዙ የተትረፈረፈ ሀብት የሚያመጣባቸውን ሰበብ ለመቅጨት ጥሩ የገንዘበ መበተኛ ዘዴአቸው ግብዣቸውን ማብዛት ነው:: በግብዣ ወቅትም ተሰብስበው የባላቸውን ንብረት የመቀነስ ወይም በራሳቸው ስም ለማድረግ ውጥን ይወጥናሉ:: ሞኞች ናቸው:: በርግጥ ሁለተኛ ሦስተኛ ሚስት ለማግባት ገንዘብ ወሳኝነት አለው:: ይህን የሚያደርጉት ባሎቻቸውን ጠልተው ሳይሆን ሀይማኖቱ እና ሕጉ የሚፈቅደውን ከአንድ በላይ ጋብቻ እንዳይፈጠር ለመከላከል ነው:: ታዲያ በሌላ ጐኑ ሚስት እንዲያገባ መገፋፋታቸውን አያውቁትም:: ሌላ ጋብቻ የመፍጠሩ ሁኔታ የሚፈጠረው በገንዘብ ብቻ ይመስላቸዋል:: በዚህ መንገዳቸው የባላቸውን ህይወት አሰልቺ ማድረጋቸውን አያገናዝቡም:: ይህን ሕይወት ከማግባቴ በፊት በታላላቅ እህቶቼ በእናቴ በአጐቶቼ በሁሉም አይቼዋለሁ:: ታዲያ

ቆንጆ ሴት ካገባሁ እንደፈለግኩ ላደርጋት አልችልም ብዬ ናዲያን አገባኋት።

ካገባኋት በኋላ ግን ይህችን ሴት የሴቶች ሁሉ ቁንጮ አድርጌ እንዳከብራት የሚያደርገኝ ብዙ ባህሪያቶችን አገኘሁ። እርሷን በማግባቴ በየቀኑ ደስተኛ ሆንኩ። ይገርምሻል ናዲያ ሙሉ ነፃነትን ሰጠችኝ። ማውራት የምፈልገውን አወራላታለሁ . . . ካልፈለግኩ አትጠይቀኝም። የት ሄድክ ከየት መጣህ አትልም። ዝም ያለች ናት። እና ይህ ሁኔታዋ ከእርሷ ያላገኘሁትን ቅጥነትና ቁንጅናን ከሎች ባገኝሁ የማትቃወም መሆኗን አረጋገጠልኝ። ህይወቴ የእርሷ እንደሆነች ታውቂያለሽ? ከእርሷ ፍፁም ሰልችቼ አላውቅም። የምሳ ሰዓትና እራት ሰዓት አሳልፌ አላውቅም። በጣም እንዳከብራት አክብራኛለች። ስሜቴን የሚነካ አንድ ቃል ተንፍሳ አታውቅም። ይህች ሴት እራሷን ጠንቅቃ ያወቀች ብቸኛ ሴት ነች። ብዙ ጊዜ ሴቶች ባሎቻቸው ወደሌላ ሲሄዱ ምንድን ነኝ ብለው እራሳቸውን በትክክል ከመገምገም ይልቅ ሽንጣቸውን ይዘው «ከእኔ በምን ትበልጥና ነው እርሷ ጋር የሄድከው» ብለው ይንጣጣሉ። እኔ ልሰጥህ ያልቻልኩት ምንድን ነው ብለው እራሳቸውን አይጠይቁም። እርግጠኛ አይደለሁም እንጂ እኔ ከተለያዩ ቆንጆዎች ጋር እንደምተኛ ሚስቴ ሳታውቅ የምትቀር አይመስለኝም። ዝም ብትልም ሞኝ አይደለችም። ግን ውበት እንደሚስለች ታውቃለች። ውበት ይሰለቻል። ስለዚህ የማይሰለቸውን የህይወት እርጋታን ትሰጠኛለች።



ሚስቴ የማይሰለች ውብ የሆነ . . . ውስጧ ቆንጆ ነው። ሥራዬ ሳይሳካልኝ ሲቀር ታረጋኛለች። ከውጭ ተናድጄ ስመጣ ታረጋኛለች። ከጭቅጭቁ ዓለም በሬን ከፍቼ ስገባ ርጋታ የሞላበትን ንፁህ ቤቴ ውስጥ ለእኔ ተብሎ በየቀኑ የሚቀየር አበባ ንፁህ አየር ንፁህ ሴት ንፁህ አልጋ ጣፋጭ ምግብ ይቆየኛል። እኔ ያለ እርሷ መኖር አልችልም የጉደላት ቁንጅና ነው ቁንጅናን ባሰኘኝ ጊዜ ከሌሎች አገኘዋለሁ። ከሌሎች ሴቶች የማይገኘውን እርሷ በትልቁ ይዛዋለች። በጋብቻዬ ደስተኛ ነኝ። ሁሉም ጓደኞቼ ስለጋብቻቸው ሲያወሩ ጀሀነብ ነው ይሉኛል። ናዲያ ህይወቴን ገነት ውስጥ ከታታለች።»

አልቀናሁም። ሴትዮዋ አሸነፈች ሁሌም ታሸንፋለች። ጉበዝ ሴት ናት። ህይወትን አውቃበታለች። ባሏን አሽከርክሮ ወደርሷው የሚስብ ከባድ ማግኔት አላት።

ደግሞም ዩስሪ ከእኔ ፊልጉ የመጣውን ነገር ስለነገረኝ እፎይታ ተሰማኝ። እኔም ውበቱን አይቼ ነበር የወደድኩት እውነቱን ነው ውበት ይሰለቻል። ተሰለቻችተናል . . . መሆኑ ነው። ለማንኛውም ውብ ወራትን አብረን አሳልፈናል።

የረመዳን ፆም ሊገባ ሦስት ቀናት ሲቀረው ስለፆሙ አስረዳኝ። «በረመዳን ወር ስህተት አይሠራም። በርግጥ በሁሉም ወቅት ስህተትን መሥራት ሀይማኖቱ ቢከለክልም ይህ ወር ግን የተለየ የሚያደርገው የሰው ልጅ

ለጌታው እራሱን በሕግጋቱ ተገዢ ለማድረግ አክብሮቱን የሚገልፅበት ልዩ ወር ነው። በመፆምም ይቅርታን ይጠይቃል። ወንድ ያለጋብቻ ከሴት ጋር መተኛቱ ሀጢያት ነው። ይህንን ስህተት እንዳይሠራ አላህ ወንድ ያማረችውን እንዲያገባ የጋብቻ ቁጥርን ለወንድ ከፍ አድርጉአል። በፆታ ጥያቄ ወንድ ከሴት ደካማ እንደሆነ አላህ ስለሚያውቅ ወንድ ከአንድ ሴት በላይ እንደምታስፈልገውም ለእኛ ተረድቶልናል። ግን ከጋብቻ ውጪ ሀራም /ሀጢያት/ ነው። እኔም ይህን ሀጢያቴን ማፅዳት አለብኝ። ስለዚህ እኔና አንቺ በሰላም እንለያያለን። ጥሩ ልጅ ነሽ።»

ምክንያቱ ይህ መሆኑን አልጠበቅኩም እንጂ ከሁለት አንዳችን የመዝጊያ ንግግር እንደሚጠበቅብን አውቄው ነበር። የፍቅሩም ነገር ሲያልቅ ታውቆኛል። እኔም የምፈልገው ውሳኔ ይህ ነበር . . . መለያየት። ብቻ ከዩስሪ ጋር መቀያየሙን አልፈለግኩትም። ጠንካራ ምክንያት ሰጥቶኛል . . . ረመዳን።

ፈገግ አልኩና የውሸቴን

«በቃ . . . አ . ረመዳን ሲያልቅ እንደገና እንገናኝ»

«በአላህ ልታሾፊ እየሞከርሽ ነውን? እንዳልጠላሽ ደግሞም የሰው ልጅ አንድ ስህተትን የሚሠራው አንዴ ብቻ ነው። አል መሰል ቢኡል ላይውልዳእ ኢብን አዳም ምንጁህሪን መራቴን /የአዳም ልጅ በእባብ መርዝ ሁለቴ አይወጋም/ ይላል ተረትና ምሳሌው። ካንቺ ጋር ላደረግኩት ስህተት ይቅርታን ጠይቄ ተመልሼ ካንቺው ጋር ስህተት መስራቴ ሀፂን አያስብለኝም?»

«እውነትም፥ ሀፃን ነህ! ስቀልድህ ነው! በዚህ አይነት ከሚስትህ ሌላ ሁለተኛ ከሌላ ጋር አትተኛም ማለት ነው?»

«አ .... ይህ የታወቀ አይደለም። እኔ ለእራሴ በሀይማኖት ታስሬ ከናዲያ ጋር ብቻ ብተኛ ደስ ይለኛል። ግን ሴቶች ሰይጣኖች ናቸው። እኔም ደካማ ነኝ። አይሆንም ማለት አልችልም። ሌላ አንቺን የመሰለች ሴት ስታሳስተኝ ደግሞ የሚቀጥለውን አመት ረመዳን የይቅርታ ፀሎት ከማድረጌ በፊት ከህይወቴ አወጣታለሁ። እኔ እንዲህ ነኝ።»

«በያመቱ ሴት ስትቀያየር ጀሀነብ መግባትህ ነበር። ረመዳን ባይኖር።»

«ካንቺ ጋር ግን ረጅሙ ነበር። በርግጥ አሳብደሽኝ ነበር። ሁሉን ነገር ትችይበታለሽ። ጥሩ እድል እመኝልሻለሁ። ስራ እስክታገኚ ድረስ እንዲጠቅምሽ ይህን ብር እንቺ። ደግሞ ስራ ቦታ እንደ እኔ ሊያታልልሽ የሞከረውን አይቻልም በይ። የወንዶች ፀባይ እንግዲህ በእኔ አይተሽዋል ብልጥ ሁኚ።»

ሁለታችንም የፈለግነው መለያየትን ስለነበር አልተጨቃጨቅንም ነበር ከመውጣቱ በፊት ግን የመጀመሪያ ጊዜ የሳመኝ አሳሳም አይነት ምጥጥ አድርጉ

ሳመኝ፡፡ እኔም በቀልድ ሸኘሁት፡፡ የሰውነት ቅርፄን ጠንቅቆ ያወጣ ቀሚስ አድርጌ

«ይህን ሁላ ጥለህ ልትሄድ?» አልኩት

«ረመዳን ባይመጣ.... » አለኝ፡፡

ሀሳቡን እንደመቀየር አለና ተመለሰ፡፡ እኔም ለመጨረሻ ጊዜ ከዩስሪ ጋር መተኛቱ አስደሰተኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን አልተመለሰም፡፡



# ምዕራፍ ሰባት

ስራ ለማግናኘቱ ላበሻ ይቀላል፡፡ ምክንያቱ በውድ ዋጋ መስራታችን ነው፡፡ የንጉስ ዘር ቤተሰቦች ርካሽ ነገር ስለማይወዱ በርካሽ ለሚሰሩት ፊሊፒኖች፣ ባንግላዴሾችና፣ ሱማሌዎች ብዙ ቦታ አይሰጡም፡፡ ፊሊፒኖችና ባንግላዴሾች በሆነው ዋጋ በርካሽም ቢሆን የሚሰሩት የሳውዲው ብር ወደ አገራቸው ሲመነዘር ከበድ ያለ ዋጋ ስለሚኖረው ነው፡፡

ሌሎች ደግሞ አሉ በደም የንጉስ ዘር ያልሆኑ ግን በገንዘባቸው ከንጉስ ዘር እኩል የሆኑ ስማቸው ሼክ ይባላል፡፡ ታዲያ ስሙ በሼክ የሚጀምር የናጠጠው ነው፡፡ እነዚህም እኛኑ ለማሰራት ይፈቅዳሉ፡፡

አንዳንዶቹ ደግሞ የንጉስም ዘር ሳይሆኑ ሼክም ደረጃ ሳይደርሱ ገንዘብ አለን ለማለት ሲሉ እኛን ይቀጥራሉ፡፡ ታዲያ እነርሱ ጋ መቀጠር ይሰለቻል፡፡ ጥሩ ልብስ እንደሚያሳዩ ሁሉ የአበሻ ሰራተኛ በውድ የሚያሰራ ሀብታም ነኝ ለማለት በየድግሱ ቤት በየጓደኞቻቸው ቤተዘመድ ቤት እነርሱን መከተል ያስፈልጋል፡፡

እንደነዚህ አይነት ሰዎች ቤት ስራ ስጀምር ከስነ ስርዓት በላይ የግዞት ትህትና መማር ነበረብኝ፡፡ የእመቤቴ ጓደኞች ወይ ይመጣሉ ወይ ደግሞ እርሷ

መሄድ ስለነበረባት አባያዋን በክብር እንዳወልቅላት ይዛኝ ትዞራለች::

የሚያወሩት ወሬ ስለልብስ ስለባሎቻቸው ስለጌጣጌጥ ወይንም ስለ ውጭ አገር ሽርሽራቸው ብቻ ስለሆነ አሰልቺ ነው:: እኔም የእመቤቴ እግር ስር በርከክ ብዬ ስለምቀመጥ ያኔ እያቴ የነገረችኝ የካፐቴሺ ታሪክ ትዝ ይለኛል:: ካፐቴሺ የጥንት ምስኪን ገረድ ታሪክ ነው:: ታሪኩ ድሮ በጣም ስለሚያሳዝነኝ አያቴን ደጋግሞ ተረቱን እንድትነግረኝ እጠይቃት ነበር:: አሁን ግን ያን ተረት ጠላሁት:: እራሴን በማላውቀው ሁኔታ ካፐቴሺ እያልኩ ማሰቡ ዘግንኖኛል::

ብዙም ሳልቆይ ቀበጥኩ:: የካፐቴሺ ታሪክን ለደቂቃ ልቀይር ሳስብ ጉድ ሆንኩ::

በእንቁዎች የተጠለፈ እጅግ ውድ የእራት ቀሚስ እመቤቴ ገዝታ መጣች:: ቀሚሱ ከሳንድሬላ የአስማት ቀሚሶች የበለጠ እጅግ ያማረ ቀሚስ ነው:: ከላይ ጀምሮ እስከታች እንደላስቲክ ይለጠጣል:: ሴትዬዋ ሳምንቱን ሁላ በጉጉት እያወራች ለምትጠብቀው የእራት ምሽት ያዘጋጀችው ነው::

ሰዎቹ ሲወጡ ከሁለት ሰዓታት በፊት እንደማይመለሱ በጣም እርግጠኛ ነበርኩ:: ያን ቀሚስ በክብር ከተሰቀለበት መስቀያ በድፍረት አወረድኩና አልጋ ላይ ዘረጋሁት:: ፊቴን በሚገባ ታጥቤ ፀጉሬን የራሴ ክፍል ሆኜ በደንብ አስተካከልኩና የእመቤቴ መቆነጃጂያ ወንበር ላይ ጉብ አልኩ:: ከፊት ለፊቴ የተደረደሩትን



የፊት ማዳመቂያ ዱቄት የአይን ማስዋቢያዎችና የከናፍር እርሳስና ቀለም ሁሉንም ልክ ሴትዮዋ እንደምታደርገው በጥንቃቄ ተቀባባሁ:: ፊገግታዬ የእርሷኑ መሰለ:: አካሄድም ኮረጅኳት:: የከናፍሬ ቀለምና ኩል ቀሚሱን እንዳይነኩብኝ እየፈራሁ አጠለቅኩት:: በጣም ያምርብኛል:: ቀሚሱ የሰጠኝን የራሴኑ ቁንጅና ሳደንቅ ደቂቃዎች አለፉ::

ሙዚቃን ፈለግኩ፤ በምቱም መውረግረግ አሰኘኝ:: ሙዚቃ ከፍቼ ስውረገረግ ስሽከረከር በየግድግዳው ያሉ አንፀባራቂ መስታወቶች እራሴን ስድስት ሰባት ቦታ እያባዙ ከጉን ከኋላ ከፊት ሲያጅቡኝ የቀሚሱን ባለቤት ረሳሁ::

በር ሲከፈት የሰዎች ኮቴ ሰምቼ ችላ ልበል ወይስ አልሰማሁም ብቻ ዞር እንዳልኩ የእመቤቴን ቁመና እንደኔው በየመስተዋቱ ስድስት ሰባት ቦታ አየሁ:: ያለችበትን አቅጣጫ በትክክል ለማወቅ ለመጨረሻ ጊዜ በዚያ ነብስ ቀሚስ ተሽከረከርኩ::

ጉንጭዋ ቲማቲም መስሎ ልትበጭቀኝ የተዘጋጀች ትመስላለች . . . ኖራ መሳይ ነጭ ቀለም የተቀቡ ረጃጅም ጥፍሮቿን እንደውሮ ቀስራዋለች:: ደነገጥኩና የራሴ ያልሆነውን ቀሚስ ጭምቅ አድርጌ ስይዘው በጥንቃቄ ከተጠለፉት እንቁዎች የምታምረዋ ርዟ ተበጥሳ ንጥር እያለች እመቤቴ እግር ስር ደረሰች::

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ እራሴን ከስራ ተባርሬ እቤት አገኘሁት::

# ምዕራፍ ስምንት

የቆንጆ መኪና ስሞችን እንደሸጭ ከነዋጋቸው አጥንቼአለሁ። እነ ሮዝራይስ ካዲላክ ሌክሰስ . . . ሌሎችም እያልኩ። ቢመሽም ባይመሽም ከጉንና ጉናቸው የተሸጉጠላቸው አንፑል የመኪናውን ከለር ሳይቀር ለመለየት ያስችላል። የታርጋ ልዩነትንም ጠንቅቄ አውቄአለሁ። የግል ወይም የድርጅት ስለመሆኑ።

ችግሩ አንዳንድ የሀብታም ተቀጣሪ ሹፌሮች በተለይ ሊባኖስና ግብፆች ሶሪያዎች የመኖች ከስዑዲዎች ጋር የመልክ ልዩነት ስለሌላቸው እንደጌቶቻቸው ለብሰው የሸፈሩ ጊዜ ነው።

የገንዘብ ማግኚያው ነገር የቀለለ ይመስላል። አዕምሮዬ ዛሬ ገና የመሸጡን ነገር አምኖበታል። ስራ እንዳላፈላልግ «ቅድስት የለች! በማን በኩል ማን ተያዥ ይሆነኛል?» እለዋለሁ እራሴን ላላምን። ስራ ማጣቱ ሳይሆን ስንፍና ተደርድሮ ደፍ ብሎ ወድቆብኛል . . . . ላዬ ላይ። ኩሩው አስተሳሰቤ ቀለለና ለመቅለሉ ሙሉ ነፃነት ሰጠኝ። አጋጣሚዎች ብቅ እያሉ የነአይሻን መንገድ ማየት አለብሽ ይሉኛል። እኔ ከማን እበልጣለሁ ስደት የሚጋርደውን ሁሉን ነገር መቅመስ ደግሞ መጥፎ



አይደለም ብዬ ስለተቀበልኩ ውስጤ ወደ መሸጫው ቦታ ግፍት እያደረገ አቀረበኝ።

ሀብታሞች የሚገበያዩበት ሱቅ ሄድኩኝ። አባያዬን በሻንፑ ሙልጭ አድርጌ አጥቤ አሳምሬ ተኩሼዋለሁ። ዕቃ የምገዛ አስመስዬ በአይኖቼ ሊያየኝ የፈለገ እንዳለ ገልመጥመጥ አልኩ። ሁኔታዬ ስለሚያስታውቅ ሁለት ወንዶች ተከተሉኝ። በአይኔ ሀብታም ወደመሰለኝ ሰው አዘነበልኩና አንደኛውን ጠፋሁበት።

ሁለተኛውን ሰውዬ በአይኔ ጠቀስኩትና ወደ አንድ ሱቅ ዘው አልን አንድ ላይ።

አልተርበተበትኩም ይልቁንም ባንዱ ከፍ ምንጥቅ የማለት ጥልቅ ፍላጐትና ድፍረት ሰጠኝ . . . ማን ሞኝ አለ አልኩ ለራሴ . . . ማን ሞኝ አለ በትዕግስት ደረጃ በደረጃ የሚወጣ?! ሽው አድርጐ ፎቅ የሚያወጣ . . . . እያለ።

«የላ ከልሲ /ቶሎ ጨርሺ/» አለኝ የገዛ ሚስቱን እንደሚያዝ አባወራ።

የሱቁ ተላላኪ አይኔ ያረፈበትን ቦርሳ አውርዶ

«ማዳም ኩዲያ ኢንቲ አህበብቲያ /እመቤቴ ውሰጂአት ወደሻታል/» አለኝ።

የተከተለኝ ሰውዬ ዓይን ዓይኔን እያየ ዋጋ ተዋዋለ። ከፈለ። ቦርሳው ውድ ነው። ሰውዬው ለመክፈል

አላወላወለም:: ሰውዬው ሀብታም ነው ማለት ነው:: ተከትዬው ወደ መኪናው ገባሁ::

«ጥቁር ሴት ጣፋጭ ናት»

የንግግሩ ሁኔታ ደስ አላለኝም:: ስሜን ይጠይቀኛል ብዬ ገምቼ ነበር:: ለስሜ ግድ የለውም:: ማን ልሁን ለማወቁ ምንም ስሜት የለውም:: ግንኙነታችን የታወቀ ሆኖ እርሱ ሴት ፈልጐ እኔ ገንዘብ ፈልጌ ቢሆንም እኔ የእርሱ ቦታ ብሆን ስሙን እጠይቅ ነበር::

እቤቱ ይዞኝ ሲገባ አምስት ጊዜ ያህል በመኪናው አሽከረከረኝ:: ሁለት ጊዜ እቤቱ ገብቶ እየተቁነጠነጠ ተመለሰ:: ለሁኔታው አዲስ ነው ብዬ ገመትኩና ዕድለኛ ነኝ አልኩ::

ቁንጅናዬን ለማድነቁ ከአይኑ አነበብኩ:: ይህ ደግሞ ትንሽም ቢሆን ጥሩ ስሜት ይሰጠኛል:: ፍቅርን ለመመሰሉም ይረዳኛል::

«ከገመትኩሽ በላይ ነሽ ይህ አጭር ቁመት ይህን ሁላ የሰውነት ውበት ይዟል! ታስጐመጃለሽ! ገላችሁ ላይ ቸኮሌት እንዳፈሰሳችሁ አንድ ጓደኛዬ ነግሮኝ ነበር:: እውነቱን ነው:: ይገርምሻል አበሻ ሴት እራቁቷን ሳይ አንቺ የመጀመሪያዬ ነሽ»

«እኔም አንተ ፊት እራቁቴን መቆሜ ገርሞኛል:: ከተዋወቅኩት አንድ ሰዓት እንኳን የማይሞላኝ ወንድ ሁሉ ነገሬን ሲያይ አንተ የመጀመሪያው ነህ»



«ሁላችሁም ውሸታሞች ናችሁ:: ማለቴ እናንተ»

«ሴቶች ማለትህ ነው?»

«አይደለም እናንተ . . . .» እጁን በንቀት አወዛወዘ:: ገባኝ ሊል የፈለገው:: በአካሉ ሊያቆስለኝ የተዘጋጀው ሳያንሰው በቃላቶቹ ሊቀቅለኝ ነው ማለት ነው::

«ቶሎ መሄድ እፈልጋለሁ»

«እኔም ብዙ እንድትቆይልኝ አልፈቅድም:: የማዝሽን ነገር በትክክል ፈፅሚ!»

«ፈገግ በይ! »

«እሺ» ሙዚቃ ከፈተ::

«ከወገብሽ በታች ተወዛወዢ»

ፊልም የምሰራ መሰለኝ:: ከወገቤ በታች በደንብ ተወዛወዝኩ:: ይህን ያህል መወዛወዝ መቻሌን እስከዛሬ አላውቅም ነበር::

ከራስ ቅሉ እና ፊት አንገቱ በቀር መላ አካሉ ፀጉር ብቻ ነው:: ይህ ሁላ የፀጉር ሀብት ከወደ አናቱ የማነሱ ጉዳይ አስገራሚ ሆነብኝ:: እርግጠኛ ነኝ የደረቱ ጥቅጥቅ ፀጉር ለአናቱ እንዲያደርግለት አማር ፀልይዋል:: 'ቆጥራ' ሲያደርግ የሸፈነውን በረሃ ጭንቅላቱን አሁን ገልጦት ከመጀመሪያው ግምቱ በዕድሜው አስር ዓመት ጨመረብኝ::

«ሳሚኝ!»

ልስመው ካለበት አጐነበስኩ::

«ላ . . .ላ» ተስፈንጥሮ ተነሳ::

አፋን ቶሎ ቶሎ ጠረገ:: ሁኔታው የመረረውን እሬት አፋን የቀቡት ያስመስለዋል:: አኳኋኑ ልቤን ሰበረው:: በጣም ጐዳኝ:: ከንፈሩን መሳሚ ይህን ሁሉ ነገር አስከተለ::

«ከንፈሬን ማን ሳሚኝ አለሽ . . . ቱ» ደጋግሞ በመጠየፍ ተፋ::

«ይቅርታ» አልኩ:: እንባዬ ጉንጩን አቀዘቀዘው:: መቼ እንዳነባሁት አላወቅኩም::

«ከዚህ ጀምረሽ . . .» ከአንገቱ በታች እየወረደ በምልክት አሳየኝ::

ያለቀውን ትዕግስቴን ባዶ በሆነው ማቀዝቀዣ፣ የምግብ መደርደሪያ እና የቤት ክራይ ክፈይ በሚለው የአከራዬ ድምፅ አበረታሁት:: የቤት ክራይ መክፈል አለብኝ::

ደረቱን . . . እጁን . . . አንገቱን . . . እየቀፈፈኝ ሳምኩ::

«እንደሱ አይደለም በፍላጐት ባህር ግቢ ይህንን ገላ ስትስሚ ገባሽ!»



ጥሩ ሀሳብ መጣልኝ . . . ዩስሪ:: ውበቱን ናፍቄአለሁ:: አይኔን ጨፈንኩና አሰብኩት:: ከዩስሪ ጋር ሆንኩ:: ዩስሪን ዳበስኩ ዩስሪን ሳምኩ::

«ውረጅ አዎን ወደ ታች» ትዕዛዝ ከዩስሪ አነቃኝ:: የሰማሁትን ማመን አቃተኝ:: ውስጤም ድንገተኛውን ትዕዛዝ መቋቋም ተስኖት ከሆዴ ያለውን ሁሉ የሰውዬው ደረት ላይ ለቀቅኩት::

ሰውዬው ወደባኞ ቤት ሲሮጥ እኔ ቶሎ ብዬ ለበስኩና ተንደርድሬ ወጣሁ::

በነጋታው ቦርሳ የተገዛበት ሱቅ ሄጄ

ካንድ ቀበጥ ወይዘሮ የሚጠበቅ እመቤታዊ አባባል ተጠቅሚ የቦርሳውን ሙሉ ክፍያ ተቀበልኩ::

«እንዴት የአሜሪካ ቦርሳ ትሰጠኛለህ:: እኔ የወሰድኩት የፓሪስ መስሎኝ ነበር» የሚል:: የቤት ክራይ ከፈልኩ:: የዚያች የሚጢጢ ቦርሳ ዋጋ ለአስራ አምስት ቀን ያህል ቁርስ ደህና ምሳና ቀላል እራት ትችልልኛለች . . . . እፎይ::

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ዛሬ ከቅድስት ፊት ስቆም አይሻ ያለችው ትዝ አለኝ::

«እኔ ቅድስት ፊት ስቆም ህሊናዬ ፊት የቆምኩ ይመስለኛል:: ስለዚህ አይኗን እንኳን አተኩሮ ማየት ያስፈራኛል:: ስለዚህ አይኗን እሸሻለሁ ልክ ህሊናዬን እንደሸሸሁ ሁሉ» ብላ ያለችው:: እነ አይሻ ቅድስትን ለምን እንደሚፈሯት አሁን ገባኝ::

ለሰላምታዋ ተንተባተብኩ:: በናፍቆት አቅፋ ሳመችኝ::

«እ! ምን አዲስ ነገር አለ?» በአይኗ የሳባን ሻንጣ እያማተረች::

« . . . . ሰባህን ጠረኳት::»

ትንሽ ትክዝ አለች:: ግን ምንም አዲስ ነገር አይደለም:: ብዙ ሰዎች ሳያስቡ ወደ አገራቸው ይላካሉ:: የተለመደ ነው::

«ምንም አትሆን:: በደንብ ቀጥ ብላ ሰርታለች:: ታውቂያለሽ?! እንደውም እግዜር ሲያድናት ነው:: ወደ መጨረሻ ሁኔታዋ አላምር ብሎኝ ነበር:: ስራ ሰለቸኝ አስጠላኝ እያለች ልትቀየር እየወላወለች ነበር:: ከምትበላሽ በሰላም አገሯ መግባት ይሻላታል:: አንቺስ ስራ አገኘሽ?»

እራሴን በአሉታ ነቀነቅኩ:: ይበልጥ ቀርባ ተቀመጠችና «አይዞሽ እናገኝልሻለን . . . አ . . አ» አለች የሆነ ነገር እንዳስታወሰች ዓይነት::



«ሰባህ ከሄደችስንት ጊዜ ሆናት?»

«አንቺ ደማም በሄድሽ በአራት ቀንሽ [illegible] ውስጥ የያዟት:: ለዘመዶቿ ደውላ ሻንጣዋን መጥተው ወሰዱላት»

«ታዲያ እስካሁን የቤቱ ኪራይ አ . ል . . . ተከፈለም?»

«ከፍዬዋለሁ»

«ወርቁን ሸጥኩ እንዳትይኝ?»

«አልሸጥኩም»

«አ . . .» አይኗን አፍጣ በጥርጣሬ

«እነሳልዋ መጥተው ነበር? ከነርሱ ጋር ሄድሽ?» ትከሻዬን ይዛ ወዘወዘችኝ:: «እረ ሰው የሚባል አልመጣም?»

«ታዲያ ገንዘቡን ከየት አመጣሽ እውነቱን ንገሪኝ»

«ምን ለውጥ ሊያመጣ» አንገቴን ደፋሁ::

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ላገባ መወሰኔን እነአይሻ ሲሰሙ «ገና ካሁኑ ልትታጠሪ ነው» ብለው

«ታጠረች አሉ በትዳር . . .» የሚለውን ዘፈን እያጨበጨቡ ዘፈኑልኝ::

አስመሮም መጀመሪያ ያየኝ የቅድስት ዘመድ ቤት ስሰራ ነበር:: ብዙ አላወራንም:: እርሱ ግን ጥሩ አድርጐ ሳያስተውለኝ አልቀረም:: እንደሌሎች ለጓደኝነት ሳይሆን ለጋብቻ ስለጠየቀኝ ደስ ብሎኛል:: ትዳር እዚህ አገር እንደማይጥም ባውቅም አንድ ቀን የሚያማምሩ ልጆቼን ይዤ አገሬ እገባለሁ:: ደግሞም ፍቅር ከተጋባን በኋላ ሊመጣ ይችል ይሆናል ብዬ አመንኩ:: እርሱም በዛ ያመነ ይመስላል:: እሰራባት የነበረችው አበሻ ሴትም ስለ እሱ ስታወራ ሁሌ ጥሩነቱን ታወሳ ነበር:: ትልቁና ዋናው ነገር ያገሬ ልጅ ነው::

ሁለተኛው ለጋብቻ መስማማቴን ቶሎ ያጠነከርኩበት ጉዳይ የፈራሁት ነይ እያለ የሚጐተጉተኝን አሳሳች መንገድ ለማምለጥ ነው:: በቀደም ተሳስቼ ወጥቼ ያን ቦርሳ የገዛልኝ ሰው ጋ የደረሰብኝ እንዲደገም አልፈልግም:: ስራ መስራቱም በጣም አስጠልቶኛል:: ስለዚህ አግብቼ አዲስ ህይወት ቢኖረኝ አይከፋም:: ይህ ትዳር ከአሳሳቹ መንገድ ያድነኛል:: ቤተሰብ መስርቼ ከባሌ ጋር ሆነን አገራችን መግባቱ ትልቅ እድል ይሆነኛል:: ቁጭ ብለን ስለቤተሰባችን ስናወራ ስበሳጭ ሳዝን በጥብቅ እቅፉ ተስፋን እንዲሰጠኝ ብቸኝነቱን ጥሶ አብሮኝ እንዲሆን ባል ማግባት መረጥኩ::

አስመሮም ስራው ሽፋጥ ነው:: ሽፋጥ የሚለው ቃል መሽፈጥ ከሚለው አረብኛ የተወሰደ ነው:: ሽፋጣ



የሚባሉት እዚህ አገር በሽንት ቤት መጣጭ መኪኖች በሹፌርነት ወይም በባለቤትነት የሚሰሩ ናቸው:: ታዲያ እዚህ ያለ ሀበሻ ወንድ ዘጠና አምስት በመቶ በዚህ ስራ የተሰማራ ነው:: ላገባው ያሰብኩት ሰው ታዲያ የሽንት ቤት መጣጭ መኪና ባለቤት ነው:: እናም ሽፋጣ አለው ከተባለ ሀብታም ነው ማለት ነው:: የሰርጌን ምክንያት በደንብ ያወቀች ቅድስት ብቻ ናት::

«እኔ አስመሮምን ለምን ልታገቢ እንዳሰብሽ አውቃለሁ አዕምሮሽ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሊያስላስል የፈለገውን ነገር እንዳያስብ አስመሮም ጆርባ ልትሸሸጊ ነው:: እራስሽን ሸጠሽ ስራ ጠልተሽ በቀላሉ ገንዘብ ልታገኚ የምትችይበትን መንገድ ፈልገሻል:: ግን ደግሞ ያን እንዳታደርጊ የሚከለክልሽ ከባድ እንቅፋት በመፍጠር እራስሽን ከዚህ ሀሳብ ትገላግያለሽ:: እመኚኝ ይህ ጥረትሽ ላሁኑ ሁኔታሽ ለጊዜው መከላከያ ይሆንሽ ይሆናል:: ግን ወደፊት አንድ እኩይ ሀሳብ በመጣልሽ ቁጥር ከራስሽ ሀሳብ ለመሸሽ ጠንካራ ምክንያት ስትሺ መኖር እንዴት ትችያለሽ:: ለምሳሌ አንድ ሰው ለመግደል አስበሽ ግን ደግሞ ያን ሰው ላለመግደል መልአክ መጥቶ «ተይ አትግደይ» ብሎ እንዲያግድሽ ትመኛለሽ:: ለምን ከራስሽ ጋር አትስማሚም!? ለምን ራስሽን ይህ አይሆንም ብለሽ አሳምነሽ ጠንካራ ውሳኔ አትወስጅም? እናም የፈራሽውን የነአይሻን መንገድ ላለመቀበል የምትከላከይው ሙሽራ ሆነሽ ነው? ትገርሚያለሽ! ፈሪዋ ሙሽራ! ቦቅቧቃ ነሽ! ጠንካራ አይደለሽም እኔ እንደምገምትሽ! እንዴት ሰው የገዛ ሀሳቡን ይፈራል::» አለችኝ:: ቅድስት የዋዛ አይደለችም::

የሰርጉ ቀን ተፋጠነ:: ከድግሱ በፊት የሚፈረም የጋብቻ ውል አለ:: አስመሮም ከሽማግሌዎች ጋር እያለን የጋብቻ ውሉ ጮክ ተብሎ እንዲነበብ ጠየቀ:: የጋብቻ ውሉን የፃፈው እራሱ መሆን አለበት::

«የሕይወት ጓደኛዬን ከመምረጤ በፊት ያፈራሁት ንብረትም ሆነ እርሷ እኔን ከመምረጧ በፊት ያፈራችው ንብረትም ሆነ ገንዘብ ከጋብቻችን ውጭ ሆኖ አብረን በሆንበት ጊዜ ብቻ የምናፈራው ገንዘብ በሁለታችን እኩል የሆነ ንብረትነት እንዲኖረው ይቀል ዘንድ የራሴን ንብረት በእንዲህ ሁኔታ ስዘረዝር የእርሷንም በሽማግሌ ፊት እንድትዘረዝርልኝ በትህትና እጠይቃለሁ::

የኔ አነስተኛ ተመኗ አርባ ሺ ሪያል የሆነ የቤት መኪና በባንክ . . . .

ንብረቱን መዘርዘር ቀጠለ:: በእውነቱ ንብረቱን አባዝቶ ስለካልሲው ሁላ የሚናገር ሰው ሳይሆን አይቀርም:: እኔ ኑሮን ፈርቼ ሕይወቴን ሕልሜን እርሱው እንደፈለገ እንዲያንቀሳቅስ ልፈቅድለት ስዘጋጅ እርሱ በንብረቱ ጠረጠረኝ::

እዛው በሽማግሌዎች ፊት ጋብቻዬን መሰረዜን አስታወቅኩ::

* * * * * *



ከዚያን ቀን በኋላ የቅድስት ምክር ጭቅጨቃ ሆነና እየሰለቸኝ መጣ:: ስንት አጠያይቃ ያመጣችልኝን ስራ ደክሞኛል ብዬ ሳልቀበለው ቀረሁ::

በዚህ መሀል ወደ መረጥኩት የህይወት መንገድ ይበልጥ የሚያበረታኝ ወሬ ዱብ አለ::

ጀሚላ ለቅድስት ስራዋ ቦታ ደውላ ጥሩ ቦታ ማግኘቷንና ከነአይሻ ጋር የነበረች ጊዜ የነበራትን ፍሪጅና ልብሶቿን ሁሉ ነገሯን ለሳልዋና አይሻ እኩል እንዲካፈሉ ብላ መልዕክት ነገረቻት::

እኔና ቅድስት መልዕክቱን ለነ አይሻ ልንነግር የሄድን ጊዜ የጀሚላን ቦታ ለመተካት ሀሳብ መጣልኝ::

በዚያ ሰሞን የጀሚላ ሁኔታ በጣም ያስገረማት ሳልዋ ወሬ ለማጠናከር የአበሻ ፀጉር ሰሪዋ ቤት ሄዳ ብዙ ብዙ ወሬ ይዛልን መጣች::

«ስለ ፀጉር ሰሪዋ ሴት እንዴት ሀሳብ መጣልሽ?» አልኳት ገርሞኝ::

«በጅዳ ውስጥ የምናውቃት ፀጉር ሰሪ እርሷ ብቻ ነች:: በምትሰራሽ ወቅት ብዙ ታስለፈልፍሻለች:: ስለዚህ እንዳለችው ጥሩ ቦታና ገንዘብ ካገኘች ፀጉሯን ለማስዋብ ፀጉር ቤት ብቅ ማለቷ አይቀርም:: የአረቦቹ ፀጉር ቤት ልሥራ ብትል ፀጉሯን ይበልጥ አከርድደው አቁመው ነው የሚልኳት:: የአበሻ ፀጉር ፀባይን የምታውቀው እዚች ፀጉር ቤት ጋ መምጣቷ አይቀርም:: በወሬ የምታጣድፈዋ

ፀጉር ሰሪ ጀሚላ የእኛ ጓደኛ እንደሆነች ታውቃለች። ስለዚህ ስለ ጀሚላ ከፀጉር ሰሪዋ የሆነ ወሬ እንደማገኝ እግጠኛ ሆኜ ነበር የሄድኩት። ይገርምሻል ስለጀሚላ ልታወራልኝ ገና ስታየኝ የምታጥባትን ልጅ ገፋ አድርጋ እጇን እያደረቀች በምልክት ጠራችኝ።»

«አ! ጀሚላ መጥታ ነበር። ባንዴ ተመነጠቃችሁ አይደል። ተሳካ ውጥኑ!. . . ሰው እንዲህ ባንዴ ይለወጣል . . . ሹፌሯን ከበር አቁማ . . . የእጅ ሞባይል ስልኳን ይዛ እመቤት ሆናለች . . . » አለችኝ።

«ስልኳ የእርሷ ባ፤ ያንስ?»

«የራሷ ነው ታስታውቃለች። በዚህ ወር ብቻ አምስት ጊዜ ፀጉሯን ተሰርታለች። ፀጉሯን ብቻ መሰለሽ?! ጥፍሯንም ተረከዟንም . . . ደግሞም የባኞ ውድ ዘይት አድርገንላት እንፋሎት ካስክ ውስጥ ገባች። የእንፋሎት ካስክ ከገዛሁ የመጀመሪያዋ አበሻ ተጠቃሚ ሆነች። እስካሁን ማንም አበሻ ሴት ይህን ካስክ ደፍራ አትጠቀምም። ዋጋው ውድ ስለሆነ!።» ብላ ትንፋሽ እያጠራት ስለጀሚላ ሀብታምነት ማስረጃ ሰጠችኝ። እርግጠኛ ነኝ ከአንድ 'አሚር' /የንጉስ ዘር/ ጋር ናት ያለችው። ምን ያረጋል ታዲያ ወንዷን እንዳንሰርቃት እራቀችን።»

«ወንዷን እንዳትሰርቋት?!» አልኩ



«እ . ሀ . ሀ አዎን» ሳቀችና ሳልዋ ቀጠለች «ግን እውነቷን ነው። አንድ ጊዜ አይሻ ምን አደረገቻት መሰለሽ?! ከሆነ አመዳም አረብ ጋር ጀሚላ ትዋዋልና ቀንና ሰዓት ብቻ ተነጋግራ እቤት ያደርሳትና ይሄዳል። ሰውዬው ቀደም ብሎ ሲመጣ አይሻ በር ከፍታ የሆነ ነገር ትለውና ተመልሶ ይሄዳል። ጀሚላ ተሰናድታ ሰውዬውን ብትጠብቅ ብትጠብቅ ሰውዬው ሳይመጣ ቀረ። ከዛ ብዙ ቆይቶ በድንገት ጀሚላ ሰውዬው አይሻን እቤት ሲያደርሳት ታያለች . . . . ውው . . .ውውው! ብታይ ሊባሉ ነበር። ከዚያ ጀሚላ ማለች ጥሩ ወንድ ስትይዝ ፊፅማ ሳትገናኘን . . . አትገርምም?! ጥሩ ናት ለማንኛውም።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ሳምንቱን ሙሉ ሳሰላስል ሳሰላስል ሰነበትኩ:: ለቅድስት አነስ ያለች ማስታወሻ ፅፌላት ሻንጣዬን ይዤ ወጣሁ::

እነሳልዋ ቤት ስደርስ ሳልዋ በሙሉ ልቧ ተቀበለችኝ:: አይሻ ሻንጣዬን ተሸክማ አስገባች::

«የጀሚላን ቦታ አገኘ ይሆን?»

«ምንግዜም!» አለች ሳልዋ በእንግሊዘኛ::

አይሻ የግብፅ አረቦች በጣም የሚወዱት ሰው አቤታቸው ሊጠጋ ሲጠይቃቸው የሚጠቀሙበትን ልባዊ አነጋገር ተጠቀመች::

«ለማሼሌቲክ አርድ ንሺሊክ ጉዋ ዓይንና /መሬት እልኸም ብትልሽ እንኳን እኛ አይናችን ውስጥ እናስቀምጥሻለን/::»

አቀባበላቸው ደስ አለኝ:: ለምን እንደመጣሁ አልጠየቁም? ግን አውቀውታል:: ቅድስትን አሸነፉ:: በነጋታው ስናወራ ስለዩስሪ አወራሁላቸው::

ሳልዋ በቁጭት እራሷን ነቅንቃ «ትዝ ይልሻል እኛንና አንቺን ያጣላው ያ ዱባ አረብ ቅድስትም የተቅየመችንና ለረጅም ጊዜ እቤቴ እንዳትደርሱ ያስባላት



ጉዳይ ትዝ ይልሻል? ያን የምነግርሽ ጥሩ ጊዜ አሁን ነው:: አሁን አንቺም የኑሮ ሁኔታ በደንብ ስለገባሽ ይቅርታ ሳታደርጊልን አትቀሪም:: እኔ ግን አውቅ ነበር . . . የሆነ አረብ አታሎ ክብርሽን እንደሚወስድ . . . ይህ የተለመደ ሆኗል ለእኛ:: ታዲያ ያ መሆኑ አይቀር ብትጠቀሚበት ይሻል ነበር:: እኔ ተዋውዬልሽ የነበረው አረብ ለክብርሽ ብዙ ይከፍልሽ ነበር:: በዛ ብር ብቻ አገርሽ ትገቢ ነበር:: አየሽ ነገ የተቀመጠልንን አናውቅም:: ህይወትሽ በተለይ በስደት እንደፈለግሻት አትሄድም:: ፍቅር . . . ፍቅር ብለሽ ምን ላይ ደረስሽ? እ!:: እኔ ያመጣሁልሽን ዱባ ብትከትፊ ግን ይሄኔ ዱቢኖ ትሆኚ ነበር:: ይህን የተከፋ ፊትሽን ዛሬ አላይም ነበር:: እኛ በተወለድንበት ዘመን ላንቺ አይነቷ ቡቡ ቦታ የለውም:: በዚህ ዘመን ሁሉም ነገር በተመን ነው:: የምታገኚው ነገር በተመን እንደሆነ ሁሉ የምትሰጪው ነገርም በተመን መሆን አለበት:: ፍቅርም ቢሆን እንኳ በተመን:: እኔ ገና ሳይሽ ህይወት እንደምታደክምሽ ገምቼአለሁ:: እንደነገርኩሽ ይህች አለም እንዳንቺ ቡቡ የዋህ ለፍቅር ብርግድ ብሎ የተከፈተ ልብ ላለው አትሆንም:: ልምክርሽ አንቺ ካሁን ወዲያ ራሷን ልትከላከል የምትችል ቁጡ ድመት መሆን መቻል አለብሽ:: ለፍቅር ብለሽ ያለተመን የሰጠሽው አረብ በነፃ የሰጠሽው ፍቅር አይጥመውም:: እነርሱ እንደዚያ ናቸው:: ምን ያህል ነች ለኔ አይደለም ጥያቄአቸው ምን ያህል አወጣሁላት ነው:: ይህ ነው ፍቅር እዚህ አገር:: ተለወጪ!»

እኔ ግን በግልፅ ከዩስሪ ጋር ያሳለፍኩትን ወራት እንደማልፀፀትበት ስነግራቸው ሁለቱም ልባቸውን ይዘው ቀለዱብኝ «ልቤን! ልቤን! » እያሉ።

እኔም ቀልዳቸውን በቀልድ ስመልስ

«ገልቢ ዳ ምሽ ሙትአድብ! በስ አነ አርፍ እዘይ አረቢ! /ይህ ልቤ አደብ የለውም እኔ ግን እንዴ እንደማድበው አውቃለሁ/» አልኳቸው በአረብኛ። እነ አይሻ ልባቸውን ለቀው ልቤን እየያዙ

«ትረቢ አልቢክ? /ልብሽን ልታድቢ?/» አሉኝ። ከዛ በኋላ ግን አይሻ በቁም ነገር ተከሳትራ « ዱሲ አለ አልቢክ አቅሊክ ቢከፊኪ /ልብሽን እርገጪው አዕምሮሽ ብቻ ይበቃሻል/ አለች።

ሳልዋ በተራዋ «አነ አኡሊክ ዱሲ ኢትፊን አልቢክ ወአቅሊክ/ እኔ የምልሽ ደግሞ ሁለቱንም ዋጋ የላቸውም እዚህ አገር። ባዶ መሆኑ ያዋጣል። ያለ ልብ ያለ አዕምሮ» አለች። የተማረች ትመስላለች።

አይሻ «አትስሚያት! አዕምሮ አስፈላጊ ነው። ግን ላንቺ ብቻ የሚፈርደው አይነት መሆን አለበት። ሁለተኛውን አዕምሮ ለእውነት የሚቆመውን ይህ ስራሽ ስህተት ነው ቀጥ በይ ብሎ ሊያቃና የሚሞክረውን የሚገስፀውን የሚፀፀተውን አዕምሮሽን ግን እርሺው!» አለችና ንግግሯን ደመደመች። እኔም ስለሁለቱቱ አዕምሮዎች እያሰላሰልኩ ወደ አልጋዬ ሄድኩ። ለነገሩ እኔ የነበረኝ አንድ አዕምሮ ነበር። አሁን በቅርቡ ደግሞ ሌላኛውን ተረከብኩ። ስለዚህ የአይሻ አባባል በደንብ ገብቶኛል።

እነ አይሻ እንዳሉት ለለውጤ የመጀመሪያ እርምጃ እነርሱን በተስፋ የምትሞላ ቻድአዊት ጠንቋይ ጋር መሄድ ነበር ደስ ሳይለኝ ተስማማሁ

አስደንጋጩን ትዕይንት አየሁ ቻዳዊቷ ጠንቋይ ጋ ቀይ ብርሃን፣ ቀያይ የለበሱ ሰዎች የሚያፍን ጭስ የሚዘገንን ድምፅ የከበሮ ድም ድም-ታ ድው ድው ዳ . . . . ዙሪያውን ተደርድረው በስልት በከበሮዋና በዕልልታው አመታት ቀና ጉንበስ ቀና እያሉ ይናጣሉ። መጨረሻ ላይ አንዷ ጧ ብላ ተዘረጋች። ጠንቋይዋ የማይገባ ቋንቋ ለፈለፈችና ዶሮ አርዳ ደሟን የወደቀችዋን ሴት ለቀለቀች። የሴትዬዋም ሆነ የሰዎቹ መልክ አያስታውቅም። ቀዩ መብራት መልካቸውን ብዥ አድርጎብኝ ነበር። ጠንቋይዋ ቤት ባዩት ነገር በተመስጦ ሌላ አለም ውስጥ የገቡትን ጓደኞቼን በአግርሞት አስተዋልኩ። ስለጠንቋይዋ ያለኝን አስተያየት ዋጥ አደረግኩ።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

አይሻ ያመጣችልኝን አዲሱ ስራዬን ባንድ ስነስርአት ፊዕሞ ባልፈጠረበት ወንድ ጀመርኩ።

አብሬው አልጋ ውስጥ እያለ ለሚስቱ ደውሎ ማውራት ጀመረ:: ገላዬን ጨመቅ እያደረገ ሚስቱ ላይ ይቀልዳል:: እኔ ላይም . . . አኳኋኑ ቢያስጠላም ተናድጄ ጠዋት የማገኘውን ብር ላለማጣት እራሴን ተቆጣጥሬ ዝም አልኩ:: ደስ ላሰኘው ፈገግ አልኩለት:: አስተያየቴ «ጀግና ነህ! በሴቶች የምትጫወት ጀግና!» እንዲለው ፈለግኩ:: እርሱም ያን ማወቅ ሳያኮራው አይቀርም:: ለሚስቱ 'ያ አዩኒ አነ ያ ሀያቲ /የኔ ሕይወት/' እያለ የፍቅር ወሬውን አደራ:: እቤት እንጼት ውሸታም ነው:: ቢያንስ የሌላ ሴት ገላ ታቅፏል::

በጣም የተቀራረበው ገላችን የመታከት ምልክት ችፍፍ አደረገ:: ነጭ ገላው አስጠላኝ:: ብቻ የኔንም ጥቁር ገላ ንቋል:: ስልኩን ዘጋና በአረብኛ «እኔ ስልክ ከሚስቴ ጋር ሳወራ ምን ያስገለፍጥሻል» አለኝ:: ክው ስላልኩ መልስ አጣሁለት:: ንግግሩን ቀጥሏል «ይኼኔ ነጠቅኳት እያልሽ ደስ ብሎሽ ይሆናል እኮ!:: ከሚስቴ እግር እጣቢ አትደርሽም:: ሽርሙጣ!» ብሎ በጥፊ አላሰኝ:: የሁኔታው ዳር ዳሩ ገባኝ:: መለያያችን ስለደረሰ ክፍያ ሊከለክለኝ የጠነሰሰው ጥንስስ ነው:: ጥፊው ተጨምሮልኝ ምንም ሳላገኝ እንገቴን ሰብሬ እቤት ተመለስኩ::

እነ አይሻ በዚህ መንገድ ከሚደርሰው መጥፎ እድል አንዱ እንደሆነ ነገሩኝ:: ለዚያውም ቀላሉ ነው:: ብቻ ለሁለተኛው እድልሽ ፀልይ አሉኝ እንደቀላል::

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋



ቅመማ ቅመሙ ብዙ አይነት ነው:: ሽታውም ይሰነፍጣል:: ከመሀላቸው የተላጡ ጥውልግ ነጭ ሽንኩርቶች አሉ:: ትልቁን ቢጫ የድንጋይ ቁራጭ በጣም አየሁት:: የሚሸተውንም ሽታ አስታወስኩ . . . . . ድኝ::

ትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ 'ሰልፈር' ብለን በተግባራዊ የኬሚስትሪ ትምህርት ሰዓት እንማርበት የነበረ ግማታም ድንጋይ . . . . ድኝ::

አይሻና ሳልዋ ይከራከራሉ::

«ሴትዬዋ ያለችው ፊጭተሽ በጥብጠሽ የሰው ትንፋሽ በማይዘርበት አስቀምጪውና ጠዋት አንድ ብርጭቆ በባዶ ሆድሽ በግራ ጉንጭሽ ብቻ ፊሳሹ እንዲያልፍ አድርገሽ ትጠጪና በቀኝ ጥርሶችሽ ምግብሽን ትወስጂአለሽ:: በግራ ጉንሽ መተኛት መጀመር አለብሽ:: የመገላበጥ ልማድ ካለሽ አንድ ሰው እንዲያስርሽ አድርጊ:: ብቻሽን ተኚ:: እራቁትሽን ሰው እንዳያይሽ:: ከቤት በፍፁም እንዳትወጪ . . . . ነው ያለችሽ::» ስትል አይሻ

ሳልዋ በተራዋ «በደንብ ሰምቼአታለሁ አረብኛው ተዘባርቆብሻል ማለት ነው:: ጠዋትም ማታም እንድጠጣ ነው የነገረችኝ::»

ስለማ ንግግር እንደሚያወሩ በደንብ ገብቶኛል . . . ስለዚያች የቻድ ጠንቋይ ነው::

በመሀል ገብቼ «ሳልዋ እኔ ያችን ቻድ አላምናትም:: እስከዛሬ ያለችው ነገር ምንም አልደረሰም

ብላ ብላ መርዝ ትሰጥሽ ጀመር:: ድኝ ልትጠጪ ነው? ሌሎቹ ዘሮች ደግሞ የምን ዘር እንደሆኑ አይታወቁም:: እባክሽን እራስሽ ይህንን አታድርጊ:: አይሻ ከልክያት!»

ሳልዋ ጮኸችብኝ «አፍሽን ያዝ:: አትነጂሽኝ::

አንደኛዋ አይነ ጥላዬ አንቺ ነሽ::»

ሳቅኩኝና «ታዲያ እኔ አይነ ጥላሽ ከሆንኩ እኔ ልሂድ ከፊትሽ ልጥፋ:: ይህንን መርዝ ግን አትጠጪ»

አይሻ መርዝ በማለቴ ተቆጣች::

«ቡዳ! ስለማታውቂው ነገር አታውሪ::» አለችኝ:: ዛሬም ቀይ ብልጭልጭ ስስ ልብስ እንደለበሰች ከባድ አጣናማ ቡናዋን አዘጋጅታለች::

እራሴን ከእነርሱ አንዷ አድርጊ ብቆጥርም ይህ እምነታቸው ያስፈራኛል:: ያች የቻድ ጠንቋይም እንደማትወደኝ አውቃለሁ:: በጣም ስላመኗት እነቂት ብትላቸው ሳያውቁት በመንፈስ ብቻ ያንቁኛል ብዬም አንዳንዴ እሰጋለሁ:: እርሷም የኔን ብቻ ሳይቀር ሁሉንም ነገር ስለኛ ታውቃለች:: ስለ እርሷ ያለኝ አመለካከት በየጊዜው ለሚፈጠረው ግጭት ዋናው መንስኤ ነው::

ለኪራይ ያዋጣሁት ገንዘብ ስላላለቀ ደስ ሳልላቸው አስቀምጠውኛል:: እኔም የየቀኑ የቡና ዝግጅት የራስ ምታቴን እየጨመረው ስለመጣ አዲስ ቤት ለመከራየት የአፓርትማ ዘበኞችን አጠያይቄ በቅርቡ ሊያስረክበኝ ቃል የገባልኝ ስላለ ግንኙነታችን እንደሚያበቃ አውቃለሁ::



አይሻ ቀጠሮ የነበረባት ሌሊት ሳልዋ እርዳታዬን ጠየቀች::

«እምነታችንን ስለጠላሽ እውነቱን ነው የምልሽ በአባባልሽ እንጂ አንቺን ጠልቼ አላውቅም:: እንደውም ታሳዝኚኛለሽ:: ለምን እንደሆነ እኔንጃ:: አመለካከታችን ስለማይመሳሰል አንድ ላይ መኖር ባንችልም በስደት ስለተገናኘን ለመደጋገፍ እህትማማቾች እንደሆንን አትርሺ:: የሆነ ችግር ሲያጋጥምሽ ከጉንሽ ነኝ:: አትቀየሚኝ:: ቤት አገኘሽ አሉ!»

«አዎን . . . አዎን:: ግን አንቺ ዛሬ ምን ሆነሻል ፊትሽ ላብ በላብ ሆኖአል::»

«ከነገርኩሽ ያው የተለመደ ጥላችን ላይ እንመጣለን:: ነገሩ የቻድ . . . »

«አወቅኩት:: ብቻ ያን ነገር ጠጣሁ እንዳትይኝ!»

ሳልዋ አይኗ በእንባ ግጥም አለ::

«ምን ላድርግ?! ሁሉም ወንዶች ይጠቀሙብኝና ሳንቲም አይሰጡኝም:: መጀመሪያ ያጋጣሚ ጉዳይ መስሎኝ ነበር:: በኋላ ግን ጉዱን የቻዷ አዋቂ ነገረችኝ:: ታውቂያለሽ! ወንዶች ይወዱኛል:: እንዳለችኝ ከሆነ የሌሊት ንግስታቸው ነኝ:: እኔን በማየት ብቻ አካላቸው ይወራጫል:: ይህ ዓይነ ጥላዬ ግን በነጋታው እንዲጠሉኝ ያደርጋቸዋል:: ለሊቱን ደህና አሳልፌው ጠዋት ያለምንም ገንዘብ እንደውሻ ያባርሩኛል:: ተሳስቶ እንኳን ለሁለተኛ

ግንኙነት የጠየቀኝ የለም:: አይነጥላ መሆኑን ሳላውቅ በዕድሌ ብዙ አልቅሻለሁ:: አሁን ግን በሚቀጥለው ሳምንት ያ ሁላ አብቅቶ እድሌ ይጠራል:: ድፍርሱ እድሌ ሲጠራ ገንዘብ አፍሳለሁ:: ይታየኛል ይህ ፈውስ አይነጥላዬን አንስቶ በምትኩ ስጧት የሚለውን ይተካልኛል:: በትንሽ ጊዜ ውስጥ ሀብታም እሆናለሁ:: ገንዘብ ሁሉም ነገር ነው:: በገንዘቤ የፈለግኩትን ሁላ በእጄ አደርጋለሁ:: ሀይለኛ እሆናለሁ::» በላብ የተጠመቀ እጇን ጨበጥ ፈታ እያደረገች::

« ሳልዋ . . . . መድሐኒቱ እየጐዳሽ ነው:: ወተት ላምጣልሽ?»

«አይ ወተት አይወድም:: መጀመሪያ አካባቢ እንዲህ እንደሚያደርግ ነግራኛለች:: ትንሽ እየቆየ እየባሰ ይሄድና በሙሉ ሀይሉ ችግሬን ከፈነገለ በኋላ ደህና እሆናለሁ:: መድሐኒቱና መጥፎው መንፈስ እየተጣሉ ነው::» ድምፅዋን አንሾካሾከ:: በፈገግታ ስታየኝ ቆየችና «በጣም ጥሩ ነሽ::» አለችኝ በምስጋና እንገቴን ወዘወዝኩ::

«ዛሬ አይሻ ቀጠሮ ስላለባት ከአልጋ ጋር እንድታስሪኝ ነው የጠራሁሽ:: በዚህ ገመድ ጥፍር አድርገሽ እሰሪኝ:: በቀኝ ጐኔ እንድተኛ አይፈቀድልኝም::

ሳቅኩኝ:: «ተይ እንጂ እኔ በጣም እንቅልፋም ነኝ ለሊቱን ሽንትሽ ቢወጥርሽ እንዴት ልታደርጊ ነው?»

እውነቱን ለመናገር ሁኔታዋ ደስ ስላላለኝ ሌሊቱን እየተነሳሁ ሳያት አደርኩ::



በነጋታው ሞቅ ባለ የቡና ጭስ ተነቃቃን:: አይሻ በደማቅ ፈገግታ ተሞልታለች:: ቀንቶአል ማለት ነው::

«አሻገረኝ! ቀላል ደማልኝ? በጣም ሙዲ እያለ አጋጠመኝ ዋው . . . » ሳልዋን አቀፈቻት::

ወደ እኔ ዞር አለችና «ይቅርታ የኔ ቡዳ! ያኮረፍሽ ትመስያለሽ ላቅፍሽ እችላለሁ?

ሁለት እጄን ዘረጋሁላት . . . . በሙሉ ሀይሏ ተጠመጠመችብኝ::

«ልንግባባ እንጣር:: እኔ ዛሬ ደህና ክፍያ አግኝቻለሁ:: ግማሹን ለቤተሰቦቼ እልክና በግማሹ የቤት ክራይ ልንቀጥል እንችላለን:: ለምግባችንም አናጣም እባክሽ አትለይን! እንወድሻለን እ . . . ይቅርታ አድርጊልኝ»

በሚቀጥለው ሌሊት ሳልዋ እንደታሰረች በጣም ታቃስት ጀመር:: ነቅቼ ፈታኋት:: አይሻ የትናንትና ድካሟ ስላለቀቃት ሞቅ ያለ እንቅልፍ ላይ ነበረች::

«ሳልዋ ዛሬም ያን ጠጣሽ ደግመሽ?»

«ሁለት ቀናት ይቀሩኛል::»

«ወይኔ! ብሶብሻል እኮ ፊትሽ ተለውጧል::

በጣም ፈራሁልሽ አይሻን ልቀስቅሳት::»

አይሻ በፍርሀት አይኗ እንደፈጠጠ

«ደም እየፈሰሳት ነው ምን እናድርግ . . .» አለች።

ጉልበቴ ተብረከረከ። መተንፈስ ተስኗት የምትንቀጠቀጠዋን አበባ/ሳልዋ/ ልረዳት እችል እንደሆነ እርግጠኛ አልነበርኩም። ይህ በኔ አዕምሮ የሚመላለሰው ፍርሀት አይሻን አድርቋታል። ሌሊት ነው እንዴት እንውጣ! የመኖሪያ ፍቃድ የለን።

በግራና በቀኝዋ እጆቿን እንደጨበጥን በፅኑ ፀለይን። አበባ ግን አሁንም «ፈውሴን አታርክሱብኝ ፀሎታችሁን አቁሙ» አለች።

«እባክሽ ስለገንዘብ ማሰብሽን አቁመሽ ስለ ህይወትሽ አስቢ ብዙ ደም እየፈሰሰሽ ነው።»

ጠዋት ሲሆን እንደ ህፃን ላስቲክ እና ጨርቅ አስታጥቀናት በታክሲ ሆስፒታል አደረስናትና «ለኛ ስትይ ጠንክረሽ አንድ አስር እርምጃ ተራመጂ» አልናት

ተስፋ በመቁረጥ እያየችን

«የአዲስ አበባ አድራሻዬን ታውቂት የለ . . .» አነጋገሯ ዘመዶቼን በሞቴ አርዱልኝ የሚል አይነት ነው። አይሻ እንባዋን እየጠረገች «አትቀጥይ ደህና ትሆኛለሽ» ብላ ሳመቻት።

እኔም አቀፍኳትና «ነገ እንጠይቅሻለን» አልኳት። አይሻ የአበባን የእስልምና ስም ፃፈችና ኢትዮጵያዊት የሚል አድራሻ አድርጋ ቦርሳዋ ውስጥ ከተተችላት።



በሩቁ ተደብቀን እየተውተረተረች ስትራመድ የሆስፒታሉ በራፍ እስክትደርስ አየናት። የሆስፒታሉ በር ላይ ሂ ብላ ስትወድቅ ከውስጥ ነርሶች ተሯሯጠው ሲያነሷትም እያለቀስን አይተናት ወደቤታችን ተመለስን።

በነጋታው ልናያት ሾርባ ቢጤ አዘጋጅተን ሄድን። የእንግዳ መቀበያው ውስጥ የቆመው አስተናጋጅ ገና ስሟንና ዜግነቷን ስንነግረው በቁራኛ እያየን ስልክ ሲያነጋግር አባያችንን ሰብስበን ረጅሙን አስፋልት ሮጠን ታጠፍን። በአይሻ ሀሳብ ፊታችንን ሸፍነን በታክሲ ሆስፒታሉ አካባቢ ዞርን። ብዙ ፖሊሶች ፍስስ ብለዋል።

«የገመትኩት ነገር ነው ፖሊሶቹ እኛን እየፈለጉ ነው» አለችኝ በጆሮዬ

«ምን . . . . አበ . . .ባ ምን ሆና ነው» ታክሲውን አስቁሜ ልወርድ ስል አይሻ አጥብቃ ያዘችኝ።

«ምን እያረግሽ ነው አበባን ማየት አለብኝ። ምንም ያድርጉኝ እንጂ. . . . » ክልብ አለቀስኩ።

እራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም። «ልቀቂኝ እወርዳለሁ» አልኳት አይሻን

አይሻ በጣም ታለቅሳለች። «ሁለታችንም ተይዘን እንቀጠቀጣለን።» እራሷ ሳትረጋጋ እኔን ደጋግማ ልታረጋጋኝ ሞከረች። ቆርጬ ከታክሲው ልወርድ ስል ሀይለኛ ምት እራሴ ላይ በያዘችው ፔርሙዝ መታችኝ። ዞረብኝ።

ባለታክሲው በመገረም ዞሮ ካየን በኋላ መንገዱን ቀጠለ። አይሻ በጣም እየተጠነቀቀች በሦስት አራት ታክሲ እቤታችን ገባን።

ሆዴን እንደጨመቅኩ ሳለቅስ ነጋልኝ።

«ሞት መጥቶ ሲያስፈራራት እንዳታመልጥ እስር ያደረግኳት እኔ ነኝ። አስሬአት ደሟ ፈሶ አለቀ። አስሬአት . . . ያችን ቻድ ማነቅ አለብኝ» ብዬ ደጋግሜ ዛትኩ።

«ሞኝ አትሁኚ። ሞትን በሩጫ የሚያመልጥ የለም። ደግሞም መሞቷን በምን አወቅሽ? ፖሊሶቹ ያንዣበቡት ለሌላ ጉዳይ ከሆነስ? ለማንኛውም ኤንባሲ እንሂድና ጓደኞችን ጠፉች ብለን እናመልክት»

ኤንባሲ ለማመልከቱ አበባ ጊዜ አልሰጠችንም። የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ከባዱ ድባብ እንደሸፈናት ፎቶግራፏ በአሳዛኝ ሁኔታ ተለጥፏል።

እኔና አይሻ መተንፈስ አቅቶን በጣም አየናት። አይሻ ቦርሳዋ ውስጥ የተወቸላት አድራሻ ተፅፏል።

አይሻን ጨምድጄ እንደያዝኩ «ሙክ ብለሽ አንብቢልኝ ሙክ በይ የሚለው አልገባኝም። አንብቢ . . . አንብቢው እያት አ - በባን አየሻ - ት ወይስ እኔ ብቻ ነኝ የማያት . . . »

አይሻ እንዳልኳት ሙክ ብላ ሰው ሁሉ እንዲሰማ አድርጋ አነበበችልኝ።



«እህታችን ሳልዋ መሀመድ ሆስፒታል ውስጥ ሞታ ስለምትገኝ ፎቶግራፏን አይታችሁ የምታውቋት ካላችሁ ለቤተሰቦቿ የምንነግርበትን መንገድ ታሳዩን ዘንድ እባካችሁ ተባበሩን»

ጉሮሮዬን ምርር እያለኝ «አ . . .ህ . . የሚል ቃል አወጣሁ።

ከኤንባሲው ስንወጣ ጀምራ ግራ ክንዴን የጨመደደች የበራችንን ቁልፍ ለመክፈት ለቀቀችኝ። ገፍትራ አስገባችኝና በማስጠንቀቅ «እውነቱን ለማንም እንዳትናገሪ! ከተናገርሽ የናፈቅሻትን እናትሽን አታይም ገባሽ?» ድምፅዋ እንደትዕዛዝ ጠብቆ አይኖቿ ያለማቋረጥ እንባ ያፈሳሉ። የፍርሃት አልነበረም በርግጥ አበባ ለእርሷ ምን ያህል እንደሆነች አውቃለሁ።

ንግግሯን ቀጠለች «እኛ አላጠፋንም። የምትጠጣው ነገር መርዝ እንደሆነ እኔ በምን አውቃለሁ እ!» ራስ ወዳድነቷ በቃላቶቿ ውስጥ ጉልቶ ታየኝ። አፈጠጥኩባት።

«እና ምን ይጠበስልሽ አሁን? ስለራስሽ ብቻ ነው የምታስቢው? እንዲህ እንሆናለን እንዲህ ሆነን ከምትይ መጀመሪያውኑ በዛች ጠንቋይ ሀተታ የሞላሻት አንቺው ነሽ . . . አይደለሽ?! ሆስፒታል በር ትተናት እንድንሄድ ያደረግሽ እራስሹ ነሽ። ለራሳችን አስበን በችግሯ ጊዜ በህመሟ ጊዜ ብቻዋን ትተናት ባንሄድ ከጉዷ ስታየን በተስፋ ትጠነክር ነበር። ይህን የትኛው መፅሐፍ ላይ

እንደሆነ እኔንጃ እንጂ አንብቤአለሁ:: ጆሮዋ ስር ሆነን አይዞሽ ብንላት ልትድን ትችል ነበር . . . ምናልባት:: እኛ ግን እንደማያውቃት ሰው ሁሉ የሆስፒታል በር ላይ ያለ ደጋፊ ጣልናት:: ምንም ነገር ቢደርስብኝ እመርጥ ነበር ኳታ ስሜቴ ይልቅ:: ህሊናዬ ጨቅጭቆ ሊገድለኝ ነው:: የሞቷ ምክንያት አንቺው ነሽ ይለኛል:: ከሁሉም የቆጨኝ እንዳትነቃነቅ እንደ እስረኛ ማሰሬ ነው:: ይህንን ስህተታችንን ማካካሻ ያቺን ቻድ መበቀል አለብን:: እውነቱን የአበባ ቤተሰቦች ማወቅ አለባቸው:: ፖሊስ ማወቅ አለበት:: ይህችን ቻድ ከምታደርገው ወንጀል ካላቆምናት ሌሎችንም መጉዳቷን አታቆምም::»

«እኔ የቻዷን ትዕዛዝ ነግሬአት ነበር:: አበባ በቀን አንዴ ብቻ የሚጠጣውን መድኃኒት እየነገርኳት ሁለቴ ጠጣች:: ያቺ አዋቂ ያለችው አንዴ ብቻ ነበር::»

«አዋቂ? ገና ለዚያች ወንጀለኛ ጠንቋይ ትከራከሪያለሽ?»

ውሃ ቀድታ አመጣችልኝ:: በእጇ ዝግ በይ! የሚል ምልክት ከፊቴ ሆና ደጋገመችልኝና ከጐኔ ቁጭ ብላ አቀፈችኝ::

«ማንም አያምነንም! እራሷ ያንን መርዝ መድኃኒት ብላ ጠጣች የሚል የሞኝ አባባል ምክንያት ብሎ ማንም አይቀበለንም:: እርግጠኛ ነኝ ገዳዮች ተብለን ጀሀነብ እንጣላለን:: ስለዚያች ቻድ ደግሞ . . . የእርሷ አምልኮት ተከታዮች ውስጥ የሚበዙት የንጉስ ዘር ሴቶች



ናቸው:: የጓደኛችን ህይወት ለእነርሱ ተራ ነው:: ጫፏን የሚነካት የለም:: እናም አፋችንን ብንከፍት የምንጐዳው እራሳችንን ነው:: አበባ እንደሆን አትሰማም ተነስታም አትመሰክርም» ምርጫ አልነበረኝም:: በዝምታው በደንብ አሰላሰልኩ:: ራስ ወዳድ ሰው የነገሮችን ተቃራኒ ያስባል . . . እንደ አይሻ አይነቱ::

በዛው ብስል አስተሳሰቧ ሌሊቱን በአበባ ሀዘን ሳይሆን ከሰዎች ጥያቄ እራሳችንን የምንከላከልበትን ቃላት በፅሑፍ ስታስጠናኝ አደረች::

«የመጨረሻ ቀን ምን ምን እንደተባባልን»

«ለብሳ የወጣችውን ቀሚስ ከለር?»

«የት እንደሄድኩ?»

«መቼ እንደመጣሁ»

«ልናመለክት ኤንባሲ መሄዳችንን ጉዳዩን ከማስታወቂያ ማንበባችንን»

ንግግራችን አንድ አይነት እንዲሆን እንደፈልግም ተዋንያን በደንብ ሸመደድን::

በነጋታው ለንቅድስት ደወልን:: ተሰባስበው ቅድስትን ያጀቡ ሴቶች ቤታችንን አጥለቀለቁት:: ለቤተሰቧ ስለመንገር እነርሱው ተባበሩን:: ሁላችንም ጥቁር ለብሰን ሀዘን ተቀመጥን::

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ያልጠበቅናት ሀብታሟ ጓደኛችን ጀሚላ ብርቱካን መስላ ሀዘን ልትደርስ መጣች:: የአበባ የዘወትር ምሳሌ ነበረች:: ላለመዋሸትም እኔም አንዳንዴ እሷን መሆን ተመኝቻለሁ:: ነፍሷን ይማረውና አበባ ከመሞቷ በፊት «እንደ ጀሚላ ጥሩ ሰው ቢያጋጥመኝ እኮ እንደርሷ ሰማይ እነካ ነበር በአንደዬ!» እያለች ትል ነበር::

ግን ይህች የጅዳ ሀበሻ ሴቶች አፍ ውስጥ ሎተሪ እንደደረሳት እድለኛ ሆና የእርሷ አድባር ይለመነን እስከመባል የደረሰችዋ ጀሚላ ከኋላው እንባ ያቀፈ ፊቷን በእኔ በአይሻና በቅድስት ፊት ገለጠችው:: ልቧን የሰበረውን የሀብቷን መነሻ ለመጀመሪያ ጊዜ ተነፈሰች::

ባለጥቁር ሸንጣም መኪና ውስጥ ስገባ ልቤ አላመነልኝም:: የማላውቀው ስሜት «ተይ አትግቢ!» እንደሚለኝ አይነት:: ግን ደግሞ ይህ ሰውዬ ብዙ ተከትሎኛል::

«አምስት መቶ . . .?»

«ላ . . . . . ላ»

«አንድ ሺ ለጥቂት ደቂቃ?»

እንግዲህ እግዜር ያውቃል ብዬ ዘው አልኩኝ:: ሰውዬው ግማሽ ፊቱን የሚሸፍን ሰው ሰራሽ ጢም አድርጐአል:: በዚያ ጨለማ በአንፀባራቂ መነፅር የተቀረውን ፊቱን ለመሸፈን ሞክሮአል:: የመንገድ ሴት



ፈላጊዎች ብዙ ጊዜ ፊታቸውን መለወጫ የተለያየ ዘዴ ቢጠቀሙም የዚህ ሰው ጉዳይ ከበደኝ::

ወዲያው የመኪናው የኋላ መስታወት ዝቅ አለና አይኖቼን የጨፈኑ ባለሰፋፊ መዳፍ እጆች ተከተሉ:: የመኪናው በር ተከፈተና ከንዴ ላይ እንደክትባት ያለ መርፌ ጠቅ ሲያደርገኝ ተሰማኝ:: ወዲያው አውቀው ያቀጠኑት ድምፅ እያባበለ አስተኛኝ::

«አይዞሽ እንጉዳሽም የሚያስተኛ መድሐኒት ብቻ ነው» የነቃሁ ጊዜ አነስተኛ የሆስፒታል ክፍል ውስጥ ጉኔ ተጀቡኖ ተጋድሜአለሁ:: ሀይለኛ ቁስል ጉኔን ጠፍንቶ ይዞታል:: መንቀሳቀስ አቅቶኛል::

ሀኪሜ በፈገግታ «ሀምደላ አሰላማ» ብሉ የእንኳን ለመሻል አበቃሽ ደስታውን ገለፀ::

«ምን ሆኜአለሁ? መኪና ተጋጨ፣ በፍፁም የሆነውን አላስታውስም::» አልኩት

በመሀል ተለቅ ያለች ሴት ገባች:: በጣም በፈገግታ:: ክፍሉን አበቦች ወርሰውታል:: ቀብሬን ለማሳመር የቆሙ መላእክት መሰሉኝ . . . ዶክተሩ፣ ነርሷ::

«ረጋ በይ ስለሆነው ሲሻልሽ እናስታውቅሻለን
ለማንኛውም እኛ በግልጋሎትሽ ስር ነን»

«በግልጋሎትሽ? ቆይ አስረዱኝ!» ጩኸቴን አንጥሮ የሚመልስ ፈገግታ ፍልቅ አድርገው ወጡ።

ስለሆነው ጉዳይ እራሴን ልመረምር ወሰንኩ። ቀኑን ሙሉ የሰራሁትን አስታወስኩ። አዎን በደንብ ትዝ ይለኛል ገንዘብ ፍለጋ . . . ስተታጠብ . . . ገንዘብ ፍለጋ . . . ስለባብስ . . . ስኳኳል ገንዘብ ፍለጋ . . . ስራመድ . . . መኪናና ወንድ ስመርጥ። ቀፋፊዋ መኪና . . . መርፌው በደንብ ቀጭ አለልኝ።

በጣቴ ከጭንቅላቴ ጀምሮ ጠቅ ጠቅ እያደረግሁ ሰውነቴ ልክ መሆኑንና አለመሆኑን ላውቅ ሞከርኩ። ሰውነቴ ምንም ልክ አይደለም። በግራ ጉኔ አላስነካ ያለ ጥልቅ ህመም አለ ከፋሻው ስር። ምን እንደሆንኩ ለማወቅ ሳቂታዎቹን ዶክተርና ነርስ መጠበቅ ነበረብኝ።

ሌሊቱን ስለ እናቴ፣ እህቶቼ፣ ዘመድ ጉረቤት አሰብኩ። ብቸኝነት ገንኖ ሆድ ባሰኝ። አለቀስኩ። ጠያቂ የለኝ የሆንኩትን አላውቅ . . .። ስለገንዘብም አሰላሰልኩ . . . ገንዘብን ከራሴ ማብለጤ ቆጨኝ. . . ለምን ሰርቼ አላገኘሁትም? ለምን ይህ ሁሉ ደረሰብኝ? ብሞትም እኮ ያው የትም ቀረሁ ማለት ነው። ሁኔታዬ አሰጋኝ።

በነጋታው ነርሴ ካርቶን ቸኮላት ይዛልኝ መጣች። የዶክተሩ እንክብካቤ የነርሷ ሁኔታ አበቦቹ . . . እኔ ማን ነኝና ይህ ሁሉ ይደረግልኛል። ሰብአዊነትም ቢሆን ገደብ አለው። ጥርጣሬዬ የመኪና አደጋ ደርሶብኝ ካሳ እንዳይከፍሉን የሚያደርጉት ሙከራ ይሆናል የሚል ነበር



እንጂ የደረሰብኝ በደል ይደርስብኛል ብዬ ፈፅሜ አልጠረጠርኩም።

«ቸኮላት ትወጂለሽ?»

«ማን ይጠላል!» አልኩ በፊቷ የሚርመሰመሰውን ፈገግታ አልወደድኩትም።

«ታውቂያለሽ?! ቆንጆ ወጣትና ጠንካራ እንደሆንሽ?!» ነገሯን ደምድማ ቶሎ ወደ ጥያቄዬ ለመግባት እራሴን በአዎንታ ነቀነቅኩ።

«አሁን ተሽሎኛል ምን እንደሆንኩ ንገሪኝ»

«ዶክተር ሲመጣ ለሁለት እንነግርሻለን» በር በሩን አየች።

«እንዴት ነሽ በሽተኛዬ?» አለ ዶክተሩ

«በሽታዬን ለማወቅ ጓጉቻለሁ እባካችሁ . . .»

«ነገር ከመስማትሽ በፊት ጥሩ ትንፋሽ ሳቢ። ይህ ሆስፒታል የግል ነው። በሁኔታው ብትጮኺ ወይ ብትፈርጪ ፋይዳ የለውም። ነገሩን ረጋ ብለሽ ከተቀበልሽ ግን ቁስልሽን ከምርቀዛ አድነሽ ህይወትሽን ታቆያለሽ። የሚጠብቅሽን ድሎት አትርሺ እ!»

ያለኝን ሀይል ሁላ ተጠቅሜ ጮህኩ

«ምን ሆኜአለሁ?»

«ኩላሊትሽን ሸጠሻል» ፈገግታማ ፊቱ ወደ ቁጡነት ሲቀየር ሌላ ሰው መሰለ::

«ኩላሊቴን? እንዴት . . . መቼ?» ተንተባተብኩ::

«በደንብ አዳምጪ!» ጣቱን አወዛወዘ:: «ሀሙስ ለት ገላሽን ለመሸጥ ስትንጐራደጂ አስታወስሽ? እኛ ታዲያ ከገላሽ ክፍል ኩላሊትሽን መረጥን::»

አለም ጨልማ ታየችኝ:: ጠላኋት:: ግን ደግሞ በጣም ስወዳት ስመኛት ተሰማኝ::

«እሞታለሁ?» ሁለነገሬ ባንዴ ሲደክም ተሰማኝ ተስፋ በመቁረጥ ጥያቄዬን ደገምኩ «እሞታለሁ?»

«ላ . . . ላ . . . አንቺ ወጣትና ጠንካራ ነሽ:: በአንድ ኩላሊት መኖር ትችያለሽ:: ብቻ ተናደሽ በማንወደው መንገድ ከቆምሽ . . .ፖሊስ ህግ ምናምን . . . ጥሩ አይሆንም:: ለኛ በጥቂቱ . . . ላንቺ ግን በትልቁ:: እኛ ከዚች ወንጀል ምንም ሳንነካ እንወጣለን:: አንቺ ግን ሁሉን ነገር ትከስሪአለሽ:: ኩላሊትሽን . . . የምንከፍልሽን ገንዘብ . . . ብሎም አዕምሮሽን»

«ኩላሊትሽን የሰጠሻት ሴት በገንዘቡ ብዙ ነገር የሚያናጋ የእጅግ ሀብታምና ታዋቂ ሰው ሚስት ናት:: ብዙ ደምም ለጥተሻታል:: ህይወት ሰጠሻት ማለት ነው:: ታዲያ ለዚህ ውለታሽ ባሏ የተቀረ ህይወትሽን ሊቀይርልሽ ቃል ገብቷል:: ስለሄደው የአካል ክፍልሽ እርሺ:: አይመለስም:: ስለሚመጣው ህይወትሽ አስቢ:: አንቺ



ካሁን ወዲያ የሚያደክም ስራ እና አድካሚ የህይወት ውጣ ውረድ መሸከሙ ቀላል ላይሆንልሽ ይችላል:: ጤንነትሽን ለመጠበቅ የተደላደለ ገንዘብ ያስፈልግሻል:: ጥሩ ልጅ ሆነሽ የተወሰኑ ወረቀቶች ላይ መፈረም ብቻ ችግርሽን ይወጣልሻል:: እንዳልኩሽ ጥሩ ልጅ ሁኚ» ትተውኝ ወጡ::

ስለምን ላልቅስ? ስለተቀደደው ቆዳዬ ወይስ ሳላውቀው ስለተቀዳው ደሜ? ወይስ ሳልፈቅድ ስለተሰረቀው ኩላሊቴ? ወይስ ስለመብቴ . . . ለማን እጮሀለሁ:: ለሁሉም ደከመኝ . . . ሀይል አነሰኝ . . . ተበሳጨሁ . . . የአለም መጥፎ ስሜቶች ሁሉ እላዬ ላይ ሰፈሩ::

ሌባው ዶክተር እንዳለው በሰላም ወረቀቶች ላይ ፈረምኩ:: በተለያየ መልኩ የተደረገልኝ የኩላሊቴ ክፍያ ሀብታም አሰኘኝ::

* * * * * *

አይሻንም እንደቀላል ተሰናበትኩ:: ለዚያውም አልጋዬ ላይ በተወችልኝ ማስታወሻ:-

መርሀባ! ይህንን ስታነቢ እኔ እርቄ እገኛለሁ:: ለስንብትሽ አልቅሼ አዝኜአለሁ:: በእንደዚህ ሁኔታ ትቼሽ

ለመሄድ የራስ ወዳድነት ስሜት ስለተሰማኝ ፊት ለፊት ልጋፈጥሽ እና ቻው ልልሽ አልቻልኩም።

ግን ከዚህ በፊት ያላልኩሽን ምክር ልምከርሽ። ገንዘብ እኛ ባመጣነው መልኩ ከተገኘ ደስታን አያስገኝም። እራሴን አይሸጡ መሸጥ ሽጬ ገንዘብ አግኝቻለሁ። ግን ይህ እዚህ አልፌው የምሄደው ምስቅልቅል ህይወት እድሜ ልኬን ይከተለኛል ብዬ ሰግቼአለሁ። ካሁኑ የለበስኩት ልብስ ይቀፈኝ ጀምሮአል። በዚህ ከቀጠለ ባገኘሁት ገንዘብ የማደርገው የኑሮ መሻሻል የድሮ ጥላሸት ህይወቴን በየደቂቃው የሚያስታውሰኝ ከሆነ ምኑን ኖርኩት?! ማን እንደሚያስቀናኝ ታውቂያለሽ? ያች ፅኑ ሴት ቅድስት። ምክሬም እንደበፊትሽ ከሷው ጋር እንድትጠጊ ነው። ያሁኑ መንገድሽ እንደሳልዋ ወይ እንደ ጀሚላ ወይ ደግሞ እንደ እኔ አይነት ዕድል ላይ ነው የሚጥልሽ። የሳልዋን እና የጀሚላን የሕይወት ሰቆቃ አይተሽዋል። የተሻለ የመሰለሽ የኔ ሕይወት ደግሞ ውስጡ ለቁስ ነው። ማድረግ የነበረብን እንደቅድስት እራሳችንን ጠብቆ ደረጃ በደረጃ የፈለግንበት መድረስ ነበር። እኛ ግን እራሳችንን ሰውተን ገንዘብ በላያችን ላይ እንዲጫወት ፈቀድን።

ለማንኛውም በድንገት አዲስ አበባ ከተገናኘን ዘመናይ ብለሽ በእውነተኛ ስሜ ጥሪኝ አይሽ።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋



# ምዕራፍ አስር

እራሴን ፍለጋ በሄድኩ ቁጥር ራሴን ሌላ ውሸት ሌላ ማስመሰል ውስጥ አገኘዋለሁ። ለምዶብኛል። በጣም የሚቀፈውን ኮሳሳ ሽማግሌ አረብ «ሰኔ ልጅ ሆነህ ትታየኛለህ ወንዳ ወንድነትህ እንዳለ ነው» ብዬ ውሸቴን አቀልጣለሁ። ለሊቱንም ሽማግሌው ሲያንኮራፋ እንቅልፍ አይወስደኝም። በተነፈሰ ቁጥር የሚያወጣውን ደስ የማይል ትንፋሽ ልሸሽ ፊቴን ሳዞር ይነቃና እንደነበርኩ አዙሮ ይባስ ጥብቅ አድርጐ አቅፎኝ ይተኛል። ብቻውን መተኛት ይፈራል። እኔም በየቀኑ እርጅናን ከአይኑ እያነበብኩ ወደፊት የሚጠብቀኝን ህይወት ፈራሁት። ኡፍ! ማርጀት ሲያስጠላ . . . ወጣት እያለን የተሰጠንን ውበት ተስፋ ሀይል ብዙ ብዙ ነገር መቀማት . . . ሲያስፈራ። ከጐኑ ተኝቼ ብዙ አሰላስላለሁ። እንደዛ እንዳልኮራሁ ለውበት እንዳልተንበረከኩ አሁን እንዴት እራሴን ከሽማግሌ ጋር አስተኛለሁ። ውበት በጣም እወድ የለ!። ታዲያ ሽማግሌ ላይ የነበረ ውበት ብቻ ነው ያለው . . .። ሽማግሌውስ ለምን ሚስቱን አያቅፍም? በርግጥ እንደርሱ አርጅታ ይሆናል። ሙቀት እንደሚፈልግ ደጋግሞ አስጠግቶ ሲያቅፈኝ ተረድቼአለሁ። እርሱ ሙቀት ሳይሰጠኝ ከእኔ ብቻ ለሚወስደው ሙቀት የሚሰጠኝ ክፍያ በቂ ነውን? አንዳንዴ ከእንቅልፌ ስነቃ

ሽብሽብ አካላቱ ይቀዘቅዘኛል:: ያ ሀይለኛ ማንኮራፋቱ ቀጥ ይልና ምንም ድምፅ አያሰማም:: ጠጋ እልና ትንፋሹን አዳምጣለሁ:: እፈራለሁ ሞቶ ይሆን እንዴ?! እያልኩ:: የዛኑ ጊዜ እምላለሁ ዛሬ የመጨረሻ ሌሊት ይሆናል ከርሱ ጋር የማድረው . . . እልና፤ ቀን ሲሆን በስልክ የሚያወራው ወሬ እግሬን ይጐትተዋል:: ሁሌ የሚያወራው ትልቅ ስለሆነው ድርጅቱ ነው:: ታዲያ ስለዚህ ድርጅቱ ሲያወራ እርጅናው ከላዩ ላይ የጠፋ ይመስላል:: እርጅናው የሚሰፍርበት ምሽት ላይ ነው:: መነፅሩን ሲያወልቅ አይኖቹ ደጋፊ ያሻሉ:: ልብሱን ሲያወልቅ ገላው ከሌላ ሰው ሙቀት ይፈልጋል:: በጣም ይተኛል ሰውዬው . . . ደክሞታል::

ግንኮ ማስመስሌን አውቆታል:: ሽማግሌው ካንድ ጓደኛው ጋር ሲያወራ «'አነ አንድ ከዛባ' /ውሽታሟ ጋ ነኝ/» ብሎ ሲለው ሰማሁ:: «ሁሌ ስትዋሸኝ ውሽቷ ይጥመኛል:: ደግሞ ውሸቷ ያልበሰለ ነው:: ሽምግዬ እያለሁ ገና ነህ ትለኛለች:: ውሽቷ እስኪሰለቸኝ ልያትና ውሽታም ብዬ አባርራታለሁ»:: የገረመኝ ግን ታወቀብኝ ብዬ አለማፈሬ ነው:: እንዳንዴ ሙልጭ እድርጐ ሰድቦኝ ገፍቶ ከቤቱ እስካላወጣኝ አልሄድም ብዬ እቀመጣለሁ:: ክብር የለ ስሜት የለ ሌላው ቢቀር ንዴት የለ:: አጥንት የሚሰብር ስድብ ሰምቼም . . . ውርደት የለም:: ምንም አይመስለኝም:: የሰውነት ስሜቶቼ ድብን ብለው ሞተዋል::



ለዚህ ሕይወቴ የከለር ዝርዝር ቢሰጠው ከለሩ ያለመወላወል ጥቁር ነው:: ሀይወቴ ከለሩ ጠቁሯል:: ለዚያውም ሙሉ አዕምሮዬን ካበላሸ ጥላሸት ጋር!::

ስናገር ስሄድ ስራመድ ስቀመጥ በስልት ሆኖአል:: ስስቅም በስልት ስለምስቅ አስካካለሁ:: በሲጋራ እየጠቆረ ያለውን ከንፈሬን ለመሸፈን ደማቅ ሊፕስቲክ እጠቀማለሁ:: የሲጋራ ጭስ መንስኤው የአረቦቹ ግፊት ነበር:: እነርሱ እንደሆን ለኔ ባልተፈጠረ አለም ውስጥ ከትተውኝ ከውጭ ሆነው ይስቁብኛል:: ከከተቱኝ አለም ስወጣ እራሴን እጅግ ረክሶ አገኘዋለሁ:: ያን ለመርሳት ጭስ ማየት ፈለግኩ:: ውስጤ ያጨሰው ነገር በሲጋራ ትነት ሲወጣ የማየው መሰለኝ:: ሲጋራ ማጨስ በዚህ መልኩ ለመድኩ:: ከንፈሬን የምሸፍንበት ደማቁ ሊፕስቲክ አያምርብኝም:: አይኖቼም ያዘሉትን ሀዘን ለማጥፋት በወፍራሙ እኩላቸዋለሁ:: ለራሴም ይታወቀኛል . . . ጭራቅ እንደመሰልኩ፤ ከማማር ይልቅ:: በዚህ ሦስት ዓመት ውስጥ ልጅነቴ ጥሎኝ የሄደ ይመስላል:: ካንዱ ከሌላው ጋር ስጫከር እነርሱም ምጥጥ እያረጉ ሲያባርሩኝ . . . ተስፋ ቆረጥኩ::

እነዛ ትልልቅ ሕልሞቼ፤ ቪላ ቤትና መኪና ልይዛቸው በሮጥኩ ቁጥር እያላገጡ ይሸሹኛል:: በርግጥ እንደ እኅቴ ልጅ እጄን በወርቅ አንባሮች ሞልቼአለሁ:: ለእነዚህ ሕይወተ-ቢስ ብልጭልጮች ሕይወቴን ከፍያለሁ:: በእነሱ ሰበብ እራሴን ፍለጋ እባክናለሁ:: ኩራቱ ልስላሴዬ ልጅነቴ አስተሳሰቤ . . . ወይ ነዶ!::

## ምዕራፍ አስራ አንድ

እመለስ ይሆናል። ምናልባት እራሴን ፈልጌ ማግኘት ከቻልኩ . . . ካልቻልኩ ግን እዚሁ በስደት መቅረቴን እመርጣለሁ። የምመለሰው ያጠፋሁትን እኔነቴን ካገኘሁ ብቻ ነው። ወዜን ትዕግስቴን አደቤን ስነ ስርዓቴን ህልሜን ተስፋዬን እንደነበር ማግኘቱ ቀላል አይመስለኝም። ግን እሞክራለሁ . . . እኔነቴን ካገኘሁ እመለሳለሁ። እመጣለሁ ምናልባት . . .።

ግን ደግሞ ይህ አገር እኔነቴን የማይመልስልኝ ከሆነ ምናልባት አንድ ቀን፡-

«'አልባብ ይጅለክ ሚኑ ሪህ ዚቱ ወእስተያህ' /ሽታ የሚያመጣልህን በር ዝጋውና እረፍ/ የሚለው ተረታቸው የገባኝ እለት የስደትን በር ለመዝጋት አገሬ እገባለሁ።»



## ምዕራፍ አስራ ሁለት

ትህትና ከፊቷ የተዝረከረኩትን ከደርዘን በላይ የሚሆኑ የፖስታ ኪሶች ወደ መሳቢያ ከተተችና በሀሳቧ አብሮ አደግ ጓደኛዋን «አይ መሲ! እንዳልሽው ቶሎ እራስሽን አግኝተሽ በመጣሽ። በጣም ናፍቀሽኛል። መጨረሻሽ ምን ይሆን?» ብላ «የህይወቱ ከለር ጥቁር ነው» በሚል ለፃፈችላት የልብ ጓደኛዋ ተከዘች። ለደብዳቤዋም አመስግናታለች . . . . ትህትና። የስደትን ችግር ሳይረዳ ልሂድ ልሰደድ የሚላትን ፍላጐቷን የመሲ ደብዳቤ አብርዶላታል።

ደግማ «ምስኪን መሲ! ምስኪን . . .» እያለች በጣም አጫጭር የሰላምታ አንቀፆች የያዙትን እጅግ ረጃጅም ደብዳቤዎችን በቅደም ተከተላቸው በወረቀት ማያያዣ አንድ ላይ አያያዘቻቸውና በትልቁ ይድረስ ለአዲስ ህትመት ድርጅት የሚል ፅሁፍ አስፈረችበት።□

*ተፈፀመ*